# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሐሙስ

84ኛ ዓመት ቁጥር 100 ታኅሣሥ 10 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









# በኤሌክትሪክ መሠረተ-ልማቶች ላይ በሚፈጸም ስርቆት የአንድ ነጥብ 7 ቢሊዮን ብር ኪሳራ ደረሰ

ኢያሱ መሰለ

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ሁለት ዓመታት ብቻ በኤሌክትሪክ መሠረተ-ልማቶች ላይ በተፈጸመ ስርቆት የአንድ ነጥብ 7 ቢሊዮን ብር ኪሳራ እንዳጋጠመው የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል አስታወቀ። ብረት አቅላጭ ፋብሪካዎች ለግብዓትነት የሚጠቀሙትን ብረት ሕጋዊነት በማረጋገጥ ሀገራዊ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ አሳሰበ።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል የኮርፖሬት ኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ ሞገስ መኮንን ለአዲስ ዘመን እንደገለጹት፤ በ2015/16 ዓ.ም ብቻ ተቋሙ በሚያስተዳድራቸው የኤሌክትሪክ መሠረተ-ልማቶች ላይ በተፈጸመ ስርቆት የአንድ ነጥብ 7 ቢሊዮን ብር ኪሳራ አጋጥሟል።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል በሀገር አቀፍ ደረጃ የኃይል

በኤሌክትሪክ መሠረተ-ልማቶች... ወደ ገጽ 8 ዞሯል











## ‹‹በምትክ ቤቱ ላይ ቅሬታ አቅርበን ጠብቁ በተባልንበት የቤታችን መብራት ተቆርጦብናል»

- እነ ወይዘሮ እየሩሳሌም ታዬ

## ‹‹ሰው ቤት ውስጥ እያለ እኛ የቆረጥነው መብራት የለም»

- በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 1 ቤቶች አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ኃላፊ

በሞገስ ተስፋና መክሊት ወንደወሰን

አዲስ አበባ፡- የልማት ተነሺ በመሆናችን በምትክ ቤቱ ላይ ቅሬታ አቅርበን ጠብቁ በተባልንበት የቤታችንን መብራት ተቆርጦብናል ሲሉ በቂርቆስ ክፍለ ከተማ የወረዳ አንድ ነዋሪዎች እነ ወይዘሮ እየሩሳሌም ታዬ ቅሬታቸውን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ገለጹ።

በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 1 ቤቶች አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ደምሰው ትኩ በበኩላቸው ሰው

‹‹በምትክ ቤቱ ላይ ቅሬታ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል

# ሠላማዊ ሰልፉ ሕዝቡ ምን ያክል ሠላም እንደሚሻ ያሳየበት እንደሆነ ተገለጸ

## - በአማራ ክልል በተለያዩ ከተሞችና አካባቢዎች ሕዝባዊ ሰልፍ ተካሄደ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- በክልላችን የተካሄደው ሠላማዊ ሰልፍ ሕዝባችን ምን ያክል ሠላም እንደሚሻ ያሳያበት ነው ሲሉ የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አረጋ ከበደ ገለጹ። በክልሉ የተለያዩ አካባቢዎች መንግሥት የሚያከናውነውን የሠላም ማስከበር ተግባርና የልማት ሥራዎችን የሚደግፍ ሕዝባዊ ሰልፍ "ሠላም ለሁሉም ሁሉም ለሠላም" በሚል መሪ ሀሳብ ተካሂዷል።

ርዕሰ መስተዳድር አረጋ ከበደ በአማራ ክልል የተካሄደውን ሠላማዊ ሰልፍ አስመልክቶ ትናንት በሰጡት መግለጫ እንዳሉት፤ ሠላማዊ ሰልፉ ግጭት በቃን፣ የምንፈልገው ሠላምና ልማት ነው የሚል መልዕክት የያዘ ነው። ሠላማዊ ሰልፉ ሕዝባችን ምን ያክል ሠላም እንደሚሻ ያሳየበት ነው ብለዋል።

ርዕሰ መስተዳድሩ ሰልፎች እንዳይካሄዱ ለማስፈራራት እና ለማሸበር የተደረገው ጥረትም አልተሳካም ነው ያሉት። ሕዝቡ ግን ዛቻ እና ማስፈራሪያዎችን በመተው ሠላምን እንደሚፈልግ በነቂስ ወጥቶ አሳይቷል ብለዋል።



ሰልፉ ጥያቄ አለኝ የሚል ኃይል ሁሉ ችግሮችን በውይይት ነው መፍታት የሚገባው የሚለውን የሚያሳስብ መሆኑንም አመላክተዋል። ሕዝብ ከጎናችን ነው እያለ መንግሥትን በኃይል እናስወግዳለን የሚለውን ኃይል ያጋለጠ መሆኑን ተናግረዋል።

ሠላማዊ ሰልፉ ሕዝቡ... ወደ ገጽ 8 ዞሯል





# በክልሎቹ የወባ በሽታ ወረርሽኝ ለመግታት የሚደረገው ጥረት ተጠናክሮ ቀጥሏል

**ክብረአብ በላቸው**

አዲስ አበባ፡- በክልሎቹ የወባ በሽታ ወረርሽኝን ለመግታት የሚደረገው ጥረት ተጠናክሮ መቀጠሉን የማዕከላዊ ኢትዮጵያና የሲዳማ ክልሎች ጤና ቢሮዎች ገለጹ።

የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጤና ቢሮ ምክትል ኃላፊና የክልሉ ኅብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር አቶ ማሙሽ ሁሴን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ ባለፉት አራት ወራት በክልሉ ከፍ ያለ የወባ ወረርሽኝ ስርጭት ተከስቶ ነበር፤ ነገር ግን ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ባሳተፈ መልኩ በተሠራው ሥራ ስርጭቱ እንዲቀንስ ተደርጓል።

የወባ ወረርሽኙ በተለየ ሁኔታ የተስፋፋባቸውን አካባቢዎች በመለየት እነዚህ አካባቢዎችን መሠረት ያደረገ ሥራ በመሥራትና የክልሉን አመራር በማሳተፍ በሽታውን ለመቆጣጠር ጥረት እንደተደረገ ተናግረዋል።

በሽታውን ለመከላከል የሚያግዙ እንደ አጎበር ያሉ ቁሳቁሶችን በአግባቡ ከመጠቀም አኳያ በኅብረተሰቡ ዘንድ የነበረው የግንዛቤ እጥረት ወረርሽኙን በቀላሉ መቆጣጠር እንዳይቻል ምክንያት ሆኗል ያሉት አቶ ማሙሽ፤ ይህንን ችግር ለመፍታትም ለኅብረተሰቡ ግንዛቤ የመፍጠር በትኩረት ተሠርቶ በአጭር ጊዜ ውጤት እንደተገኘ አብራርተዋል።

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል 80 በመቶ የሚሆኑ ወረዳዎች ለወባ በሽታ ተጋላጭ ናቸው ያሉት አቶ ማሙሽ፤ በክልሉ ከ600 ሺህ በላይ ቤቶች ላይ ቤት ለቤት አሰሳ ማድረግ ተችሏል፤ በዚህም የበሽታው ምልክት የታየባቸው ሰዎች ሕክምና እንዲያገኙ ተደርጓል ብለዋል።

በሽታውን በዘላቂነት ለመከላከልም አንድ ነጥብ ስድስት ሚሊዮን የሚሆን አጎበር ማሰራጨት ተችሏል፤ በተጨማሪም በሽታው በስፋት በሚታይባቸው 31 ወረዳዎች ላይ የኬሚካል ርጭት ተደርጓል ያሉት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤ በበሽታው በከፍተኛ ደረጃ ተጋላጭ የሚሆኑ እናቶችና ሕፃናትን ሕይወት ለመታደግ ርብርብ መደረጉን አንስተዋል።

የሲዳማ ክልል ጤና ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ በላይነህ በቀለ በበኩላቸው፤ በክልሉ የወባ በሽታ ለመከላከል በተሠራው ሥራ የበሽታውን መስፋፋት መግታት ተችሏል።

በቀሩት ሦስት አካባቢዎች አሁንም የበሽታው ምልክት በስፋት ይታያል። ይህንን መነሻ በማድረግ አመራሩን ጨምሮ ሁሉንም ባለድርሻ አካላት ያሳተፈ ሥራ በመሥራት ወረርሽኙ በኅብረተሰቡ ላይ የከፋ ጉዳት እንዳያደርስ ጥረት እየተደረገ ነው ብለዋል።

አካባቢን ፅዱ ማድረግና የአልጋ አጎበር በአግባቡ መጠቀም የወባ በሽታ ለመከላከል አስተዋፅዖው ከፍተኛ መሆኑን ገልጸው፤ ኅብረተሰቡ እነዚህን የመከላከያ መንገዶች በአግባቡ ተግባራዊ እንዲያደርግ የግንዛቤ መፍጠር ተግባራት እየተከናወኑ ስለመሆኑ ተናግረዋል።

እስከአሁን በክልሉ አንድ ሰው በወባ በሽታ ምክንያት ሕይወቱን ማጣቱን የተናገሩት አቶ በላይነህ፤ በቀበሌ ደረጃ ያሉ የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች በሠሩት ጠንካራ የመከላከል ሥራ የሰዎችን ሕይወት መታደግ መቻሉን አንስተዋል።

በክልሉ የወባ በሽታን ለመከላከል ከ2015 ዓ.ም ጀምሮ 915 ሺህ የአልጋ አጎበር ተሰራጭቷል፣ በተጨማሪም በአራት ወረዳዎች በሚገኙ 23 ቀበሌዎች የኬሚካል ርጭት ተካሂዷል ያሉት ምክትል ቢሮ ኃላፊው፤ የኬሚካል ርጭቱ ከፍተኛ የወባ ወረርሽኝ በሚታይባቸው አካባቢዎች ተጠናክሮ መቀጠሉን ተናግረዋል።

በአጠቃላይ በክልሎቹ በበሽታው የተያዘ ሰው ሕክምና ለማግኘት ወደ ጤና ተቋማት ሲሄድ በቂ የሕክምና አገልግሎት ማግኘት እንዲችል የጤና ተቋማትን በግብዓት የማሟላት ሥራ እንደተሠራ አብራርተዋል።

# የተማሪዎች ሥነ ምግባር ጉዳይ

**ነፃነት ዓለሙ**



የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ያወጣው መመሪያ ትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ ሲጋራ ሲያጨስ የተገኘ ተማሪ ከትምህርት ቤት ለአንድ ዓመት እንደሚያግድ የሚናገሩት በአንዶዴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ምክትል ርዕሰ መምህር የሆኑት አቶ ወ/አብ እሸቱ፤ እሳቸው በሚሠሩበት ትምህርት ቤት ድርጊቱን ሲፈፅሙ የተያዙ ተማሪዎች እንደነበሩ ያስታውሳሉ።

ነገር ግን ቤተሰብ በመጥራት ተመካክረንና ለተማሪዎቹም ምክር ሰጥተን ድጋሚ በዚህ ድርጊት ከተገኙ እርምጃው እንደሚወሰድባቸው በማስጠንቀቅ በይቅርታ ያለፍንበት ሁኔታ አለ ይላሉ።

ትምህርት ቤት ማረቂያ፣ ማረሚያና ማስተካከያ ነው የሚሉት ምክትል ርዕሰ መምህሩ፤ በሕጉ መሠረት ከዚህ ብናስወጣቸው ሊገጥማቸው የሚችለውን ከዚህ የከፋ ነገር በማሰብ ይቅርታው እንደአማራጭ መወሰዱን ይገልፃሉ።

ለሌሎች የሥነምግባር ችግሮችም ወደ እርምጃ ከመግባታቸው በፊት የሚወስዷቸው እርምቶች መኖራቸውን የገለጹት ምክትል ርዕሰ መምህሩ፤ ካልሆነ ግን እርምጃዎቹን ለመውሰድ እንደሚገደዱ ያስረዳሉ።

ምክትል ርዕሰ መምህሩ እንደሚሉት ትምህርት ቤቱ በተማሪዎች ሥነምግባር ዙሪያ የተለያዩ ሥራዎችን እየሠራ ይገኛል። ከእነዚህ ውስጥ የተማሪ ክበባትን ማደራጀት አንዱ ነው። ትምህርት ቤቱ በሥነ ምግባር ላይ የሚሠሩ የተለያዩ የተማሪ ክበባት አሉት። እንደ ምሳሌም በተማሪዎች ሚኒ ሚዲያ ክበብ አማካኝነት በተለያዩ ቋንቋዎች የተማሪዎችን ሥነ ምግባር በተመለከተ መልዕክቶች ይተላለፋሉ ነው ያሉት።

ከሚኒ ሚዲያ ክበብ በተጨማሪም የፀረ ሙስና ክበብና የተማሪ ትራፊክ ክበብ እንዳለ ገልፀው፤ የተማሪዎች ፓርላማንም አደራጅተውና ሚኒስትሮችን አስመርጠው በጉዳዩ ዙሪያ እየሠሩ መሆኑን ይገልፃሉ። እነዚህ ሥራዎችም የመማር ማስተማር ሂደቱን ሠላማዊ እንዳደረጉት ያስረዳሉ።

በተለይም ከባለፈው ዓመት ወዲህ በሥነ ምግባር ዙሪያ የተለያዩ ለውጦች እንዳሉ ገልፀው፡- አሁን ላይ ጉዳዩ አሳሳቢ የሚባል ደረጃ ላይ አለመሆኑን ይጠቁማሉ። በፊት በፊት ይታዩ የነበሩ የቡድን ፀቦች እንደነበሩ አስታውሰው፡- አሁን ላይ ካለው ክትትልና ቁጥጥር አኳያ አልፎ አልፎ ካልሆነ በቀር ችግሩ መቀረፉን ይገልፃሉ።

አርፋጅ ተማሪዎችን በተመለከተ ለመጀመሪያ ጊዜ ያረፈደ ተማሪ በዩኒት ሊደር፣ ሁለተኛ ሲያረፍድ ዩኒት ሊደርና የክፍል ኃላፊው፣ ሦስተኛ ሲያረፍድ ደግሞ ወላጁንና ራሱን ተማሪውን በማድረግ የሚመከርበት ሁኔታ ስላለ እንደ ማርፈድ ያሉ ችግሮች እየቀነሰ የሄደበት አግባብ እንዳለ ያብራራሉ።

በዳግማዊ ምኒሊክ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር የሆኑት አቶ በላይ ወልደፃዲቅ፤ በበኩላቸው በፊት ከነበረው አኳያ የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች ማርፈድ እየቀነሱ፣ የሰልፍ ሥነ ሥርዓት ላይ እየተገኙና የሕዝብ መዝሙር እየዘመሩ መሆናቸውን ይገልፃሉ።

የሥነምግባር ችግር ባለባቸው ተማሪዎች ላይ የሚወሰዱ እርምጃዎችን በተመለከተም በመጀመሪያ እርስ በእርሳቸው ማለትም በተማሪዎች እንዲመከሩ እንደሚደረግ ገልፀው፤ በዚህ ምክር በቀላሉ የሚመለሱ እንዳሉ ያስረዳሉ። የተወሰኑት ደግሞ በመምህራን ተመክረው የሚመለሱ እንዳሉም ይጠቅሳሉ። ከዚህ ካለፈ ደግሞ በምክትል ርዕሰ መምህር ይመከሩና አልፈው ከመጡ ርዕሰ መምህር ወላጅ ጠርቶ ቃለጉባኤ በመያዝ የተማሪውን ሥነምግባር ከመመለስ አኳያ የሚሄዱበት አግባብ እንዳለ ያብራራሉ።

ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የተማሪ ተወካዮች፣ ወላጆች፣ መምህራንና የፀጥታ አካላት ጋርም በጋራ እየሠሩ እንዳሉ ይገልፃሉ። ከዚህ ባሻገርም በትምህርት ቤቱ የሞባይል ስልክ ይዞ መገኘት እንደማይቻል ገልፀው፤ ይህ እንዳይሆን ተፈትሸው እንደሚገቡ ያስረዳሉ። በዚህ ዓመት ሱስ ከመጠቀም ጋር በተያያዘ ተለይተው የተያዙ ወደ ሰባት የሚጠጉ ተማሪዎች እንዳሉ ገልፀው፤ ከትምህርት ቤት ማገዱ መፍትሔ ስለማይሆን ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን የሚለወጡበት መንገድ ላይ እየሠሩ እንዳሉ ያስረዳሉ። እነርሱን የመለየቱ ሥራም ሱስ ያለባቸው ተማሪዎች ምን አይነት ባሕሪ ያሳያሉ ከሚለው በመነሳትና ሥልጠና በመስጠት በተማሪ ተወካዮች አማካኝነት እንደተሠራ ያስረዳሉ።

ከመለየቱ ባሻገርም ሥልጠና በመስጠትና ሰው መድቦ ክትትል በማድረግ ከሰባቱ ተማሪዎች ሦስቱ ከሱሱ የወጡበት ሁኔታ እንዳለም ይጠቁማሉ።

የትምህርት ሥራ የሁሉንም አካላት ርብርብ ይጠይቃል የሚሉት ርዕሰ መምህሩ፤ ሁሉም ተቀናጅቶ የተማሪዎችን ሥነምግባር በማረቁ ረገድ ቢሠራ ተማሪዎች ላይ የተሻለ የባሕሪ ለውጥ ማምጣት ይቻላል የሚል መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

የአዲስ አበባ ትምህርት ቢሮ ተማሪዎች በትምህርት ቤት በጥሩ ሥነ-ምግባር በመታነጽ ለራሳቸውም ሆነ ለማኅበረሰባቸው እንዲሁም ለሀገራቸው ጠቃሚ ዜጋ ሆነው ሊቀረጹ እንደሚገባ በማመን የተማሪዎች የሥነ-ምግባር ችግር በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ እየፈጠረ ያለውን አሉታዊ ተፅዕኖ ለማስተካከል ያለመ የተማሪዎች የሥነ ምግባር መመሪያ ቀርፆ እየሠራ እንደሚገኝ ይታወቃል። የሥነምግባር ጉዳይ ትውልድን ከማነፅ አኳያ ያለው ሚና አይነተኛ ነውና በዚህ ረገድ በከተማዋ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች አሁን ላይ ምን እየሠሩ ይገኛል?

# የ19 ሚሊዮን ዶላር ፕሮጀክት ተግባራዊ ለማድረግ የጋራ ስምምነት ተፈረመ

**ታምራት ተስፋዬ**



ዶ/ር ደረጄ ድጉማ



ኢንጂነር ለሊሴ ነሜ

አዲስ አበባ፣ በሃገር አቀፍ ደረጃ የአየር ብክለት መጠንን ለመቀነስ፣ ፅዱና ከብክለት የፀዳች ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ የሚያግዝ ከ19 ሚሊዮን ዶላር በላይ ወጪ የሚደረግበትን ፕሮጀክት ለመተግበር የጋራ ስምምነት ተፈርሟል።

ለፕሮጀክቱ ተግባራዊነትም በአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን፣ በጤና፣ በግብርና፣ በኢንዱስትሪ፣ በትራንስፖርትና ሎጂስቲክስ፣ በከተማና መሠረተ ልማት፣ በውሃና ኢነርጂ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች እንዲሁም በብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ መካከል የመግባቢያ ስምምነት ትላንት ተፈርሟል።

በፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣንና በጤና ሚኒስቴር አስተባባሪነት ተግባራዊ በሚደረገው ፕሮጀክት ትግበራ የመግባቢያ ስምምነት ላይ የጤና ሚኒስትር ዴኤታው ዶክተር ደረጄ ዱጉማ እንደገለፁት፣ የአየር ብክለት በአካባቢ ብሎም በሰው ልጆች ጤና በተለይ በሕፃናት በእናቶች ላይ ከባድ ጉዳትና ህልፈትን የሚያስከትል ነው። በኢትዮጵያም በየዓመቱ ከ 39 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ሰዎች ህልፈትና ለበርካቶች የአስም፣ የሳንባ፣ የልብ፣ የኩላሊትና የጉበት ሕመም መንስኤ መሆኑ በጥናት ተረጋግጧል።

መሰል ቀውስን የሚያስከትለውን አየር ብክለት ጨምሮ የአካባቢ ብክለትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር ከቅርብ ዓመታት ወዲህ መንግሥት ልዩ ትኩረት በመስጠት የተለያዩ ተግባራትን እያከናወነ ስለመሆኑ ያስገነዘቡት ዶክተር ደረጄ፣ ሕጎችን በአግባቡ ማስተግበር፣ ታዳሽ የኃይል ምንጮችን ማስፋት፣ በኤሌክትሪክ ኃይል የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎችን ማብዛት፣ ፅዱና ከብክለት የፀዳች ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ የሚያስችሉ የኮሪደር ልማትን የመሳሰሉ ግዙፍ ፕሮጀክቶችም የዚሁ አካል መሆናቸውን አብራርተዋል።

እነዚህና መሰል እርምጃዎችም ከተማን ከማዘመን ባሻገር የአየር ብክለትን በመቀነስ ረገድ አይነተኛ አስተዋፅዖ እያደረጉ መሆናቸውን ያስገነዘቡት ሚኒስትር ዴኤታው፣ ከ19 ሚሊዮን ዶላር በላይ ወጪ የሚደረግበት በአውሮፓ ኅብረት የገንዘብ ድጋፍ የሚተገበረው ፕሮጀክትም፣ በሃገር አቀፍ ደረጃ የአየር ብክለት መጠን ለመቀነስ፣ ፅዱና ከብክለት የፀዳች ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ የተጀመሩ ጥረቶችን ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል ነው›› ብለዋል።

በትግበራው በተለይ በጤናው ዘርፍ በተቋማት ውስጥ ደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ማዘመንና የአገልግሎት ጊዜ ያለፈባቸው መድኃኒቶችን በአግባቡ ማስወገድን ጨምሮ የተለያዩ ለብክለት መንስኤዎችን የማስተካከልና የመቆጣጠር ተግባራት እንደሚከናወኑም አስረድተዋል። በተለይ በአዲስ አበባ ከተማ የሚገኙ ሦስት የአየር ብክለት መለኪያ መሣሪያዎች አቅም ማጎልበትና የማስፋት ሥራ እንደሚከናወንም ጠቁመዋል።

የፌዴራል አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር ኢንጂነር ለሊሴ ነሜ በበኩላቸው፣ ‹‹ፕሮጀክቱ በቀጣይ አምስት ዓመታት ተግባራዊ የሚሆንና የአየር ጥራትን ማረጋገጥ፣ በብክለት ምክንያት በሰው ልጆች ላይ የሚደርስ ሞት መቀነስና በአካባቢ ላይ የሚደርስ ጉዳትን ማስቀረትን ዓላማው ያደረገ ነው›› ብለዋል።

በስምምነቱ በተቋማት የሚተገብሩ ሥራዎች በዝርዝር መለየታቸውና ፅዱ ኢትዮጵያን ለመፍጠር በተሰጠ አቅጣጫ መሠረት ሁሉም የቤት ሥራውን በትኩረት መሥራት እንዳለበት ያመላከቱት ኢንጂነር ለሊሴ፣ በየወሩም በአካባቢ ጥበቃና በጤና ሚኒስቴር በሚመራ ኮሚቴ አፈፃፀሙ በትኩረት የሚገመገም መሆኑን አስገንዝበዋል።

ስምምነቱን የፈረሙት ተቋማት አመራሮችም፣ በቀጣይ ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በተቀናጀ መልኩ የአየር ብክለት ለመከላከልና ለመቆጣጠር ልዩ ትኩረት ሰጥተው እንደሚሠሩ አስታውቀዋል።

# አየር መንገዱ ወደ እሥራኤል የሚያደርገው በረራ የሀገራቱን የጠበቀ ግንኙነት የሚያሳይ እንደሆነ ተገለጸ

**ሊዩሌል ክፍሉ**



እየሩሳሌም፡- የኢትዮጵያ አየር መንገድ በሁኔታዎች ሳይገደብ ወደ እሥራኤል የሚያደርገው በረራ የሁለቱን ሀገራት የጠበቀ ግንኙነት የሚያሳይ መሆኑን የእሥራኤል ምክትል ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሸረን ሜሬየም ኸስኬል ገለጹ።

ምክትል ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሸረን ሜሬየም ኸስኬል ለጋዜጠኞች እንደገለጹት፣ በርካታ አየር መንገዶች ወደ እሥራኤል የሚያደርጉትን በረራ ባቋረጡበት ጊዜ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ወደ እሥራኤል የሚያደርገውን በረራ ባለማቋረጡ አመስግነዋል።

አየር መንገድ በሁኔታዎች ሳይገደብ ወደ እሥራኤል የሚያደርገው በረራ የሀገራቱን የጠበቀ ግንኙነትና ለጋራ ጥቅም አብሮ መሥራትን ያሳየ እንደሆነም አስታውቀዋል።

ኢትዮጵያና እሥራኤልን ለረጅም ጊዜ የቆየ ግንኙነት፣ የሕዝብ ለሕዝብ ትስስር እና የሚጋሯቸው ሃይማኖታዊ እሴቶች አሏቸው ያሉት ምክትል ውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ፣ ይህም የሁለቱን ሀገራት ግንኙነት የጠበቀ እንዲሆን ማስቻሉን ገልጸዋል።

በእሥራኤል የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የአፍሪካ ዲቪዥን ቢሮ ኃላፊ ኖአ ፉርማን በበኩላቸው፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ ፈተናዎችን ተቋቁሞ ወደ እሥራኤል የሚያደርገውን በረራ ለማስቀጠል ያሳየውን ቁርጠኝነት አድንቀዋል። ለዚህም የኢትዮጵያ መንግሥት ላደረገው ድጋፍ ምስጋና አቅርበዋል።

በሚኒስቴሩ የደቡብ አፍሪካ ሪጅን ዳይሬክተር በላይነሽ ዘቫዲያ፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ በኮቪድ-19 ወረርሽኝና እሥራኤል እየተፈተነች ባለችበት ወቅት ያልተቋረጠ አገልግሎት መስጠቱን አስታውሰው፣ በአስቸጋሪ ጊዜያትም ወደ እሥራኤል የሚያደርገውን በረራ ቀጥሏል፤ ይህም ለጠንካራ ግንኙነታችን ማሳያ ነው" ብለዋል።

ዳይሬክተሯ፤ የኢትዮጵያ አየር መንገድ የሁለትዮሽ ግንኙነትን በማጎልበት ረገድ ያለውን ወሳኝ ሚና ጠቅሰው፣ "ኢትዮጵያ ለእሥራኤል እውነተኛ ወዳጅ ነች" ሲሉ ገልጸዋል። አየር መንገዱ በአገልግሎቱ ያሳየውን ቁርጠኝነት በመግለጽ፣ ይህም በእሥራኤል መንግሥትና ሕዝብ የተመሰገነ እንደሆነ አስታውቀዋል።



ፎቶ - ገባቦ ገብሬ

# የቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ለጎብኚዎች ክፍት ሆነ

**ክብረአብ በላቸው**

አዲስ አበባ፡- የመንበረ ጸባኦት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ቅርስነቱን በጠበቀ መልኩ እድሳት ተደርጎለት ከትናንት ጀምሮ ለአገልግሎትና ለጎብኚዎች ክፍት እንደሆነ የካቴድራሉ አስተዳዳሪ ገለጹ።

የካቴድራሉ አስተዳደሪ ሊቀ ሥልጣናት ቆሞስ አባ ሲራክ አድማሱ እንደገለፁት፤ ካቴድራሉ እድሳት ሳይደረግለት ረጅም ጊዜ በመቆየቱ በውስጣዊና በውጫዊ የሕንፃው አካሉ ላይ የከፋ ጉዳት ደርሶበት ነበር።

ሕንፃው ከተጋረጠበት ጉዳት ለመታደግ ዕድሳት ማድረግ እንዳስፈለገ ያመለከቱት አስተዳዳሪው፤ ባለፉት 17 ወራት በምን መልኩ መታደስ እንደሚገባው ጥናት በማድረግ ወደ ሥራ ተገብቶ የዕድሳት ሥራውን በአሁኑ ጊዜ 95 በመቶ ማድረስ ተችሏል ብለዋል። ከትናንት ጀምሮ ለአገልግሎትና ለጎብኚዎች ክፍት መሆኑንም ጠቁመዋል።

እስካሁን የተካሄደው የዕድሳት ሥራ 773 ቀናት እንደወሰደ ጠቁመው፤ ዕድሳቱን ሙሉ በሙሉ ለማጠናቀቅ ተጨማሪ 225 ቀናት እንደሚያስፈልጉ አባ ሲራክ አስረድተዋል። ለዕድሳት ሥራው 172 ሚሊዮን 500 ሺህ ብር እንደሚፈጅ ገልጸው፤ እስከአሁን ለሥራ ተቋራጩ 124 ሚሊዮን 800 ሺህ ብር ክፍያ መፈጸሙን ተናግረዋል።

ይሁን እንጂ ለሥራ ተቋራጩ ያልተከፈለ 47 ሚሊዮን ብር ቀሪ ሂሳብ ስላለ ይህንን ክፍያ አጠናቆ ለመክፈል ታኅሣሥ 12 ቀን 2017 ዓ.ም በመላው ዓለም በተለያዩ የማኅበራዊ ሚዲያዎች በቀጥታ ስርጭት የገንዘብ መሰብሰብ ፕሮግራም እንደሚካሄድ ተገልጿል። በቀጥታ የገንዘብ ማሰባሰብ ፕሮግራሙ የቤተክርስቲያንቱ ምዕመናን ብሎም መላው ኢትዮጵያውያን የነቃ ተሳትፎ በማድረግ የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ ጥሪ ቀርቧል።

ካቴድራሉ በቤተ ክህነት ደረጃ በከፍተኛ የመሪነት ቦታ ላይ ሆነው ይመሩ የነበሩ እንዲሁም የኢትዮጵያን ዳር ድንበር ጠብቀው በነፃነት የምንኖርባት ነፃ ሀገር ያስረከቡን ጀግኖች አርበኞች፣ የጦር መኮንኖች መካነ እረፍት ሥፍራም እንደሆነ አመልክተዋል። ይህን ታሪካዊ ሥፍራ አድሶ እና አስጠብቆ ወደ ቀጣይ ትውልድ ማስተላለፍ የሁሉም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ኃላፊነት ነው ብለዋል።

የቅድስተ ሥላሴ ካቴድራል ከአክሱም ፅዮን ቀጥሎ ትልቅ መንፈሳዊ ሥፍራ መሆኑን ጠቅሰው፤ ካቴድራሉ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ብሎም የኢትዮጵያ ታሪካዊ ቅርስ መሆኑን ተናግረዋል።

ካቴድራሉን የማደስ ሥራ የሚከናወነው በቫርኒሮ ኮንስትራክሽን እንደሆነ በወቅቱ ተገልጿል።

# ‹‹መንግሥት የሽግግር ፍትሕን ለማስፈን በቁርጠኝነት እየሠራ ነው››

- ኤርሚያስ የማነ ብርሃን (ዶ/ር)
የፍትሕ ሚኒስትር ዴኤታ

**ማሕሌት አብዱል**



አዲስ አበባ፡- በሀገሪቱ በተለያዩ ዘመናት የተከሰቱ እና የቀጠሉ ችግሮችን ለማከም የሚያስችል የሽግግር ፍትሕን ለማስፈን መንግሥት በቁርጠኝነት እየሠራ መሆኑን የፍትሕ ሚኒስቴር ዴኤታ ኤርሚያስ የማነ ብርሃን (ዶክተር) አስታወቁ። የፍትሕ ዘርፉን ዘመናዊ፤ ቀልጣፋ እና የሕዝብ አመኔታን ያተረፈ እንዲሆን የተለያዩ የሪፎርም ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን አመለከቱ።

ሚኒስቴር ዴኤታው ከአዲስ ዘመን ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ እንዳስታወቁት፤ በሀገሪቱ በተለያዩ ዘመናት የተከሰቱ፣ የቀጠሉ፣ ተደራራቢ እና ሰፊ የተጎጂና የአጥፊ ወሰን ያላቸው የሰብዓዊ መብት ጥሰቶች፣ የእርስ በርስ ግጭቶች፣ ያልጠሩ ትርክቶች እና በደሎችን ለመፍታት የሚያስችል የሽግግር ፍትሕ ለማስፈን የተለያዩ ተግባራትን በማከናወን ላይ ይገኛል።

በእውነት፣ በእርቅ፣ በምሕረት እና በፍትሕ ላይ የተዋቀረ እና በግልፅ የሚመራ ሁለንተናዊ የሽግግር ፍትሕ ስልትን በተደራጀ፣ በተቀናጀ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለመተግበር ያስችል ዘንድ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሚያዚያ 9 ቀን 2016 ዓ.ም እንዲፀድቅ መደረጉንም ገልጸዋል።

ፖሊሲውንም ለማስፈፀም የሚያስችል ፍኖተ ካርታ መዘጋጀቱን የተናገሩት ኤርሚያስ የማነ ብርሃን (ዶ/ር)፤ በቀጣይም የሽግግር ፍትሕን ለማስፈፀም የሚያግዙ የባለድርሻ አካላት ሚናን የመለየት እና የሽግግር ፍትሕ ተቋማትን የማቋቋም ተግባራት እንደሚከናወኑ ጠቁመዋል።

ከዚሁ ጎን ጎን የሽግግር ፍትሕ ለማቋቋም የሚያስችሉ ሕጎችን የዘርፉ ባለሙያዎችን በማስተባበር ማውጣት መቻሉን የተናገሩት ሚኒስትር ዴኤታው፤ የሽግግር ፍትሕ ልዩ ችሎት ማቋቋሚያ ረቂቅ አዋጅ፣ የዓለም አቀፍ ጉልህ ወንጀሎች ረቂቅ አዋጅ፣ የሽግግር ፍትሕ ልዩ ዓቃቤ ሕግ ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ ረቂቅ አዋጅ፣ የእውነት አፈላላጊና የይቅርታ ኮሚሽን ማቋቋሚያ ረቂቅ አዋጅና የተቋምና የሕግ ሪፎርም ኮሚሽን ማቋቋሚያ ረቂቅ አዋጆች ዝግጅት መጠናቀቃቸውን አመልክተዋል።

ከሽግግር ፍትሑ ባሻገርም እንደሃገር የፍትሕ ዘርፉን ዘመናዊ፤ ቀልጣፋ እና የሕዝብ አመኔታን ያተረፈ እንዲሆን የተለያዩ የሪፎርም ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን የተናገሩት ኤርሚያስ የማነ ብርሃን (ዶ/ር)፤ የማሻሻያ ሥርዓቱ የዳኝነት ዘርፉን ለማሻሻል እና ተጠያቂነትን ለማስፈን እንደሚረዳ ገልጸዋል።

ሚኒስትር ዴኤታው እንዳብራሩት፤ ውጤታማ፣ ቀልጣፋ፣ ግልፅ፣ ወጪ ቆጣቢና አካታች የሆነ የፍትሕ ሥርዓት ለመፍጠር ሕግ ማውጣትና ተቋም መፍጠር ብቻ ሳይሆን አሠራሩን ዘመናዊ ማድረግ ይጠበቃል። ከዚህ አንፃር የፖሊሲ ተቋማትን ፤ ፍርድ ቤቶችንና ፍትሕ ሚኒስቴርን በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የማጠናከር ሥራዎች ተጀምረዋል።

በተለይም የዳኝነት ሥርዓቱ ነፃ እና ገለልተኛ እንዲሆን በርካታ ሥራዎች መሠራታቸውን ያስረዱት ሚኒስቴር ዴኤታው፤ በተለይም የዳኝነት አካሉ ከፖለቲካ ጣልቃ ገብነት የፀዳ እንዲሆን መደረጉን ተናግረዋል።

ከለውጡ በፊት ዳኞች የሚሾሙበት ሁኔታ በአብዛኛው በፖለቲካ ተፅዕኖ እንደነበር አውስተው፤ በሪፎርሙ የዳኞች ሹመት፣ ምልመላ፤ ዝውውር ሥርዓት ባለው መልኩ ለመምራት ይቻል ዘንድ በአዋጅ ደረጃ ፅድቆ ወደ ተግባር መገባቱን አስታውቀዋል።

ከሚኒስትር ዴኤታው ጋር የተደረገውን ቃለ ምልልስ ሙሉቃል በገጽ 6 ይመልከቱ

# ርዕሰ አንቀፅ

## የግብርናው ዘርፍ የስኬት ትርክቶች!

ከለውጡ ማግስት ጀምሮ ሁለንተናዊ ዕድገት በማምጣት ሀገራዊ ብልፅግናን እውን ለማድረግ ሰፋፊ ሥራዎች እየተከናወኑ ነው። የሀገሪቱን የኢኮኖሚ ዕድገት ቀጣይ እና አስተማማኝ ለማድረግ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ፖለሲ ተቀርጾ ተግባራዊ ከሆነ ውሎ አድሯል። በዚህም እየተመዘገበ ያለው ውጤት ተስፋ ሰጭ እንደሆነ በተጨባጭ እየተመለከትነው ነው።

ሀገር በቀል ፖሊሲው ግብርናን፣ ማዕድንን፣ ቱሪዝምን፣ ዲጂታል ትራንስፎርሜሽንን እና ኢንዱስትሪን ማዕከል ያደረገ፣ እነዚህን እምቅ አቅሞችን በማልማት የሀገርን ኢኮኖሚ ስትራቴጂክ በሆነ መንገድ ማሳደግን ታሳቢ ያደረገ ነው። በተለይም የግብርናውን ዘርፍ ካለበት ኋላቀርነት በማውጣት መዋቅራዊ ለውጥ ማምጣት እንደሚያስችል የታመነበት ነው።

እስካሁን ባለው ሁኔታ የግብርናው ዘርፍ በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ውስጥ ከፍ ያለ ስፍራ አለው፣ ከ80 ከመቶ በላይ የሚሆነው የሀገሪቱ አምራች ኃይል በዚሁ ዘርፍ የተሠማራ ነው፣ በሀገሪቱ ለግብርናው ዘርፍ አመቺ የሆነ የአየር ንብረት እና ሰፊ የሚታረስ መሬት አለ፣ በተለያዩ ወቅቶችም ግብርናን መሠረት ያደረጉ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ተግባራዊ ሆነዋል። ይህ ባለበት እና በሆነበት ሁኔታ፣ ዘርፉ የሚጠበቀውን ያህል ተጨባጭ ለውጥ ሳያመጣ ዘመናት ተቆጥረዋል ።

በዚህም ሀገሪቱ ዜጎቿን መመገብ የሚያስችል አቅም መፍጠር አቅቷት የምግብ እህል ከውጪ ጠባቂ እንድትሆን ተደርጋም ኖራለች። በተለያዩ ወቅቶች በተፈጠሩ የድርቅ አደጋዎች እጅግ ለከፋ የረሃብ አደጋ የተጋለጠችባቸው ሁኔታዎች ተፈጥረዋል። ክስተቶቹ የሀገሪቱን ገጽታ በማጠልሸት በዓለም አቀፍ ደረጃ የረሃብ መለያ እስከመሆን የደረሰችበት ትርክት ተፈጥሯል።

ይህንን ሀገራዊ እውነታ ለመለወጥ የለውጡ ኃይል ወደ ሥልጣን ከመጣ ማግስት ጀምሮ በምግብ እህል ራስን የመቻል ራዕይ አስቀምጦ ላለፉት ስድስት ዓመታት ሰፋፊ ሥራዎችን ሲያካሄድ ቆይቷል። በተለይም ዘርፉን ከነበረበት ሁለንተናዊ ኋላ ቀርነት ለማውጣት እና ለማዘመን ሰፊ ጥረቶች አድርጓል። በዚህም እንደ ሀገር እየተመዘገበ ያለው ስኬት ዓለም አቀፍ እውቅና የተቸረው ነው።

መንግሥት በፖሊሲ በተደገፈ መንገድ በአንድ በኩል አርሶ አደሩ ስለ ዘመናዊ ግብርና የተሻለ ግንዛቤ እንዲኖረው ለማስቻል፣ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን በመሥራት፣ በሌላ በኩል ዘርፉን ማዘመን የሚያስችሉ የቴክኖሎጂ ግብዓቶችን በተለያዩ አማራጮች በተጨባጭ በማቅረብ ሀገሪቱም ሆነ አርሶ አደሩ ከዘርፉ የተሻለ ተጠቃሚ እንዲሆን ረጅም ርቀት ተጉዟል።

ትራክተሮች፣ ኮምባይነሮች እና ሌሎች ዘርፉን ለማዘመን የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎች ከቀረጥ ነፃ የሚገቡበትን ሁኔታ ከማመቻቸት አንስቶ ለአርሶ አደሩ በነፃ እስከማቅረብ የተለያዩ ድጋፎችን በማቅረብ አርሶ አደሩ ለቴክኖሎጂ ቅርብ እንዲሆን ተንቀሳቅሷል።

የግብርና ባለሙያዎች ከመቼውን ጊዜ ይልቅ አርሶ አደሩን በቅርብ ሆነው እንዲያግዙት በማድረግ፣ የግብርና የምርምር ተቋማት ለዘርፉ የሚኖራቸውን ስትራቴጂክ ጠቀሜታ በኃላፊነት መወጣት የሚችሉበትን አስቻይ ሁኔታ በመፍጠር፣ የፖለቲካ አመራሩ ዘርፉን በማሳደግ ሂደት ያለውን የማይተካ ሚና በአግባቡ እንዲወጣ በማስቻል ሰፋፊ ሥራዎችን ሠርቷል።

በዘርፉ ምርት እና ምርታማነት ለማሳደግ የግብርና ግብዓቶችን በበቂ ሁኔታ እና በወቅቱ ለአርሶ አደሩ በማድረስ፣ አዳዲስ የእርሻ መሬቶችን ወደ ሥራ በማስገባት፣ የእርሻ ሥራ ባልተስፋፋባቸው አካባቢዎችን ግብርናን በማላመድ፤ አስቻጋሪ በሆኑ ወቅቶች ብዙ ዋጋ በመክፈል የግብርና ግብዓቶች ለአርሶ አደሩ በማቅረብ ስኬታማ ሥራዎችን አከናውነዋል።

ለዚህም በመላው ሀገሪቱ የተጀመሩ የበጋ ስንዴ እርሻ፣ በአፋር፣ በጋምቤላ እና በሌሎች ክልሎች የጤፍ ሰብል ለማምረት እየተደረጉ ያሉ ጥረቶች፤ ግጭት በነበረባቸው የአማራ ክልል የተለያዩ አካባቢዎች በእጀባ ጭምር ማዳበሪያ ለአርሶ አደሩ ለማድረስ የተደረጉ ጥረቶች እና የተገኙ ውጤቶች ተጠቃሽ ናቸው ።

የኩታ ገጠም አስተራረስን በመጠቀም እየተመዘገበ ያለ ምርታማነት፣ በሌማት ትሩፋት የተመጣጠነ ሀገራዊ የምግብ ሥርዓት ለመፍጠር እየተሠራ ያለው ሥራ በብዙ መልኩ የግብርናውን ዘርፍ በማዘመን ሀገር እና ሕዝብን ተጠቃሚ ለማድረግ የሚያስችል የስኬት ትርክት ነው።

በዚህም ሀገሪቱ በብዙ ሚሊዮን ዶላር ከውጭ ሲገባ የነበረውን ስንዴ አቁማ ወደላኪነት የተሸጋገረችበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ትርፍ ምርት በማምረትም ባለፉት አምስት ዓመታት ያጋጠሙንን አስቸጋሪ ሁኔታዎች ያለ ብዙ መንገጫገጭ ማለፍ የሚያስችል ተጨባጭ ተሞክሮ መፍጠር ችላለች።

አሁን ላይ በተለይም ለውጭ ገበያ የሚቀርቡ የግብርና ምርቶችን በብዛት እና በጥራት ለማቅረብ እየተደረገ ባለ ሀገራዊ ንቅናቄ ብዙ ስኬቶች እየተመዘገቡ ነው። በዘርፉ በታሪክ ተመዝግበው የማያውቁ የሽያጭ አኀዞች መስማት ከጀመርንም ውለን አድረናል። ለዚህም በስንዴ፣ በሩዝ እና በቡና እየተመዘገበ ያለው ስኬት ማሳያ ተደርጎ ሊወሰድ የሚችል ነው !

**አዲስ ዘመን**
ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et
**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን
**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፦ 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ
- አልማዝ አያሌው

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የግብርና ዘርፍ የታሪክ እጥፋት

ወጋሶ

ጊዜው የአዝመራ ስብሰባ ነው፤ በሃገራችን የተለያየ አቅጣጫ ለሚንቀሳቀስ ሰው፤ የደረሰ ምርት ሲታጨድ፣ ሲሰበሰብ፣ ሲከመር ወይ ደግሞ ሲወቃ ሊመለከት ይችላል። እንዲህ ማለቴ ሁሉም ቦታ ተመሳሳይ እንዳልሆነ ግንዛቤ ይያዝልኝ።

በየቦታው ሲዘናፈል የቆየው ምርት ግን ወደጎተራ የሚከተትበት ወቅት በመሆኑ በርከት ያለ ቦታ የሚያጭዱና የታጨደውን ወቅተው ምርቱን እዛው እጅ በእጅ ለአምራቹ የሚያስረክቡ ማሽኖች በየማሳው ሲርመሰመሱ መታየታቸው እውን ነው።

በእርግጥ የሚያጭዱና የሚወቁ ማሽኖች በየማሳው ተፍ ተፍ የማለታቸው ምስጢር በየአካባቢው ያለው አርሶ አደር ጤፉን፣ ስንዴውንም ሆነ ገብሱን በኩታ ገጠም ማረስ በመቻሉ ነው። ይህ የኩታ ገጠም የአስተራረስ ዘዴን ተግባራዊ ለማድረግ ግን ብዙ ተደክሞበታል።

**በእርግጥ የሚያጭዱና የሚወቁ ማሽኖች በየማሳው ተፍ ተፍ የማለታቸው ምስጢር በየአካባቢው ያለው አርሶ አደር ጤፉን፣ ስንዴውንም ሆነ ገብሱን በኩታ ገጠም ማረስ በመቻሉ ነው**

በቀበሌው ውስጥ ካለው የግብርና ባለሙያ ጀምሮ እስከ ፌዴራል ግብርና ሚኒስቴር ድረስ እንደ ቀላል የማይታይ ልፋትን ጠይቋል። ዛሬ አርሶ አደሩ ጥቅሙ ስለገባው በጋራ ማረስን ምርጫው አድርጓል። የአስተራረስ ዘዴው ተቀባይነት ስለ ማግኘቱም በርካታ ማሳያዎችን እንደ ማሳያ መጥቀስ ይቻላል።

ነገር ግን በጥቅሉ የግብርና ሚኒስቴር መረጃን ማየቱ ገላጭ ሆኖ አግኝቸዋለሁ። የሚኒስቴሩ መረጃ እንደሚያሳየውም፤ ዘንድሮ በመኸር ወቅት ከታረሰው ከ20 ነጥብ አራት ሚሊዮን ሔክታር መሬት 11 ነጥብ ስምንት ሚሊዮን ሔክታር መሬት የታረሰው በኩታ ገጠም ነው። ይህ አኀዝ ከቁጥር የዘለለ ነው።

ለረጅም ጊዜ በራሱ ምርጫና ፍላጎት የፈለገውን ሲዘራ የኖረን አርሶ አደር አሳምኖ ወደዚህ ውጤታማ ወደሆነው የአስተራረስ ዘዴ ማምጣት ብዙ ልፋትን ጠይቋል። በአሁኑ ወቅት የእርሻ ጊዜ ሆኖ የእርሻ ትራክተሮች እንደ አጫጆቹና መውቂያዎቹ ማሽኖች በየማሳው ባይርመሰመሱም በባለፈው የእርሻ ጊዜ በትራክተር የታረሰው መሬት ወደ አምስት ሚሊዮን ሔክታር ነበር ።

እንደእነዚህ አይነት ለውጦች ስንመለከት ግብርናችን እንደቀደመው ጊዜ ሁሉ በዝናብ ላይ ተንጠልጥሎ የመዳዙ ነገር እያበቃለት የመምጣቱ ነገር እውን እየሆነ ነው ማለት ይቻላል። ለዚህ ደግሞ በዋንኛነት የሚጠቀሰው መንግሥት ዘርፉን በብዙ መልኩ መደገፍ የሚያስችሉ ወሳኝ ርምጃዎችን መውሰዱ ነው።

በተለይም የተለያዩ ኢንሼቲቮችንና አዲስ የግብርና እና ገጠር ልማት ፖሊሲ መቅረጹ ብዙ ርቀት መሔድ አስችሏል። ይህ የመንግሥት ጥረት ግብርናውን ኮሜርሻላይዝድ በማድረግ እና በማዘመን ለኢንዱስትሪ ግብዓት እና ለወጪ ንግድ በቂ የሆነ ምርት እንዲመረት በመደረግ ላይ ይገኛል።

መንግሥት ተግባራዊ እደረገ ያለው የግብርና ፖሊሲ ሃገራችን በዘርፉ ያላትን ሃብት አሟጦ መጠቀም የሚያስችል ነው። የግብርናው ዘርፍ በዓለም አቀፍ ደረጃ የተደረሰበትን ሁኔታ ያገናዘበ፣ ምርታማነትን በጥራትም በብዛት የማስፋቱን አካሔድ የሰነቀ ነው። ከዚህም እልፍ ሲል መጪውን ዘመን መዋጀት የሚያስችለው ነው ለማለት ያስደፍራል።

ፖሊሲው፣ የአምራቹንም የአስመራቹንም ዓይን የሚገልጥ ነው። ባለፉት አምስት ዓመታት በግብርናው ዘርፍ የተገኘው ስኬት አስገራሚ ነው። መሬቱም ውሃውም የነበረ እና ያለ ነው፣ ይህ እንዴት ሆነ ብሎ መጠየቅ መልካም ነው።

አርሶ አደሮችም ቢሆኑ ምናልባት ከዓመት ዓመት ቁጥራቸው ይጨምር እንደሆን እንጂ እነርሱም ወትሮም የነበራቸውን መሬት ይዘው የቀጠሉ ናቸው። ታዲያ የተቀየረው ምንድን ከተባለ የተቀየረው አመለካከት ነው። ከአይቻልም ወደይቻላል መንፈስ መምጣት መቻል ነው።

ቀደም ሲል በሥራ ላይ የነበረው የገጠር ልማት ፖሊሲ፣ የግብርናን ምርታማነት እና ተወዳዳሪነትን ለማረጋገጥ ብሎም የገጠር መዋቅራዊ ሽግግር ለማሳካት እና ለአጠቃላይ የኢኮኖሚ እድገት ጉልህ ድርሻ እንዲያበረክት በመታሰቡ በአዲሱ ፖሊሲ ሊተካ ችሏል።

ነባሩ ፖሊሲ በአዲስ መተካት ካስፈለጉ ነገሮች ውስጥ አንዱ፣ ቀደም ሲል ሃገራችን ትከተለው የነበረው የግብርና መር የልማት ፖሊሲ ወደ ብዝኃ ዘርፍ የልማት ፖሊሲ አቅጣጫ በመቀየሩ ነው። ሌላው ደግሞ ገበያን መሠረት ያደረገ የግብርና ምርት አቅርቦትን በማስፋትና ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ በዓለም ደረጃ ተወዳዳሪነትን ከፍ ለማድረግ ነው።

በተለይም ከዘርፉ ተለዋዋጭ ባሕሪያት ጋር የሚመጡ ለውጦችን ለማስተናገድ እንዲሁም የዘርፉን መልካም አጋጣሚዎችና የመልማት አቅም በስፋት በመጠቀም የዘርፉን ምርትና ምርታማነት ማረጋገጥ ከብዙዎቹ መካከል የሚጠቀሱ ናቸው።

በርግጥ አሁን ላይ የግብርናው ዘርፍ በርካታ ስኬቶችን በማስመዝገብ ላይ ነው መሆኑ የአደባባይ ምስጢር ነው፤ ለምሳሌ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) አነሳሽነት ወደትግበራ የገባውን የስንዴ ኢንሼቲቭ መጥቀስ ይቻላል። ይህ የስንዴ ኢንሼቲቭ በአሁኑ ወቅት አስገራሚ ውጤት እያስመዘገበ መሆኑ ይታወቃል።

የስንዴ ውጤት ብቻ ሲስተዋል አምና በ2016 ላይ 230 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ማምረት ተችሏል። ከዚህ አኳያ ስንዴ ኤክስፖርት ማድረግም ተጀምሯል። በዚህ ውስጥ አይነተኛ ሚና የተጫወተው ደግሞ የመስኖ ስንዴ እንደሆነ ግልጽ ነው።

ለንጽጽር ያመች ዘንድ ከአራት ዓመት በፊት በመስኖ የተመረተው ስንዴ 700 ሺ ኩንታል አካባቢ ብቻ እንደነበር መረዳቱ በቂ ነው። የአምና የ2016 በጀት ዓመት ሲታይ ደግሞ ከሦስት ሚሊዮን ሔክታር መሬት ላይ 107 ሚሊዮን ኩንታል ማግኘት መቻሉን የፕላንና ልማት ሚኒስቴር ከአንድ ወር በፊት ካወጣው መረጃ መረዳት ይቻላል።

መንግሥት በወሰደው ከፍተኛ ውሳኔ ለዓይን የሚያጠግብ ለውጥ መታየት መጀመሩን አለመመስከር ደግሞ ንፉግነት ነው። በእርግጥ ትናንት "እነዚህንና እነዚያን እቅዶች ከሕዝብ ጋር ሆኜ እተገብራቸዋለሁ" ብሎ እቅዱን ይፋ ሲያደርግ፤ ብዙዎች "የማይተገበሩ እቅዶች ይፋ እየሆኑ ነው" በማለት ዳር ቆመው እቅዱን እንደቅዠት ሲቆጥሩ እንደነበር ይታወሳል።

ይሁንና መንግሥት የእነርሱን ይሁንታ በመፈለግ ጊዜ የሚያጠፋበት ምንም ምክንያት ስለሌለው ወደተግባር ገብቶ በስንዴ ኢንሼቲቭም ሆነ በሌላው መስክ ትልቅ ታሪክ መሥራት ችሏል። እውነታው ሀገሪቱ በግብርናው ዘርፍ አዲስ ታሪክ እያስመዘገበች ስለመሆኑ ተጨባጭ ማሳያ ነው።

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ እንግዳ

## ‹‹ዳኞች ነፃነት ላይ አትኩረው ተጠያቂነትን በመተው እንዳሻቸው የሚሆኑበት ስርዓት አይቀጥልም››

- ኤርሚያስ የማነ ብርሃን (ዶ/ር)
የፍትሕ ሚኒስትር ዴኤታ

ማህሌት አብዱል

**ከለውጡ ማግስት ጀምሮ በፍትሕ ሥርዓቱ ዘርፈ ብዙ ውጤታማ የማሻሻያ ሥራዎች ሲከናወኑ ቆይተዋል፤ እየተከናወኑም ይገኛሉ፡፡ በተለይም የሕዝቡን የፍትህ ጥማት እና የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥ የተጀመሩ የሪፎርም ሥራዎች ውጤታማ እንዲሆኑ ሰፊ ጥረቶች እየተደረጉ ነው፡፡**

**በ ሚኒስቴሩ የሪፎርም ሥራዎች ዙሪያ ከፍትሕ ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር ኤርሚያስ የማነ ብርሃን ጋር ቆይታ አድርገናል፡፡ እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡**



**አዲስ ዘመን፡- በቅድሚያ በሃገር አቀፍ ደረጃ በፍትሕ ስርዓቱ ላይ ሪፎርም ማድረግ ያስፈለገበትን አብይ ምክንያትና ሪፎርሙ ያካተታቸውን ዋና ዋና ማሕቀፎች ቢያብራሩልን ?**

**ኤርሚያስ ዶ/ር፡-** እንደሚታወቀው ለለውጡ ገፊ ከነበሩ ሃገራዊ ችግሮች መካከል በፍትሕ ዘርፉ በተለይም በዳኝነት አካላት ላይ ይነሱ የነበሩ የሕዝብ እሮሮና ምሬቶች ዋነኞቹ ናቸው። እሮሮና ምሬቶቹ ያስነሳቸው ሕዝባዊ ተቋውሞዎች ለዓመታት ሲንከባለሉ የቆዩ፤ የተወዘፉ ችግሮች ነበሩ።

በዘርፉ የፍትሕ ማጣት፣ የፍትህ ጉድለት፣ የዳኝነት በደል፣ የሰብአዊ መብት ጥሰት፣ አፋኝ፣ ጨቋኝ፣ አሳሪ ሕጎች፤ የፍትህ ስርዓቱ ፖለቲካዊ አድሎ ያለበት መሆኑ እነዚህና መሰል ጉዳዮች ናቸው ሕዝቡን ገፋፍተው ጎዳና እንዲወጣ፣ መንግሥትን እንዲቃወም፣ ሁለትና ሶስት ጊዜ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እንዲታወጅ ያደረጉት። በተለይም ፍትሕ ይስፈንልን፤ የዳኝነት በደልን ይቁምልን የሚል ጥያቄ በሕዝቡ በስፋት ይነሳ ነበር።

በለውጡ ማግስት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በምክር ቤት ንግግራቸው ከገለጿቸው ጉዳዮች መካከል ዋነኛው የፍትሕ ስርዓቱን ስርነቀል በሆነ መልኩ መለወጥ ያስፈልጋል የሚለው ተጠቃሽ ነው። ሕዝብን መሰረት ያደረገና የሕዝብን ጥያቄ የሚመልስ የሕግ የበላይነት፤ ፍትሕን፣ የዳኝነት ነፃነትን እንመልሳለን በሚል በግልፅ የገቡት ቃል ነበር። በዚያ መሰረት ነው በፍትሕ ዘርፉ የሪፎርም ሥራ የተጀመረው።

ሪፎርሙ መተግበር ከተጀመረ ወዲህ ያመጣውን ለውጥ በሚመለከት በሁለት ከፍለን ማየት ይኖርብናል። አንደኛው ከ2010 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2014 ዓ.ም ድረስ የተሰሩ ሥራዎች ናቸው። በተለይ ሃገራዊ ምርጫ ከመደረጉ በፊት የተከናወኑ ሥራዎችን ማየት ተገቢ ነው። በነዚህ ጊዜያት በሃገር አቀፍ ደረጃ የፍትሕ እና የዳኝነት ማሻሻያ ሪፎርሞችን ጀምረናል።

የሕግ የበላይነት፣ የዳኝነት ነፃነት፣ የሰብአዊ መብት መከበር የመሳሰሉት ላይ የመጡ ለውጦች ምን ይመስላሉ? ውስንነታቸውስ ምንድን ነው? የሚለውን በአግባቡ በመንግሥትም፣ በአጋር አካላትና በሕዝብም ተገምግሞ መልካም ነገሮችን ይዘን፣ ክፍተቶችን ለይተን ወሳኝ የሆኑ መሰረታዊ ለውጦችን ሊያመጡ የሚችሉ ጉዳዮችን በመለየት አዲስና የሶስት ዓመት የፍትሕ ዘርፍ ትራንስፎርሜሽን ፍኖተ-ካርታ ተዘጋጅቶ ወደ ሥራ ከተገባ አንድ ዓመት ተኩል ሆኖታል።

በእነዚህ ዓመታት ከሕግ፣ ከአሰራር፣ ከተቋም አንፃር በርካታ ለውጦችን ማስመዝገብ ችለናል። አፋኝ፣ ጨቋኝና አሳሪ የነበሩ ሕጎች፤ ሁልጊዜ ኢትዮጵያ በዓለም አደባባይ ስትነሳ አብረው ከሚጠቀሱ ችግሮች መካከል አንዱ የሆነው የሲቪል ማኅበረሰብ ማቋቋሚያ አዋጅ፣ የፕሬስ ሕግ፣ የምርጫ ቦርድ ሕግ፣ የፀረ ሽብር አዋጅንና ሌሎችንም ሕጎችን የማሻሻል ሥራ ተሰርቷል።

በተጨማሪም ከፖሊሲ፣ ከምርመራ፣ ከደህንነት ተቋማት ጋር የተያይዞ የነበሩ አሰራሮች፣ ሲጠቀሙበት የነበሩት ሕጎችና አካሄድንም የማረቅ ሥራ በስፋት ተከናውኗል። በተለይም በፖለቲካ አመለካከታቸው የታሰሩ በቡዙ ሺ የሚቆጠሩ እስረኞች እንዲፈቱ የማድረግ ሥራም ተሰርቷል። እነዚህ ሁሉ በፍትሕ ሪፎርሙ ፓኬጅ ውስጥ የሚታዩ ናቸው። የዲሞክራሲ የሰብአዊ መብትና የሕግ የበላይነትን ጥያቄዎችን ለመመለስ መንግሥት የሄደባቸው ርቀቶች ናቸው። ይህንን ሲያደርግም ከፍተኛ ዋጋ ከፍሎ ጭምር ነው።

ጫካም ሆነ ውጭ የነበሩት ኃይሎች በአንድ ጊዜ መጥተው በኢትዮጵያ የፖለቲካ ለውጥ ሂደት ውስጥ እንዲሳተፉ እድል የተሰጣቸው ፍትሕና የሕግ የበላይ እንዲሰፍን በማለም ነው። እንደምናውቀው የተለያዩ ኮሚሽኖችን በማቋቋም ብሔራዊ መግባባት፣ ይቅርታን፣ የድንበርና የማንነት ጥያቄዎችን ለመፍታት ሥራዎች ተሰርተዋል። የቡድን መብትን ከማስከበር አንፃር ደግሞ የሕዝቦችን የራስን እድል በራስ የመወሰን ሕገ-መንግስታዊ መብት ጋር የተያያዙ የክልሎች ጥያቄ በተጨባጭ እንዲመለሱ ጥረት ተደርጓል።

እነዚህ ለውጦች በተጨባጭ ሕዝቡ ከሚፈልገው የለውጥ ውጤት አንፃር የሕዝቡን ፍላጎት አርክተዋል ወይ? የሕዝቡን ምሬት ቀንሰዋል ወይ ? የሚለውን ነገር ለማየት ያስቻለን ዘንድ ጥናት አስጠንተናል። በዳኝነት፤ በፍትሕ አካሉ፣ በፖሊሲና በሌሎችም አካላት የሚሰሩ ሥራዎች፤ የሚወጡ ሕጎች፣ የተቋሞች አደረጃጀትና አሰራሮች ምንይመስላሉ የሚለውን በማጤን፤ ሁኔታዎቹን ለመቀየር ሰፊ ሥራዎች ተሰርተዋል፤ አበረታች ውጤቶችን ማምጣት ችለናል።

ይህም ሆኖ አሁንም ቢሆን የሕብረተሰቡን እሮሮ፣ ምሬትና ቅሬታ ከመቀነስ አንፃር ብዙ የሚቀረን መሆኑን ተረድተናል። ጥራት ያለው፣ ፈጣን፣ ቀልጣፋ፣ ወጪ ቆጣቢ፣ ሁሉን ያካተተ ግልፅ የሆነ የፍትሕ አገልግሎት መስጠት ላይ አሁንም ከፍተኛ ክፍተት አለብን።

ክፍተቶችን ታሳቢ በመድረግ፣ ሁሉን አቀፍ በሆነ መንገድ፤ የተገኙ መልካም ውጤቶችን፣ ሕገመንግሥቱን እና የሃገረ-መንግሥት ግንባታን መሰረት ባደረገ መልኩ፣ አካታች፣ ሁሉን አቀፍ፣ ከክልሎች ጋር አብሮ የሚሰራ የሶስት ዓመት የፍትሕ ትራንስፎርሜሽን ቀርፀናል።

ለዚህም ፍትሕ ሚኒስቴር፣ የዳኝነት አካሉ፣ የፌደራል የፍትሕና የሕግ ማሰልጠኛ ተቋም ከሄግ ኢንስቲትዩት ፎር ሎው ከሚባል ተቋም ጋር በመሆን የዳሰሳ ጥናት አካሄደዋል። ጥናቱ የሕዝባችንን ምሬትና ቅሬታ ለመፍታት ከተለመደውና ከቃላት ጨዋታ ውጪ ከተገልጋዩ ናሙና ተወስዶ የተሰራ ነው።

የሶስት ዓመቱ የትራንስፎርሜሽን እቅዱ ከሐምሌ 1/2016 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2018 ዓ.ም የሚተገበር ነው። ወሳኝና ሁሉን አቀፍ ርብርብ የምናደርግበት ፍኖተ ካርታም ወጥቶለታል። ይህ ፍኖተ- ካርታ አስር አምዶች ያሉት ነው፤ በፊት የነበሩ ለውጦችን መሰረት ያደረጉ፤ የሚነሱ ችግሮችን ሊቀንሱ የሚችሉና ተጨባጭ ለውጥ ሊያመጡ እንደሚችሉ ታምኖባቸው የተቀረፁ ናቸው።

ከእነዚህም አምዶች መካከል የመሰረተ -ማኅበረሰብ ፍትሕን እናስፋፋለን የሚል ነው። ፍትህ መነሻውንም ሆነ መድረሻውን ዋና ግቡ ማድረግ ያለበት ሕብረተሰቡን ስለሆነ የማኅበረሰብ ፍትህን የማጠናከር ሥራ ትኩረት ተሰጥቶታል። ይህም ሲባል አደረጃጀት፣ ተቋም ላይ ሳይሆን በዋነኛነት የሕብረተሰቡ ፍትህን ለማግኘት የሚያስችለውን፤ የሚጠቀምበትን ውጤታማ አካሄድ በመለየት፤ እሱን ጥቅም ላይ የማዋል አስተሳሰብ ነው።

ይህም ሲባል ከመደበኛ የፍትሕ ስርዓት ውጪ ማኅበረሰቡ ለረጅም ጊዜ ሲጠቀምበት ውጤታማ የሆነ፣ የዳበረ፣ ተዓማኒነት ያለው የባሕላዊ የግጭት መፍቺያ ስርዓት የመጠቀም ባህሉ እንዲጎለብት የማገዝ ሥራ ነው። እንደሚታወቀው ከመደበኛው ፍርድ ቤት ውጪ 80 በመቶ የሚሆኑ ጉዳዮች ረጅም ጊዜ ባዳበሩ የባሕላዊ ፍርድ ስርዓት የሚዳኙ ናቸው።

> **የፍትሕ ሪፎርሙ ከሃገረ-መንግሥት ቀጣይነት፤ ከልማት፤ ከሕዝቦች አብሮ መኖር ፤ መዋቅራዊ በደል እንዳይኖር ከማድረግ አንፃር የሚሰራ ሥራ ነው**

አክስፎርድ የባሕላዊ የዳኝነት ስርዓትን በሚመለከት በሁሉም ክልሎች የዳሰሳ ጥናት አካሂዷል። አብዛኛው በሚባል ደረጃ ባሕላዊ ፍርድ ቤቶችን መጠቀምን እንደሚመርጡ ተናግረዋል፤ ለዚህም እንደምክንያት ያነሱት ከጊዜና ከቅልጥፍና ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ነው። አጠቃላይ በመሬት ላይ ያለው እውነታም የሚያሳየው እሱኑ ነው።

ከዚህ አንፃር የማኅበረሰብ ፍትህን በሶስት ዓመት ውስጥ ቢያንስ በተቋም ደረጃ እውቅና እንዲሰጠው የማድረግ፤ የመደገፍ፣ ሞዴል ባሕላዊ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቀርፆ ክልሎች እንዲመሩት እስከማድረግ የሚዘልቁ ሥራዎች ሰርተናል።

በአጠቃላይ ፍኖተ ካርታው በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ታምኖበት፣ በአፈ ጉባኤው በሚመራ አደረጃጀት አብይ ኮሚቴ፣ ቴክኒክ ኮሚቴ የዳኝነት ነፃነቱን በጠበቀ ደህንነት፤ የፍትህ አካላት፣ ፖሊስ፣ አቃቤ ሕግ፣ ማረሚያ ቤቶች እንዳሉ ሆኖ አጠቃላይ በሕዝብ ተወካዮች ፀድቆ እየተተገበረ ነው። በክልሎች ደግሞ በተመሳሳይ አደረጃጀት በሕግ አውጪው ምክር ቤት አፈጉባኤ አማካኝነት ሌሎችም አባል ሆነውበት እንዲደራጁ እየተደረገ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ሪፎርሙ በተለይም የዳኝነት ስርዓቱን በማሻሻልና ፍትሕ እንዲከበር ከማድረግ አኳያ ምንአይነት ሚና ይኖረዋል?**

**ኤርሚያስ ዶ/ር፡-** የፍትሕ አካላት እምነት እንዲጣልባቸው የሙያ ብቃት እና ስነምግባር ሊኖራቸው ይገባል። ከዚህ ቀደም በቂ የሙያ ብቃት ፣ ስነምግባር የሌለው፤ ከሕጋዊ ገቢው በላይ ከፍተኛ ሃብት ያፈራ በፍትሕ፤ በዳኝነት፣ በፖሊስና በአቃቤ ሕግ በአጠቃላይ ለስርዓቱ አሉታዊ ምስልን የሚፈጥር፤ ሕዝቡ በስርዓቱ ላይ አመኔታ እንዳይኖረው የሚያደርግ፣ ለሮሮውም ለምሬቱም፤ ለተስፋ ማጣቱም በአንድም በሌላ መልኩ አስተዋፅኦ ያደረገበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር። እነዚህን ችግሮች የማጥራት ሥርዓት ያስፈልጋል የሚለው ሃሳብ በእቅዱ ጎልተው ከተካተቱ ጉዳዮች ዋነኛው ነው።

ውጤታማ፣ ቀልጣፋ፣ ግልፅ፣ ወጪ ቆጣቢና አካታች የሆነ ስርዓት ለመፍጠር ሕግ ማውጣትና ተቋም መፍጠር ብቻ ሳይሆን አሰራሩን ዘመናዊ ማድረግ ይጠበቃል። ከዚህ አንፃር የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን በደንብ መጠቀም ያስፈልጋል። በዚህ ረገድ በፖሊሲ፤ ፍርድ ቤቶችና በፍትህ ሚኒስቴር የሚታዩ ለውጦች አሉ። እነዚህ ሥራዎች የሶስት ዓመት ፍኖተ ካርታው አካል ናቸው። በአጠቃላይ በፍትህ ውጤታማ የሆነ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ለመዘርጋት ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ ነው።

ሌላው የፍትሕ ብሔር፣ የአስተዳደር ሕግና የወንጀል ፍትህን በአዲስ እይታ መታየት የሚለው ጉዳይ ነው። ያመጣናቸው ለውጦች የበለጠ ጠቃሚ እንዲሆኑ፤ የሕዝቡን ምሬት እንዲቀንሱ ማድረግ ያስፈልጋል። ምክንያቱንም ምንም ያህል ብናሻሽልም በሚፈለገው ደረጃ ምሬቱን ቀንሰናል ብለን አናምንም። ለዚህም ነው የትራንስፎርሜሽን እቅድ ማዘጋጀት ያስፈለገን።

አብዛኛው ማኅበረሰብ የእለት ተእለት ኑሮውን ሲከውን ከአስተዳደር አካላት ጋር ይገናኛል። አስተዳዳሪዎች የሚሰሩበት ሕግ፣ አሰራራቸው፣ የሚሰጡት ውሳኔዎች (ከፍርድ ቤት መለስ) ምን ይመስላሉ? ግልፅ ነው ወይ? ተጠያቂነት አለው ወይ? መመሪያ ሲወጣ የሚመለከታቸውን አካላት በማካተት ውይይት ይደረግበታል ወይ? የሚሉትንም ነገሮች ለመዳሰስ ተሞክሮሯል።

ከዚህ ቀደም በነበረው አካሄድ መመሪያ ከወጣ በኋላ አንዱ ኃላፊ መሳቢያ ውስጥ ተቆልፎ ‹‹መመሪያው እንዲህ ይላል›› ነው የሚባለው፤ መመሪያ ስጡ ሲባልም ለመስጠት ፈቃደኛ አይሆኑም። አዋጅ 1183/2012

**ወደ ገጽ 7 ዞሯል**

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ እንግዳ

# ‹‹ዳኞች ነፃነት ላይ አትኩረው...

ከገጽ 6 የዞረ

የወጣውም ለዚህ ነው። ከዚህ የበለጠ ደግሞ ማጠናከር ያስፈልጋል በሚል ነው፤ ፍኖተ ካርታው የተዘጋጀው። ይህ አዋጅ ከወጣ በኋላ ተፈፃሚነቱ በፌዴራል ደረጃ ነበር፤ በአዲስ እይታ ብለን አጠቃላይ በክልሎችም እንዲወጣ አድርገናል። በአንድ ዓመት ተኩል ውስጥ ስድስት ክልሎች አውጥተዋል። አሁን ትላልቁ ክልሎች እንዲያወጡም ይጠበቃል።

ይህም አስተዳደር ፍትሕ ለኅብረተሰቡ ለመስጠት የሚያስችል ነው። ሆኖም መመሪያ ሲወጣ ከሕዝብ ጋር መወያየት ያስፈልጋል። የሚወጡ መመሪያዎች ከብሔራዊ ደህንነት ጋር የተያያዙ እስካልሆኑ ድረስ ተጠያቂነት የሰፈነበት መሆን አለበት። ሕገመንግሥቱ አንቀፅ 12 ላይ የመንግስት አሰራር ግልፅና ተጠያቂነት ሊኖረው እንደሚገባ ይደነግጋል። ደግሞም በአንድ ዴሞክራሲያዊ ማኅበረሰብ ለመገንባት እና ሃሳቦች በግልፅ ተወያይተው ሲወጡ ነው ውጤታማ መሆን የሚቻለው። ዝም ብሎ እኔ አውቅልሃለሁ በሚል አሰራር፣ አዋቂ ነን የሚሉ ካድሬዎች ወይም ኃላፊዎች ብቻ ተሰብስበው የሚሰጡት የውሳኔ አካሄድ የትም አላደረሰንም።

ለውጡም ያስፈለገበት አንዱ ምክንያት ይሄ ነው። ይህንን እውን ለማድረግ ነው ክልሎች የአስተዳደር አዋጅ እንዲያወጡ የተደረገው። በቅርቡ ኦሮሚያና አማራ ክልሎች አዋጁን ለማውጣት ዝግጅት እያደረጉ ነው፤ ይህም የትራንስፎርሜሽኑ አካል ነው። በጥቅሉ በግልፅና በተጨባጭ ሁኔታ አዋጁን አውጥቶ በሕጉ መሰረት እንዲተገበር ለሕዝቡ የተሻለ እድል የሚሰጥ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- አንዳንድ የሕግ ባለሙያዎች አዋጅ በራሱ አወዛጋቢ ሃሳቦችን የያዘና ለአፈፃፀምም አስቸጋሪ እንደሆነ ያነሳሉ፤ እርሶ በዚህ ላይ የሚሰጡት ምላሽ ምንድን ነው?**

**ኤርሚያስ ዶ/ር፡-** እንደተባለው አሻሚና አከራካሪ የሆኑት ነገሮች በዚህ አዋጅ ላይ ከአምስት በመቶ አይበልጥም። ከአዋጁ 95 በመቶ የሚሆኑ አንቀፆች በአግባቡ ቢተገበሩ ከአስተዳደር ፍትህ መጓደል ተያይዞ የሚነሱ ችግሮችን ይፈታል ተብሎ የታመነባቸው ናቸው።

እርግጥ ነው በንድፈ ሃሳብ ደረጃ የሚወጣ አዋጅ ፍፁምና ምሉዕ ሊሆን አይችልም። መሬት ላይ ተግባራዊ ሲሆንም የራሱ የሆነ ተግዳሮት ሊያጋጥመው፤ አዳዲስ ነባራዊ ሁኔታዎችንም ከግምት ውስጥ ላያስገባ ይችላል። ከአፈፃፀም፤ ከምዝገባ፤ ከሚጠበቁት ነገሮች፤ ከአጠቃላይ የፍርድ አፈፃፀም አኳያ ሊኖሩ የሚችሉ ክፍተቶች ሊኖሩ ይችላሉ። እነሱንም ለይተናቸዋል፤ በቅርብ የሚሻሻሉ ናቸው።

ግን አስረግጬ መናገር የምፈልገው አንዲቷን ጉድፍ ከመለየት ባሻገር ያለውን እንኳን በአግባቡ ብንተገብረው ከመንግሥት ተጠያቂነት ከማረጋገጥ ጋር ተያይዞ በሕዝብ የሚነሱ ቅሬታዎችን ይፈታል።

ለምሳሌ ከዚህ ቀደም አንድ መመሪያ አንድ ኃላፊ እንደፈለገ ያወጣ ነበር፤ አሁን ግን መመሪያ ከማውጣቱ በፊት የሚመለከታቸውን አካላት በማወያየት ሕዝቡ አስተያየት እንዲሰጥበት መደረጉ በራሱ ትልቅ ነገር ነው። መመሪያ ከመውጣቱ በፊት ሰዎች እንዲከራከሩበት እድል ይሰጣል።

የሚወጣው መመሪያ የሕዝብን ፍላጎት ያንፀባረቀ እና ተፈትሾ ያለፈ መሆን አለበት። ይህ በመሰረታዊነት የሕግ አውጪውንም ቅቡልነት የሚጨምር ነው። በተጨማሪም ይህንን ሂደት ሳያልፍ የሚወጣ መመሪያ ተቀባይነት የለውም ሲል የመሟገት እድልን ይፈጥራል። ግለፀኝነትንም ይፈጥራል።

በአጠቃላይ አዋጁ ችግሮች የሉበትም ማለት ባይሆንም ከዚህ ጋር ተያይዞ ይነሱ የነበሩ ቅሬታዎችን ለመፍታት ግን ያግዛል። አሁን ስድስት ክልሎች ሲያወጡ ከፌደራል ተሞክሮ ወስደው ማሻሻያ አድርገው እንዲያወጡ ያደርጋል። በሌላ በኩል ከፍትሕ ተቋማት ውጪ ይሰጡ የነበሩ ዳኝነቶችን ወጥ በሆነ መልኩ ለመምራትና መልክ ለማስያዝ ያስችላል።

ደረጃውን በጠበቀ የሕጋዊነት መርህ፤ የመደመጥ መርህን፤ የመንግሥትን ወጪ በሚቆጥብ፤ ፍትሐዊ ውሳኔ ለመስጠት ያስችላል። ሁልጊዜም ቢሆንም አስተዳደራዊ ሲባል ከፍጥነት ከቅልጥፍና ጋር



የሚያያዘው ነው። በመሆኑም ከፊል የዳኝነት ውሳኔ የሚሰጡ አካላትን ተቀራራቢ በሆነ አደረጃጀት፤ አሰራርና የሚያቀራርብ ስርዓት ለመዘርጋት ያስችላል። በቀጣዮቹ የትራንስፎርሜሽን ዓመታት የወንጀል ስነስርዓት ሕጉና የማስረጃ ሕጉ አዳዲስ ማሻሻያዎች ይዞ የሚመጣ ይሆናል። የፍትሐ ብሔር ፖሊሲያችንን ለማውጣት ጥናት እየተደረገ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ፍኖተ ካርታው ለማከናወን ከለያቸው ጉዳዮች አንዱ የክልሎችንና የፌደራል መንግስቱን ግንኙነት በሚመለከት ነው፤ እስቲ ስለዚህ ጉዳይ ምንነት ያብራሩልን?**

**ኤርሚያስ ዶ/ር፡-** ኢትዮጵያ የፌዴራል ስርዓት የምትከተል ሃገር እንደመሆንዋ ውጤታማ የጎንዮሽና የተዋረድ ግንኙነት ያስፈልጋል። ለዚህም የክልልና የፌዴራል መንግሥት ግንኙነት የሚወስን አዋጅ ወጥቷል። በመንግስት ትኩረት ከተሰጠው የሶስት ዓመት የፍትህ ማሻሻያ መርሃ-ግብር ለሕብረተሰቡ ወሳኝ ሚና ይጫወታል ካልናቸው ጉዳዮች አንዱ ውጤታማ የሆነ የጎንዮሽና የተዋረድ ግኙኝነትን እንዲጠናከር በመደረጉ ለመጀመሪያ ጊዜ ሃገር አቀፍ የወንጀል ሪፖርት ማቅረብ ችለናል። ድሮ የአዲስ አበባን ብቻ ነበር የምናቀርበው። በመሆኑም ከተደራሽነት አንፃርም ሆነ ውጤታማ ግንኙነት በመፍጠር ረገድ አበረታች ሥራ ተሰርቷል።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የማኅበረሰብ ባሕላዊ ማቋቋሚያ አዋጅ በመውጣቱ እንደ ኦሮሚያ ያሉ ክልሎች ቀድመው አዋጅ በመዘጋጀትና አደረጃጀቱንም በሺዎች በሚቆጠሩ ቀበሌዎች በማውረድ ከ300 ሺ እስከ 400 ሺ ጉዳዮችን በዓመት የሚያዩበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ይህ ሊሳካ የቻለው ውጤታማ የጎንዮሽና የተዋረድ ግኑኘትን የሚወስነው አዋጅ ተግባራዊ በመደረጉ ነው። በአጠቃላይ በድምር ውጤቱ የኅብረተሰቡን ምሬት ይቀንሳል የሚል እምነት አለ። በቀረው አንድ ዓመት ተኩል ጊዜ ውስጥ ባቀድነው መሰረት ለመጓዝ ከክልሎች ጋር እየተናበብን እንሰራለን።

**አዲስ ዘመን፡- ከባሕላዊ ፍርድ ቤቶች ጋር ተያይዞ በተለይ ከሰብአዊ መብት አያያዝና የሴቶችን እኩልነትን ማረጋገጥ ረገድ ክፍተቶች እንዳሉባቸው ይነሳል። እንዲህ አይነት የፍትህ ጥሰቶችን በምን መልኩ ነው የምትከታተሉት?**

**ኤርሚያስ ዶ/ር፡-** በነገራችን ላይ ባሕላዊ የዳኝነት ስርዓቱ አሁን ላይ በመንግሥት ደረጃ እውቅና ተሰጥቶ ድጋፍ የሚደረግለት ቢሆንም ሕብረተሰቡ ለረጅም ጊዜ ሲጠቀምበት የኖረ ነው። በመሰረቱ አንድ ባሕል ችግሮችን የሚፈታበትን ዘዴ መንግሥት ሊቀይስለትና በይዘቱ ላይ ሊወስን አይችልም። ይህ ከሆነ ባህሉን እኛ ልንቀርፅለት ነው ማለት ነው። ከዚያ ይልቅ ከመርህ፤ ከአካታችነት፣ ከእኩልነት፣ ከሕግ የበላይነት አንፃር የሚኖሩ ግድፈቶችን፤ ውስንነቶችን እንዴት መፍታት ይቻላል? በሚለው ላይ ነው ትኩረት የምናደርገው።

ለምሳሌ የሴቶች እኩልነትን ለማረጋገጥ ሴቶች በባህላዊ ዳኝነቱም ሆነ በሌሎች ማሕበራዊ ኃላፊነቶች ላይ እንዲሳተፉ የማድረግ፤ የመደመጥ መብታቸው እንዳይጣስ ተደርጎ ነው ሞዴል ሕጉ የተቀረፀው። ይህ ሞዴል ሕግ ሲወጣ በሕገመንግስቱ የተደነገጉ የሕፃናት የሴቶችን መብቶችን የሚጣረስ መሆን እንደሌለበት ይታመናል። አፈፃፀም ላይ ግን ክፍተቶች ሊያጋጥሙ ይችላሉ፤ ግን በሂደት አስተሳሰቡን የማስረፅ ሥራ ይሰራል።

በነገራችን ላይ ኦሮሚያ ክልል ቀድሞ ይህንን ሞዴል ባሕላዊ የዳኝነት ሥርዓት ስለጀመረ ለሌሎች ተሞክሮ ይሆን ዘንድ የአዋጪነት ጥናት በዓለምአቀፍ ድርጅት አስጠንተናል። በዚህም ጥናት እውነትን በማውጣት ረገድ እንዲሁም የፍርድ ቤትን ጫና መቀነስ ላይ በጎ ተፅዕኖ እየፈጠረ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል። ያነሳሻቸው ችግሮችም እንዲሁ የታየ ሲሆን ኦሮሚያም ሆነ ሌሎች ክልሎች የሚማሩበት ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡- የባሕላዊ ፍርድ ቤቶች የመደበኛ ፍርድ ቤቶችን የሥራ ጫና በተጨባጭ መቀነሱን በጥናት መረጋገጥ አለበት ብለው የሚያነሱ የሕግ አካላት አሉ፤ በዚህ ላይ የእርሶ ሃሳብ ምንድን ነው?**

**ኤርሚያስ ዶ/ር፡-** በመርሕ ደረጃ ጫና ይቀንሳል የሚለውን መውሰድ አለብን። ግን በየትኞቹ ጉዳዮች የሚለውን ዝርዝር ነገር መለየት ያስፈልጋል። መደበኛ ፍርድ ቤት የሚመጡትን ጉዳዮች ለመቀነስ ሲባል ብቻ አይደለም ባሕላዊ ፍርድ ቤቶች እንዲቋቋሙ የተፈለገው። ሕገመንግስታዊ መብትም ጭምር በመሆኑ ነው።

የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት እኮ ሕገመንግስታዊ ነው። የባሕልና የቋንቋ ነፃነት ተብሎ የሚጠቀሰው እኮ ለፖለቲካ ፍጆታ ብቻ አይደለም። ባሕላዊ ፍርድ ቤቶች የተቋቋሙት የመደበኛ ፍርድ ቤቶችን ጫና ለመቀነስ ብቻ ሳይሆን ሕገ-መንግሥታዊ መብት በመሆኑ ነው። ባሕልን የማሳደግ መብት ሲባልም ጭፈራና እስክስታ ብቻ አይደለም፤ ይልቁኑም ነበርና ትርጉም ሊሰጡ የሚችሉ እሴቶችን ለማስቀጠል ኢንቨስት ስናደርግም ጭምር ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በሃገሪቱ ይተገባራል የተባለው የሽግግር ፍትሕ ምን ላይ ደገኛል?**

**ኤርሚያስ ዶ/ር፡-** በሃገሪቱ በተለያዩ ዘመናት የተከሰቱ፣ የቀጠሉ፣ ተደራራቢ እና ሰፊ የተጎጂና የአጥፊ ወሰን ያላቸው የሰብአዊ መብት ጥሰቶች፣ የእርስ በርስ ግጭቶች፣ ያልጠሩ ትርክቶች እና በደሎችን ለመፍታት በተለይም በእውነት፣ በእርቅ፣ በምህረት እና በፍትህ ላይ የተዋቀረ እና በግልፅ የሚመራ ሁለንተናዊ የሽግግር ፍትሕ ስልትን በተደራጀ፣ በተቀናጀ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ በሃገር አቀፍ ደረጃ ለመተግበር ያስችል ዘንድ የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሚያዚያ 9/2016 ዓ.ም እንዲፀድቅ ተደርጓል።

ፖሊሲውንም ለማስፈፀም የሚያስችል ዝርዝር «የሽግግር ፍትሕ ፖሊሲ የአፈፃፀም ፍኖተ ካርታም ተዘጋጅቷል። በዚህ የአፈፃፀም ፍኖተ ካርታ ከተካተቱ ጉዳዮች መካከል የሽግግር ፍትሕን ለማስፈፀም የሚያግዙ የባለድርሻ አካላት ሚናን መለየት፣ የሽግግር ፍትሕ ተቋማትን በፖሊሲው መሰረት ለማቋቋም የሚያስችሉ ተግባራትን መፈፀም ለአብነት ለሽግግር ፍትህ አስፈላጊ የሆኑ እንዲወጡ ማድረግ፣ የባለድርሻ አካላትን ቅንጅታዊ መድረክ መፍጠር የሚሉ ሃሳቦች ተካተዋል።

ከዚህ ባሻገር የሽግግር ፍትሕ ለማቋቋም የሚያስችሉ ሕጎችን የዘርፉ ባለሙያዎችን ባማስተባበር ማውጣት ተችሏል። ከእነዚህም መካከል የሽግግር ፍትሕ ልዩ ችሎት ማቋቋሚያ ረቂቅ አዋጅ፣ የዓለምአቀፍ ጉልህ ወንጀሎች ረቂቅ አዋጅ፣ የሽግግር ፍትሕ ልዩ አቃቤ ሕግ ፅሕፈት ቤት ማቋቋሚያ ረቂቅ አዋጅ፣ የእውነት አፈላላጊና የይቅርታ ኮሚሽን ማቋቋሚያ ረቂቅ አዋጅና የተቋምና የሕግ ሪፎርም ኮሚሽን ማቋቋሚያ ረቂቅ አዋጆች ዝግጅት ተጠናቀዋል። በቀጣይም ከባለድርሻ አካላት ጋር ውይይት የሚደረግባቸው ይሆናል።

**አዲስ ዘመን፡- የፍትሕ ስርዓቱን ለማሻሻል የቱንም ያህል አዳዲስ ሕጎች ቢወጡም መሬት ላይ በተጨባጭ ለውጥ አልመጣም፤ አሁንም ስርዓቱ በብልሹ አሰራሮች የተተበተበ ነው ብለው የሚያነሱ አሉ፤ እርሶ በዚህ ሃሳብ ይስማማሉ?**

**ኤርሚያስ ዶ/ር፡-** በነገራችን ላይ ዳኝነት በጣም ውስብሰብ የሆነ ስርዓት ነው። ከለውጡ በፊት ዳኞች የሚሾሙበት ሁኔታ በአብዛኛው በፖለቲካ ተፅዕኖ ነበር። በሪፎርሙ የዳኞች ሹመት፣ ምልመላ፤ ዝውውር ስርዓት ባለው መልኩ ለመምራት ይቻል ዘንድ በአዋጅ ደረጃ ፀድቆ እንዲተገበር ተደርጓል። አሁን ችግሩ ነፃነትና ተጠያቂነት የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታዎች ናቸው፤ ዳኝነት አካሉ ላይ አስተያየት መስጠት ተገቢ ባይሆንም ነፃነት ላይ ትኩረት ካደረግን የተባለው እሮሮ እውነት ነው። የፍኖተ ካርታው መነሻም ይኸው ነው።

አንዳንድ ቦታዎች ላይ ነፃነት በዝቶ አጉራዘለልነት የሚታይበት ሁኔታ ነበር፤ እጅግ አማራሪ የሆኑ ዳኝነትን በገንዘብ ለመሸጥ የሚደረጉ ሙከራዎች የሉም ማለት አልችልም። ይህ ማለት ግን መዋቅራዊ የሆነ ችግር ማለት አይደለም። ሆኖም ዳኞች ነፃነት ላይ አትኩረው ተጠያቂነትን በመተው እንዳሻቸው የሚሆኑበት ስርዓት አይቀጥልም።

በሕገ-መንግስቱም ተጠያቂነት ሊሰፍን እንደሚገባ የሚደነግግ በመሆኑ ዳኞችን የማጥራት ሥራ እንዲሰራ የተፈለገው። ይህም ሲባል ሙያዊ ብቃታቸውን፤ ስነ-ምግባራቸውና ገቢያቸውንም ጭምር የሚፈትሽ ነው። በእርግጥ በሙስና የተገኘ ገቢ በቀጥታ በስም ሊቀመጥ ስለማይችል ማግኘቱ ከባድ ነው። ሆኖም መፈተሽና ማጥራት ይገባል የሚለውን በመርህ ደረጃ ቅቡልነት አለው።

በመሆኑም ነፃነትን ብቻ እያውለበለብን ተጠያቂነትን ከኋላ ኪሳችን አድርገን የምንሰራው ሥራ ዞሮ ዞሮ ለሃገር አደጋ ነው። ምክንያቱም የፍትሕ ሪፎርሙ ከሃገረ-መንግስት ቀጣይነት፤ ከልማት፤ ከሕዝቦች አብሮ መኖር ፤ መዋቅራዊ በደል እንዳይኖር ከማድረግ አንፃር የሚሰራ ሥራ ነው። ፍትህ በሌለበት ልማት፣ ብልፅግና ቀጣይነትን እውን ማድረግ አይቻልም። በሰነዱም ተቀንሷል። በመሆኑም የሰራናቸውን ጥሩ ሥራዎች አጠናክረን መቀጠል አለብን።

**አዲስ ዘመን፡- ስሰጡን ማብራሪያ በዝግጅት ክፍሉ ስም ከልብ አመሰግናለሁ።**

**ኤርሚያስ ዶ/ር፡- እኔም አመሰግናለሁ።**

# በኤሌክትሪክ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ማመንጫ፣ ማከፋፈያ እና የማስተላለፊያ መስመር ፕሮጀክቶችን ይገነባል፤ ያስተዳድራል ያሉት ኃላፊው፣ ለፕሮጀክቶቹ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ አፍስሶ የኤሌክትሪክ ተደራሽነትን ለማስፋት እየሠራ ይገኛል ብለዋል። ይህም ሆኖ መሠረተ-ልማቱ ላይ በሚደርስ ስርቆት ኪሳራ እያጋጠመው መሆኑን አመልክተዋል።

በተለይም በከፍተኛ ኃይል ተሸካሚ የብረት ምሰሶዎች ላይ የሚፈጸመው ስርቆት የከፋ እንደሆነና ምሰሶዎችን ሙሉ ለሙሉ እስከመጣል የሚደርስ፤ የኤሌክትሪክ ፍሰትን እስከ ቀናት ብሎም እስከ ወራት በሚዘልቅ ሁኔታ የሚያስተጓጉል እንደሆነ አስታውቀዋል። ተቋሙ የሚሰረቁ ብረቶችን ለመተካት ከፍተኛ ወጪ እንደሚያወጣና በሚቋረጠው የኤሌክትሪክ ፍሰት ምክንያትም ማግኘት የሚገባውን ከፍተኛ ገቢ እያጣ መሆኑን ጠቁመዋል።

በ2015 ዓ.ም ተቋሙ በስርቆት ምክንያት 700 ሚሊዮን ብር ኪሳራ እንዳገጠመው፤ በ2016 ዓ.ም በተመሳሳይ ምክንያት ያጋጠመው ኪሳራ አንድ ቢሊዮን ብር መድረሱን ገልጸዋል። የስርቆት መጠኑ ከባለፉት አምስት ዓመታት ጀምሮ እያደገ መምጣቱን እንዲሁም ስርቆት የማይፈጽማቸው አዳዲስ ቦታዎችም ላይ ጭምር እየተከሰተ መሆኑን ተናግረዋል። ችግሩ እንደሀገር የተያዘውን የኤሌክትሪክ መሠረተ-ልማት የማስፋፋት እቅድ ፈተና ላይ ጥሎታል ብለዋል።

የብረት አቅላጭ ፋብሪካዎች የሚገዙትን ብረት መነሻ ሳያጣሩ መግዛታቸው ለመሠረተ-ልማት ስርቆት መባባስ ዋናው ምክንያት እንደሆነ አመልክተው፡- ፋብሪካዎቹ ምንም እንኳን በአሠራር መመሪያቸው ላይ የኤሌክትሪክ ኃይልን፣ የቴሌንና የባቡር ሐዲድን ብረቶች አንቀበልም የሚል መርሕ ቢኖራቸውም፤ ከተቋሙ መሠረተ-ልማቶች የሚሰረቁት ብረቶች ግን እየተቆራረጡና ቅርጻቸው እየተቀየረ መዳረሻቸው ብረት ማቅለጫ ፋብሪካዎች እንደሆነ መረጋገጡን ገልጸዋል።

ጉዳዩንም ፖሊስ እንዲያውቀውና አስፈላጊውን የክትትል ሥራ እንዲሠራ ስለመደረጉ አቶ ሞገስ ጠቁመው፤ ብረት አቅላጭ ፋብሪካዎች በወረቀት ላይ ላስቀመጡት አሠራር ቢገዙ፣ የኤሌክትሪክ መሠረተ-ልማት በዚህ ልክ ጉዳት ሊደርስበት እንደማይችል አስታውቀዋል ።

ተቋሙ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም አደጋውን ለመቀነስ የሚያስችል ጥናት እያስጠና እንደሚገኝ፣ የብሔራዊ መረጃ እና ደኅንነት ማዕከልም አስፈላጊውን የክትትል ሥርዓት እንዲዘረጋ የሚያስችል እቅድ ስለመነደፉ ገልጸዋል።

ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት ስርቆት በሚዘወተርባቸው አካባቢዎች በመገኘት ከላይኛው እስከ ታችኛው መዋቅር ካሉ የመስተዳድርና የፀጥታ አካላት ጋር በችግሩ መንስዔ እና መፍትሔው ላይ ውይይቶች ሲደረጉ እንደነበርም አስታውሰዋል። ሕዝቡን የማስገንዘብ ሥራ ሲሠራ እንደነበርም አስረድተዋል።

ይህ በሂደት ለውጥ ያመጣል ተብሎ ቢታመንበትም አሁን ላይ ብዙ አውድመው ጥቂት ማግኘት የሚፈልጉ የልማት ጸሮች ፈጥነው ከድርጊታቸው ባለመታቀባቸው ችግሩ እየከፋ ስለመሆኑ ጠቅሰዋል። እስከ አሁን ባለው ሁኔታ አጥፊዎች ለሕግ ሲቀርቡ ካጠፉት ጥፋት ጋር የሚመጣጠን አስተማሪ ቅጣት እንደማይጣልባቸው አመልክተዋል።

የኤሌክትሪክ ምሰሶ ቆርጠው ጥለውና ዘርፈው ሲያበቁ ሁለት ዓመት ብቻ ታስረው የሚወጡበት፤ አንዳንዴም በአነስተኛ የገንዘብ ቅጣት የሚለቀቁበት ሁኔታ እንዳለ አመልክተው፤ እንዲህ አይነቱ ቅጣት ወንጀል ፈጻሚዎችን ከድርጊታቸው እንደማያርማቸው አስታውቀዋል።

ተቋሙ የኤሌክትሪክ መሠረተ-ልማቶችን በልዩ ሕግ ከማስጠበቅ አንጻር ኬንያ፣ ታንዛኒያ፣ ፊሊፒን እና ሌሎች ሀገራት ተግባራዊ ያደረጓቸውን ከባድ ቅጣት የሚያስከትሉ ሕጎችን በመፈተሽ እና በመቀመር አጥፊዎች የሚታረሙበት ራሱን የቻለ የሕግ ማዕቀፍ እንዲዘጋጅ እያስጠና መሆኑን ጠቁመዋል።

አጥፊዎች በኅብረተሰቡ ጉያ ውስጥ ያሉና ከሕዝብና ከሀገር ጥቅም ይልቅ የራሳቸውን ርካሽ ጥቅም የሚያስቀድሙ፤ በሽርፍራፊ ሳንቲሞች የሚታለሉና ነገዎቻቸውን አሻግረው የማይመለከቱ ናቸው ያሉት አቶ ሞገስ፤ እነዚህን ግለሰቦች ኅብረተሰቡ አጋልጦ እንዲሰጥ ጥሪ አቅርበዋል።

# ‹‹በምትክ ቤቱ ላይ ቅሬታ አቅርበን ጠብቀ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ቤት ውስጥ ሰው እያለ እኛ የቆረጥነው መብራት የለም ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል።

በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ አንድ ነዋሪ የሆኑት ወይዘሮ እየሩሳሌም ታዬ ለኢፕድ እንደተናገሩት በኮሪደር ልማቱ ተነሺ ሲሆኑ የሚፈርሰው ለልማት በመሆኑ ምንም አይነት ቅሬታ እንደሌላቸው ይናገራሉ። ነገር ግን አብረዋቸው ከሚኖሯቸው የቤተሰብ አባላት ውስጥ ዓመት ያልሞላት “የዳውንሲንደረም” ሕመም ተጠቂ፤ የልብ ሕመምተኛ የሆነች የእህታቸው ልጅ እና የሚያሳድጓት የአዕምሮ ሕመምተኛ ቤተሰብ አሏቸው።

ለልማት እንዲነሱ የቤት ዕጣ ሲያወጡ ዕጣቸው የደረሳቸው በበሻሌ አካባቢ መሆኑ የአዕምሮ ሕመምተኛ ለሆነችው ቤተሰባቸው፤ ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ሕክምና ለምትከታተለው የ‹‹ዳውን ሲንድረም›› ተጠቂ እና የልብ ሕመምተኛ ለሆነችው የእህታቸው ልጅ ቦታው ሩቅ በመሆኑ ለአዲስ አበባ ቤቶች ልማት እና አስተዳደር ቢሮ ቅሬታ አስገብተው ቅሬታው ተቀባይነት ማግኘቱን ይናገራሉ። በተቋሙ ቅሬታውም ተቀባይነት በማግኘቱ ቤቱ እስኪቀየርላቸው ድረስም በልማት በሚፈርሰው ቤት ውስጥ እንዲኖሩ ተወስኖላቸዋል።

ታኅሣሥ 9 ቀን 2017 ዓ.ም ግን በወረዳው ሠራተኛ የሆኑ ግለሰቦች የቅሬታ ሂደት ላይ እንደሆኑ እየታወቀ የቤታቸውን መብራት መስመር አቋርጠውት እንደሄዱ እና ጨለማ ውስጥ ሕመምተኛ ቤተሰብ ይዞ መቀመጥ ከባድ ስለሆነ ከፍተኛ መረበሽ ውስጥ እንዳሉ ገልጸዋል። ቆጣሪው ይነሳልን ጥያቄ ባላቀረብንበት ሁኔታ በቤቱ ውስጥ እየኖርን መብራት መቆረጡ ተገቢ አይደለም ሲሉ ቅሬታቸውን ገልጸዋል።

በወረዳው ቤቶች አስተዳደር ባለሙያ የሆኑት አቶ ዐቢይ የሚባሉ ግለሰብ መስመሩ ሲቆረጥ በቦታው እንደነበሩ እና በስልክም ሲያነጋግሯቸው መስመሩን እንደሄደ እና ቦታውን መልቀቅ እንዳለባቸው እንደነገሯቸው ገልጸዋል። ወይዘሮዋም መነሳት ፍላጎት ቢኖራቸውም ቤቱን ስላልተረከቡ ፈራሽ የሆነውን ቤታቸውን ሊለቁ እንዳልቻሉ ነግረዋቸው የስልኩ ንግግር እንደተቋረጠ ተናግረዋል።

በአካባቢያቸው ያሉ እና በልማት ተነሺ የሆኑ ጎረቤቶቻቸው የመብራት መስመራቸው እንዳልተቋረጠባቸው ተናግረው፤ የእሳቸው መስመር ብቻ ተለይቶ መቋረጡ ምክንያቱ በወረዳው የሚሠሩ ባለሙያዎች ሊሆኑ እንደሚችሉ ጥርጣሬያቸውን ገልጸዋል።

በልማቱ ደስተኞች መሆናቸውን የገለጹት ወይዘሮዋ ቤቱ እንደተሰጣቸውም ለመልቀቅ ዝግጁ መሆናቸውን ተናግረው፤ ነገር ግን አሁን ይህ ባልሆነበት ሁኔታ መብራታቸውን መቋረጡ ተገቢ አይደለም ሲሉ ቅሬታቸውን አቅርበዋል። በቤቶች ልማት እና አስተዳደር በኩል ያለው ቅሬታን የመስማትና የመፍታት አካሄድ መልካም እንደሆነ አመልክተዋል።

ሌላኛዋ ቅሬታ አቅራቢ ወይዘሮ ሙሉነሽ ታደሰ እንደሚሉት፤ ከዚህ ቀደም አቅመ ደካማ በመሆናቸው እና እግራቸውን በመታመማቸው በዕጣ የደረሳቸው ቤት እንዲቀየር ለአዲስ አበባ ቤቶች ልማት እና አስተዳደር ቢሮ አቤት ብለው ለቅሬታቸው ምላሽ ያገኙት 7/04/2017 ከሰዓት በኋላ ነው። ነገር ግን በወረዳው በኩል በ9/04/2017 እስከ ቀኑ 11 ሰዓት ቤቱን ለቀው እንዲወጡ እንደተነገራቸው እና ቅሬታ ላይ የቆዩ ስለነበሩ ቤቱን ለመልቀቅ ዝግጅት አለማድረጋቸውን ገልጸዋል።

የደረሳቸውን ቤት ለማስተካከል ጊዜ እንደሚያስፈልጋቸው ቢናገሩም በዕለቱ ቤቱን ካለቀቁ የእቃ ማጓጓዣ ትራንስፖርት አገልግሎት እንደማያገኙ እንደተነገራቸው አብራርተዋል።

በቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 1 ቤቶች አስተዳደር ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ ደምሰው ትኩ የልማት ተነሺዎች ወደ ደረሳቸው ቤት ሲገቡ መጨረሻ ላይ ቆጣሪ ይነሳልኝ ጥያቄ አቅርበው ይነሳል እንጂ በምንም ተዓምር ሰው ቤት ውስጥ እያለ እኛ የቆረጥነው መብራት የለም። ቅሬታውን እስካሁን አላውቅም፤ እንዲህ አይነት አሠራር የለም ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል።

እንደ ጽሕፈት ቤት ኃላፊው ገለጻ፤ የኮሪደር ልማቱ ሥራ በአደረጃጀት የሚመራ ነው። መብራት የሚቆረጠው እያንዳንዱ ሰው ከቤቱ ወጥቶ ወደ ምትክ ወደተዘጋጀለት ቤት ከሄደ በኋላ ነው። ይህ ሲሆንም ነዋሪዎች ቆጣሪ ይነሳኝ ብለው ሲያቀርቡ የመብራት ኃይል ሠራተኞች ጠርተን የሚቆረጥበት አሠራር ነው ያለው።

ትናንት ተቆረጠብን ስለተባለው የመብራት ቅሬታ መብራት እንዲቆረጥ ተብሎ የተጠራ የመብራት ኃይል ሠራተኛ የለም። ቅሬታ ያቀረቡ ነዋሪዎች ካሉ የተነሱትን ሲቆርጡ በስህተት ከቆረጡባቸው ችግሩን እንቀርፋለን።

በተቀናጀና በተናበበ መንገድ በቁጥጥርና በክትትል የምትሠሩ ከሆነ ከአንድ የመብራት ፖል ላይ መብራት ሲቆረጥ እኛ አናውቅም ማለት መናበቡን ጥያቄ ውስጥ አያስገባም ወይ ተብሎ ለተነሳቸው ጥያቄ ሲመልሱ፤ በዕለቱ የተጠራ የመብራት ኃይል ሠራተኛ የለም። ቅሬታው በምን ሁኔታ እንደቀረበ አላውቅም። ነገር ግን ማንም ይቁረጥ ማን ችግሩን እንፈታለን ነው ያሉት።

ለአዲስ አበባ ቤቶች ልማት እና አስተዳደር ቢሮ አቤት ብለው ለቅሬታቸው ምላሽ ያገኙት በ7/4/2017 ዓ.ም ከሰዓት በኋላ ነው። ነገር ግን በወረዳው በኩል በ9/4/2017 ዓ.ም እስከ ቀኑ 11 ሰዓት ቤቱን ለቀው እንዲወጡ እንደተነገራቸው ገልጸዋል። በዚህ ሀሳብ ላይ ምላሽዎት ምንድን ነው? ስንል ላነሳንላቸው ጥያቄ አቶ ደምሰው በምላሻቸው ቤታቸውን አይተው ለመግባት ከተዘጋጁ በኋላ እንጂ ዛሬውኑ ተነሱ የሚል አካል የለም ብለዋል።

ይህ ከሆነ የቅሬታው ምንጩ ምንድን ነው ብለው ያስባሉ? የሚነሱት እያንዳንዱ ነገር ከተዘጋጀላቸው እና የሚስፈልጋቸውን መሠረተ ልማት ከተሟላ በኋላ እንጂ እንዲሁ የሚነሱበት አሠራርም አግባብ የለም። ቅሬታ ያላቸው ሰዎች ቅሬታው እስኪፈታላቸው እንጠብቃለን።

ቅሬታቸው ተቀባይነት አግኝቶ ወደ ቤታቸው ለመግባት የዝግጅት ጊዜ ተነፍጎኛል ጥድፊያ ሆኖብኛል የሚል ቅሬታ አንስተዋልና ምላሽዎት ምንድን ነው? በምንም ተዓምር እቃ የሚጭኑት በተዘጋጁ ሰዓት እና ጫኑልን ባሉን ጊዜ ነው እንጂ በግዴታ የሚሠራ ሥራ የለም ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል።

ወረዳ ላይ ያሉ አንዳንድ ባለሙያዎች ለተነሽዎች የመልካም አስተዳደር ቅሬታ ምንጭ እንደሆኑ ይነገራል። እዚህ ላይ አስተያየትዎት ምንድነው? የባለሙያዎች ቁጥጥር እና ክትትሉ እስከ ምን ድረስ ነው? ሠራተኞች በትክክል እንቆጣጠራለን። በቁጥጥሩ ግን የዲስፕሊን እርምጃ የተወሰደበት ሠራተኛ የለም። እስካሁን ስድስት የሚደርሱ ቅሬታዎች ቀርበውልን አምስቱን በተገቢው መንገድ ምላሽ ሰጥተናል ሲሉ የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ ተናግረዋል።

# ሠላማዊ ሰልፉ ሕዝቡ ምን ያክል...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ሰልፉ እንደ መንግሥት ልዩ ትርጉም አለው ያሉት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ መንግሥት ለሠላም ያደረገውን ጥረት በአደባባይ ወጥቶ የደገፈበት ነው ብለዋል።

በሰልፉ ሕዝቡ መንግሥትን ብቻ አይደለም የደገፈው፣ የደገፈው ሠላምን ነው ብለዋል። ሠላም ሲሆን ለመንግሥት ትልቅ አቅም መሆኑን ነው የተናገሩት።

የተደረገው የሠላም ሰልፍ በቀጣይ ለሚደረገው ሠላማዊ እንቅስቃሴ ጉልበት የሚፈጥር ነው ብለዋል። በሕዝባችን ትልቅ ኩራት ተሰምቶኛል፣ ምስጋናም እናቀርባለን ነው ያሉት። ሕዝቡ በሠላም ወጥቶ እንዲገባ ላደረጉ የፀጥታ ኃይሎች ምስጋና አቅርበዋል።

ሰልፉ ወደፊት ለሚደረገው የሕግ ማስከበር እና የሠላም ሥራ ትልቅ አስተዋፅዖ ይኖረዋል ነው ያሉት። መንግሥት ሠላማዊ አማራጮችን ቀዳሚ የችግር መፍቻ አድርጎ እንደሚጠቀምም አስታውቀዋል። አውዳሚ ተግባርን አንመርጥም፣ የምንመርጠው ዘላቂ ሠላምን የሚያመጣውን ሠላማዊ አማራጮችን ነው ብለዋል።

እንደ አሚኮ ዘገባ ችግሩ ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የሠላም አማራጮችን መፈለጋቸውን እና ማስቀመጣቸውን የተናገሩት ርዕሰ መስተዳድሩ፤ የሠላም አማራጭ ለይስሙላ የምናደርገው ሳይሆን አምነንበት እና አዋጭ መሆኑን ተረድተን የምናደርገው ነው ብለዋል።

የክልሉ ሕዝብ በአንድነት ወጥቶ ባሳየው የሠላም ፍላጎት ኮርተናል፣ ምስጋናም ይገባዋል ብለዋል።

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ተመስገን ጥሩነህ ትናንት በማኅበራዊ ትስስር ገፃቸው ባስተላለፉት መልዕክት በተለያዩ የአማራ ክልል ከተሞች፣ የገጠር ወረዳዎች እና ቀበሌዎች ሕዝባችን "ሠላም ለሁሉም፣ ሁሉም ለሠላም" በሚል መሪ ሀሳብ በነቂስ ወጥቶ ላሳየው የሠላም የድጋፍ ሰልፍ ምስጋና ይገባዋል ብለዋል።

ሠላም ወዳዱ ሕዝባችን መንግሥት ለሠላም እያቀረበ ያለውን ተደጋጋሚ ጥሪ በመደገፍና ፅንፈኝነትን በማውገዝ የታጠቁ ቡድኖች ወደ ሠላም እንዲመጡ ጥሪ አቅርቧል ያሉት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የአማራ ክልልን የሠላምና የልማት ማዕከል ለማድረግ ሁሉም ለሠላም ዘብ ሊቆም ይገባል ሲሉም ገልጸዋል።

መንግሥት ሁልጊዜም ቢሆን ለሠላም በሩ ክፍት በመሆኑ ትጥቅ ያነሱ ቡድኖች ፅንፈኝነት እና ግጭት ማንንም እንደማይጠቅም በመገንዘብ ወደ ሠላማዊ መድረኩ እንዲመጡ ጥሪ እናቀርባለን ነው ያሉት።

የብልፅግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት አደም ፋራህ በበኩላቸው ባስተላለፉት መልዕክትም፤ በአማራ ክልል የተለያዩ ከተሞች ሕዝቡ በነቂስ በመውጣት በክልሉ ሠላም እንዲሰፍን፣ የሕግ የበላይነት እንዲከበር፣ በንፁሓን ላይ ግፍ እየፈፀሙ የሚገኙ ፅንፈኛ ኃይሎች ለሕግ እንዲቀርቡ፣ መንግሥት በተደጋጋሚ እያቀረበ ለሚገኘው የሠላም ጥሪ ድጋፍ እንደሚቸር በይፋ ድምፁን ማሰማቱን ገልጸዋል።

የክልሉን ሕዝብ ላቀረበው የሠላም ጥሪም ምስጋናቸውን አቅርበው፤ በቀጣይም ክልሉ በተሟላ ሁኔታ ዳግም ወደ ሠላማዊ እንቅስቃሴ እንዲመለስ በብልፅግና ፓርቲ የሚመራው መንግሥት ኅብረተሰቡን በማሳተፍ ያላሰለሰ ጥረት ማድረጉን እንደሚቀጥል ተናግረዋል።

“በመንግሥት በኩል ለሠላም፣ ለውይይትና ድርድር የምትጠልቅ ጀምበር እንደሌለችም ደጋግመን ማረጋገጥ እንወዳለን” ሲሉ አቶ አደም በማኅበራዊ ትስስር ገጻቸው አስፍረዋል።

ስለሆነም በአማራ ክልል ታጥቀው የሚንቀሳቀሱ አካላት በኃይል አማራጭ የሚገኝ መፍትሔ አለመኖሩን በመረዳት በዛሬው ሰልፍ ጨምሮ ሕዝቡ በተደጋጋሚ እያነሳቸው ያሉ ጥያቄዎች ምላሽ እንዲያገኙ፣ በተለያዩ የሀገሪቷ አካባቢዎች እየታየ እንደሚገኘው በአስቸኳይ ወደ ሠላማዊ እንቅስቃሴ እንዲመለሱ ጥሪ አቅርበዋል።

በባሕር ዳር፣ በጎንደር፣ በደሴ፣ በደብረማርቆስ፣ በሰቆጣ፣ እንጅባራ፣ደብረ ብርሃን፣ በአርጎባ በደባርቅ፣ በደብረታቦር፣ በኮምቦልቻ፣ በሌሎች ከተሞችና የገጠር ወረዳዎች ትናንት ሕዝባዊ ሰልፎች ተካሂደዋል።

በሰልፉ የተሳተፉ እንዳሉት፤ ክልላችን ጦርነት ሳይሆን ሠላምና ልማት ነው የሚያስፈልገው፣ መንግሥት ሕግ በማስከበር የዜጎችን ሕይወት መታደግ አለበት የሚሉና ሌሎችን መልዕክቶች አስተላልፈዋል።

ፅንፈኛው ኃይል በንጹሓን ላይ የሚፈጽመው ግድያና መፈናቀል ሊቆም ይገባል፣ የመከላከያ ሠራዊታችን፣ የፌዴራልና የክልላችን የፀጥታ ኃይሎች ለከፈሉት ዋጋ ክብር እንሰጣለን ብለዋል። የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ፅንፈኞችን በማውገዝ የሕግ ማስከበሩን ተግባር የሚደግፉ መልዕክቶችንም አስተላልፈዋል።

ክልላችንን የሠላምና የልማት ማዕከል ለማድረግ ሁላችንም ለሠላም ዘብ እንቆማለን፤ በግጭት የሚፈታ ምንም ነገር እንደሌለ ሁሉም ተገንዝቦ ታጣቂ ኃይሎች ለሠላም ቅድሚያ በመስጠት መነጋገርና መወያየት እንዳለባቸውም ተናግረዋል።

“በንፁሓን ላይ የሚፈፀመው ግድያ፣ ማገትና ማፈናቀል ሊቆም ይገባል፤ ንጹሓን በመጨፍጨፍ አማራን ነፃ ማውጣት አይቻልም፤ መንግሥት በተደጋጋሚ የሚያደርገውን የሠላም ጥሪ እንደግፋለን፤ የልማት ማዕከል የነበረውን ክልላችንን የጦርነት ቀጣና ለማድረግ የሚሠራው ሥራ የባንዳነትና የፅንፈኝነት ጥግ ነው” የሚሉ እና ሌሎች ዘላቂ ሠላምና ልማትን የሚጠይቁ መልዕክቶች ተላልፈዋል።

እንዲሁም ሰልፈኞቹ “ሠላም ተጠምተናል”፣ “ሠላም የጋራ ሐብት ነው”፣ “ከሠላም ዕጦት ያጣነው እንጂ ያተረፍነው የለም”፣ “መንግሥት በተደጋጋሚ ያደረገውን የሠላም ጥሪ እንደግፋለን”፣ “ንፁሐንን በግፍ መጨፍጨፍ አረመኔነት በመሆኑ እናወግዛለን” የሚሉና መሠል መፈክሮች በሰልፎቹ ተሰምተዋል።

የክልሉ ፖሊስ ባወጣው መግለጫም÷ የአማራ ክልል ሕዝብ ለዓመታት የተደቀነበትን የሰቆቃ ቀንበር የሚያወግዝ ሠላማዊ ሰልፍ “ሠላም ለሁሉም፤ ሁሉም ለሠላም” በሚል መሪ ሃሳብ በተለያዩ ከተሞች ማካሄዱን አንስቷል።

ለዓመታት ክልሉ በራሱ አለሁ ባይ ፅንፈኛ ኃይሎች ምክንያት በሰቆቃ ሕይወት ውስጥ እንዲኳዝ፣ እንዲዘረፍ፣ እንዲፈናቀልና እንዲሰደድ መደረጉን ጠቁሞ፤ ይህን የመከራ ቀንበር የተሸከመው የክልሉ ሕዝብ የሠላም ካውንስል እስከመወከል የደረሰ “ሠላሜን መልሱልኝ” ጥያቄውን ከጀመረ መሰነባበቱን ጠቅሷል።

ይሁን እንጂ ፅንፈኛው ኃይል የማኅበረሰብን የሠላም ጥያቄ “ጆሮ ዳባ ልበስ...” በማለት ከሰብል ማቃጠል ጀምሮ የክልሉን ሕዝብ ባሕልና ወግ የማይገልጽ፣ ዘመኑን የማይመጥንና ፀያፍ ተግባር መፈጸሙንም አስታውሷል። በትናንትናው ዕለትም የፅንፈኛውን ተግባራት የሚያወግዝ ሰልፍ በተለያዩ የክልሉ ከተሞች ተካሂደው በስኬት መጠናቀቃቸውን ፖሊስ አስታውቋል።

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

# ከገጸ ሰብ ባህር

ሙሉጌታ ብርሃኑ

ምድራችን ከተሸከመቻቸው እጅግ ግዙፍና ጥልቅ ባህሮች የገዘፈው ባህር የት ነው ካልን የትም ሳንሄድ እኛው ውስጥ ነው። ከሰውነት ክፍሎቻችን መካከል ባህርን የመሰለ ባህሪ ያለው ከራስ ቅላችን ላይ የሰፈረው አዕምሯችን ነው። የገጸ ሰብ ባህረ ሃሳብ የሚለን አንድም እንዲህ ይመስለኛል።

ባህር የምናውቃቸውንና የማናውቃቸውን ፍጥረታትና ቁሳዊ አካላትን አጭቆ የያዘ ምስጢራዊ የምድራችን ክፍል ነው። አዕምሮም ሌላው ሰው ቀርቶ ራሱ ባለቤቱም በውል ባልገባው ውስብስብ ነገሮች የተደረተና ምስጢራዊው የሕይወት ቁልፍ የተሰወረበት ስፍራ ነው። ባህር ማለት ግዙፍ የውሃ ክምችት ብቻ አይደለም። በዓይናችን ልናጤናቸው ከማንችላቸው ነፍሳት እስከ ግዙፍ ፍጥረታት ድረስ አሉበት። እጅግ አስደናቂ የሆነውን ውበት የምንመከተው ከባህር ውስጥ ነው።

መድኃኒትና መርዝ ከአንድ ግዙፍ ውሃ ውስጥ ይኖራሉ። የሰው ልጆች ለመብልነት ከሚጠቀመው ዓሳ ጋር የሰውን ልጅ የሚበላው አዞ ይገኝበታል። ለፍቅር አቻ የለውም ከሚባለው ዶልፊን አጠገብ አደገኛው ሻርክ ብቅ ይልበታል። በድምሩ እዚህ ውስጥ ሞትና ሕይወት መሳ ለመሳ ሲዋኙ እንመለከታለን። ከተንኮል የነጹ የዋሆች፣ አደገኛ መርዝ አንጋቢዎች፣ ውብና ማራኪ፣ አስቀያሚና ዘግናኝ... ቁጥር ራሱ ቆጥሮ የማይችላቸው ፍጥረታት ከአንድ ባህር ውስጥ ይኖራሉ። የአንድ ደራሲ የምናብ ዓለምም ልክ እንዲሁ ነው።

የአዕምሮው የባህር ውሃ ማለት ሃሳቡ ነው። ሃሳብ ከሌለ ውስጡ ደረቅ በረሃ ነው። በረሃ ከሆነ ደግሞ ከእነዚያ ፍጥረታት መካከል አንዳቸውም አይኖሩም። ባህሩንና የባህሩን ዓሳዎች የፈጠረው ፈጣሪ ሁሉን ሠሪና አድራጊ እንደሆነበት ሁሉ፤ ከራሱ የሃሳብ ባህር ውስጥ የሰጠመ ደራሲም በባህሩ ውስጥ ያሻውን ፈጥሮ እንዳሻው ያደርጋቸዋል። እኚህ የደራሲው ፍጥረታትም ገጸ ሰብ(ገጸ ባህሪያት) ናቸው። በሃሳባዊው የታሪክ ውሃ ውስጥ ነዋሪ አድርጎ የየራሳቸውን መልክና ግብር ይሰጣቸዋል።

የፈጣሪው ፍጡር፣ ምስኪኑ ደራሲ እሱም ባምሳሉ ይፈጥራል። የሰው ልጅን የፈጠረ አምላክ ከአፈር አበጅቶ፣ እስትንፋሱን እፍ ብሎ ሲያበቃ "በአምሳሌ ፈጠርኩት" ይላል። ታዲያ ምናልባትም ከአምሳል ሁሉ አንደኛው አምሳል ይህ የደራሲው የመፍጠር ሃይል ይሆናል። ደራሲው የእግዜር፣ ገጸ ባህሪያቱም የደራሲው አምሳል ናቸው።

በመለኮታዊው አምላክና በደራሲነት ውስጥ ያለው ፈጣሪነት ሁለቱም ያለማንም ጣልቃገብነት የፈለጉትን እንዳሻቸው መፍጠራቸው ነው። ነገር ግን በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት ደግሞ ገሀዳዊ መለኮትና ምናባዊ ተምሳሌት ነው። አንደኛው የመንፈስ፣ ሁለተኛው ደግሞ የአዕምሮ ጨዋታ ነው። አምላካዊውና እውን ሆኖ በሚታየው ፈጣሪነት ውስጥ ሙሉእነትና ዘላለማዊ የራስ የበላይነት ያለበት ነው።

ምስኪኑ ደራሲ ግን በውበትና ጥበብ ሁሉንም ፈጥሮ ሲያበቃ ለራሱና በራሱ ላይ ምንም ነገር ለማድረግ የማይችልበት ሰንኮፍ ውስጥ ሊሆን ይችላል። አንደኛውን ገጸ ባህሪ ሀብታም፣ ጀግና፣ ዘናጭና አማላይ አድርጎ ፈጥሮት እሱ ግን ምንም የሌለው መናጢ ድሃ ሊሆን ይችላል። ያሻውን ነገር ላሻው ገጸ ሰብ አስታቅፎ የሚያንበሸብሸው ምስኪኑ ደራሲ የዕለት ጉርሱንም ሊያጣ ይችላል። የርሱ ትልቁ ሕይወት ለጥበብ እስትንፋሱን ሊሰጥ ከስጋ ዓለም መንኖ ወደ ባህሩ መሄድና መጥለቅ ነው።

በአንድ ባህር ውስጥ፣ በአንዱ ምስኪን ደራሲ ምናብ ውስጥ መልከ መልካም መልአክና መልከ ጥፉ ሰይጣን፣ ምስኪን የዋህና አስፈሪ ጨካኝ፣ ሀብታምና ድሃ፣ ቆንጆና አስቀያሚ፣ ጥቁር ወፍራምና ቀይ ቀጭን፣ ምሁርና መሃይም... አድርጎ የፈጠራቸውን ገጸ ባህሪያት ጎንበስ ቀና እያደረገ ባሻው መልኩ እግዜራቸው ይሆናል።

ስለ ደራሲው ዓለም የምናብ ባህረ ሃሳብና የውስጡ ፍጥረት ስለሆኑት ስለነዚሁ ገጸ ሰቦች ከባህሩ የማንኪያ ያህል እንጭለፍ። ታዲያ የደራሲው ምናባዊ ፍጥረት የሆኑት እኚህ ገጸ ባህሪያት፤ ከባህሩ እየቀዘፉ ከወዴትስ ይሄዳሉ? አድራሻና መልክ ግብራቸውስ?

መገኛቸው ባህሩ ነው። ባህሩም ከደራሲው ምናብ ውስጥ ነው። ደራሲውም በዋናነት ምናልባትም ከሁለት በአንዱ ላይ ነው፤ ከፊልም አሊያም ከመጽሐፍ መርከብ ላይ። ከሃሳብ ውሃው ላይ ከሚሽከረከረው ባህር ሰርጓጁ መርከቡ ላይ ስምጥ እየገባ፣ እምጥ እየተሰወረ፣ የታሪክ አፈርን በውሃው ለውሶ የወደደውን ይፈጥራል። ብሽቅ፣



ጨካኝ፣ አጎብዳጅ፣ አሽሟጣጭ፣ ተወዳጅና ተናፋቂ፣ ውብ፣ ፋንጋ... ሁሉንም እንደ ጥበቡ። እኛ ግን እንደ እይታ ከሁለት ከፍለን ልንመለከታቸው ይገባል።

የመጀመሪያው ነገር በፊልሞች ውስጥ የምንመለከታቸው ገጸ ባህሪያትና በመጽሐፍት ውስጥ የምናገኛቸው፤ በሁለቱ መካከል አንድ መሠረታዊ የሆነ ልዩነት አለ። ደራሲው ስዕላዊ አድርጎ በአንድ የልቦለድ ታሪክ ውስጥ ያኖራቸው ገጸ ሰቦች፤ የሚታዩት በአንባቢው ዓይነ ህሊና ነው። በፊልም ውስጥ የሚገኙ ገጸ ባህሪያት ግን አካላዊ ገጽታን ተላብሰው፣ በተዋንያኑ ተምሳሌትነት ገሀድ ሆነው ይታያሉ።

ሁለቱም ገጸ ባህሪያት ውልደትን እንጂ ሞትን አያውቁም። ይህ ማለት በታሪኩ ሴራ ውስጥ አይሞቱም ሳይሆን፤ በየትኛውም ጊዜና ቦታ ከመጀመሪያው የሚጨምር ዕድሜና ማንነት አይኖራቸውም። ከዛሬ አሥር ዓመት በፊት ዕድሜው 40 የነበረው ገጸ ባህሪ ዘንድሮም ያው አርባ ነው። አርጅቶ መሸበት፣ እድሜ ገፍቶ መሞት የሚባል ነገር አይደርስባቸውም። ደራሲው መጀመሪያ ላይ የወሰነላቸውን እጣ ፈንታ መኖር ነው ድርሻቸው። ደራሲው የረገማቸው እንደሆን ዘለዓለማቸውን እንደተረገሙ ይኖራሉ። የባረካቸው እንደሆነም እንደተባረኩ ይኖራሉ። ምንም የማያውቁ መሃይም ከነበሩ እድሜ ልካቸውን መሃይም እንደሆኑ ናቸው። በደራሲው የተጫነባቸውን የድህነት ቀንበር የሚያወርድላቸው አይኖርም።

አብዛኛውን ጊዜ በተለይ ደግሞ የታሪኩ ቁልፍ የሆኑ ገጸ ባህሪያት ከደራሲው እውነተኛ ማንነትና አስተሳሰብ ጋር የሚዛመዱ ናቸው። እንዲሆን የሚፈልገውንና የሚመኘውን የሚያኖረው እነርሱ ላይ ነው። ለዚህ እንደ ምሳሌ ፍቅር እስከ መቃብርን እንውሰድ። ሀዲስ አለማየሁ ፍቅር እስከ መቃብርን ሲጽፉልን እንዲሁ ከምናብ ብቻ በመነሳት አልነበረም። ለምን ካልን ብዙሃኑን የሚያስማማው የዚህ መጽሐፍ ወግ ፍቅር ነው። በዛብህና ሰብለ ወንጌል ናቸው። ሀዲስ ያሳለፉትንና የነበሩበትን የፍቅር ሕይወት በቀጥታም ባይሆን ከእነርሱ ላይ አሳርፈውታል።

ሀዲስ በጣም አብዝተው የሚወዷትና ነብሳቸውን የሰጧት ሴት ነበረቻቸው። እሷም ከበበ ጸሐይ ናት። በጣፋጭ ፍቅራቸው መሃል ግን መራራ የሞት ጽዋ ተደፋበት። ጸሐይ ለዘለዓለሙ አሸለበች። ከዚያ በኋላ ሲወራ የምንሰማው እውነትም ከእርሷ ሞት በኋላ ሀዲስ ከማንኛይቱም ሴት ጋር አለመድረሳቸውን ነው። ውሃ አጣጭ ፍለጋ ቀርቶ የሌላ ሴት ጠረን ከትንፋሻቸው ጋር ተዋህዶ አያውቅም። የደራሲው ይኼ ሁኔታም በበዛብህና በሰብለ ወንጌል ፍቅር ላይ ተጽኗዊ ዐሻራውን አሳርፏል።

በአንድም ሆነ በሌላ ደግሞ የገጸ ባህሪያት ማንነትና ምንነት በደራሲው ቀሪ ሕይወት ላይ ዳፋቸውን ያኖራሉ። ለዚህ ማሳያው "ኦሮማይ" ነው። በዓሉ ግርማ እምጥ ይግባ ስምጥ እንዳይታወቅ የሆነው በጻፈው ታሪክ ብቻ ሳይሆን በገጸ ባህሪያቱ አሳሳልም ጭምር ነው። አንዳንዱ ገጸ ባህሪያት መልክና ቁመና እንዲሁም ድርጊቶቻቸው የገሀዱ ውክልና አለባቸው የሚል ነው። ታዲያ ከታሪክና መቼት ባሻገር ገጸ ባህሪያት በራሳቸው አንድ የተለየ ጭብጥ ይኖራቸዋል። በዓሉ ግርማ ጸጋዬን ጋዜጠኛ አድርጎ ሲፈጥረው ከራሱ መስታየት ፊት ቆሞ ነው። ምክንያቱም ራሱ በዓሉ ጋዜጠኛ ነበር። ጋዜጠኛ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ውስጣዊውን ማንነቱን ያሰፈረው በፈጠረው ጋዜጠኛ ጸጋዬ ኃይለማርያም ላይ ነው። የነብሱን አዱኛ ዘርቶበታል። በመጽሐፉ ውስጥ በውክልና የተቀመጠው ብቻውን አይደለም። ኮሎኔል ታሪኩ ወልዳይ፣ የሺጥላ ማስረሻ፣ ተድላ ረጋሳ፣ ስዕላይ ባራኺ የተሰኙት ገጸ ባህሪያትን መጥቀስ ይቻላል። ምንም እንኳን የነበረው የፍቅር ግንኙነት ፈጠራ ቢሆንም ፊያሜታ ጊላይም ከእውን የተወሰደች ናት። ግዳችን ስለ እነርሱ ስላልሆነ እነማን ናቸው የሚለውን ባንጠቅሰውም እኚህ ሁሉ ግን ተደማምረው በዓሉን አስምጠውታል።

ገጸ ባህሪያት የሚወለዱት ከደራሲው የምናብ ባህር ብቻ ነውን? እርግጥ ነው ከደራሲው ምናባዊ ዓለም ውስጥ ይወለዳሉ። ግን ከደራሲው፣ በደራሲው ብቻ የሚፈጠሩ አዲስ ፍጥረት አይደሉም። ከእኛ ማንነትና ሕይወት የራቁ፣ ከዚህ ቀደም ዓይተንና ሰምተን የማናውቃቸው እንግዳ ፍጡራን አይደሉም። በአንድም ሆነ በሌላ እኚህን ገጸ ባህሪያት ከዚህ ቀደም እናውቃቸዋለን አሊያም ደግሞ ከሆነ ጊዜ በኋላ እንገናኛቸዋለን።

በአንድ ፊልም ላይ አሊያም መጽሐፍ ላይ የምናገኘው ገጸ ባህሪ ከቤተሰቦቻችን መካከል አንደኛው ሊሆን ይችላል። ከጓደኛ ወዳጅ ዘመድ፣ ከሰፈርና ሥራ ቦታዎቻችን ከአንደኛው አይጠፋም። የደራሲው ምናባዊ ፈጠራ ናቸው ስንል ፈጽሞ በዚህች ምድር ላይ የሌሉ፣ ያልነበሩና ወደፊትም ሊኖሩ የማይችሉ ናቸው ማለት አይደለም። ደራሲው ከዚህች ዓለም ተገልሎ ለብቻው የኖረ አይደለምና ምናባዊ ማማው የተገነባው ከልጅነቱ ጀምሮ ከኖረው፣ ከተመለከተውና ከሰማው፣ እንዲሁም አሁን ከሚኖረው ሕይወት ላይ ነው። ነገር ግን ፈጠራ እንዲባል ያደረገው ነገር የገጸ ባህሪያቱም ሆነ የታሪኩ መቼት ማለትም ደግሞ በጊዜና ቦታ የተወሰነ ማስረጃና መረጃ ሊገኝለት ስለማይችል ነው።

የገጸ ባህሪያት ውልደት ከማህበረሰባዊ የኑሮና ህይወት ማኅፀን ውስጥ ነው ስንል ደግሞ በአንደኛው ገጸ ሰብ ውስጥ የተመለከትነውን ባህሪና ማንነት ሁል ጊዜም ሳይጎድልና ሳይሸራረፍ እንደወረደ ከአንድ ሰው ላይ ልናገኘው እንችላለን ማለት አይደለም። ደራሲው አንዱን ክፉ ገጸ ባህሪ ለመግለጽ ጨካኝ፣ ነፍሰ ገዳይ፣ ሴሰኛ፣ ኪስ አውላቂ...አድርጎ ቢስለውና ይህን ሰውዬ ከገሀዱ ዓለም ብንፈልገው እኚህን ሁሉንም ያሟላ አናገኝ ይሆናል። ነገር ግን አምስቱንም ባህሪያት ከተለያዩ አምስት ሰዎች ላይ ለማግኘት ሩቅ መሄድ አይጠበቅብንም።

የደራሲው ትልቁ የፈጠራ ችሎታም አምስቱን ማንነቶች ማስቀመጡ ላይ ሳይሆን፤ አምስቱንም ወደ አንድ ማንነት አምጥቶ ከታሪኩ ጋር የሚገጣጥምበት መንገድ ነው። ይህም የገጸ ባህሪያት የአሳሳል ጥበብ ልንለው እንችላለን።

እንድንወዳቸውም ሆነ እንድንጠላቸው የሚያደርገን ቁልፍ ያለው እዚህ ጋር ነው።

ለምሳሌ ለየትኛውም ሰው ሌብነት በድፍኑ ወንጀል ወይ ደግሞ ሀጢያት ነው። ስለዚህ በሁሉም ሰው ጭንቅላት ውስጥ የተሳለው የሌብነት ምስል መጥፎና አስቀያሚ ነው የሚል ነው። አንድ ደራሲ ግን የአዕምሮ ህጋችንን ሽሮ ሌባውን ገጸ ሰብ እንድንወደው ሊያደርገን ይችላል። ነብሰ ገዳይ መሆኑን እያወቅን እንድናዝንለት አልፎም እንድናለቅስለት ለማድረግም ይቻለዋል። ይህ የሆነውም ደራሲው ገጸ ባህሪውን ከታሪኩ ጋር የሳለበት ልዩ ፈጠራዊ ችሎታው ነው።

በአፈንጋጭና ወጣ ባሉ ድርጊቶች ውስጥ ሳንወድ በግድ እንድንቀበለው ያደርገናል። ሌላኛው የገጸ ባህሪያት አሳሳል ደግሞ እውነት፣ ባህል፣ ቋንቋና መሰል ማህበረሰባውያንን መሠረት በማድረግ የሚቀመጥ ነው። በመጽሐፍትና በሌላውም ውስጥ ያለ ቢሆንም በጉልህ የምንመለከተው ግን በአብዛኛው ፊልሞች ውስጥ ነው። ለአብነት ፊልሙ የተሠራው በአንድ ማህበረሰብ ቀዬ ውስጥ፣ በዚያው ማህብረሰብ የሚያጠነጥን ቢሆን፤ ገጸ ባህሪያቱ ከአለባበስና አነጋገር አንስቶ እነርሱኑ መስለው ይሳላሉ።

ከዚህ በመነሳት አንዳንድ ጊዜ ድርጊትና አነጋገር ማንነትን የሚወክል ሆኖ ይሳላል። በፊልሞቻችን ውስጥ ይህ የተለመደ ነው። አንደኛው ገጸ ባህሪ የመጣበትን ማህበረሰብ የሚገልጽ ምንም ዓይነት ነገር ሳይታይበት፣ መሀል አዲስ አበባ ውስጥ ከፎቆች ጫካ ስር ቁጭ ብሎ በአነጋገር ዘዬው ብቻ ከወዴት እንደመጣ ልንለየው እንችላለን። ታዲያ ንግግሩ ሁላችንም በምንሰማው አማርኛ እንጂ ባደገበት ቋንቋ አይደለም።

እንደገና ከሌላ ፊልም ውስጥ ሌላኛው ገጸ ባህሪ ከአንድ ሱቅ ላይ ሆኖ ብቅ ሲል ገና የሰውየውን ማንነትና ንግግሩ እንዴት ሊሆን እንደሚችል አስቀድመን እንገምታለን። ከወንዝ ወርዳ እንሥራዋን በውሃ እየሞላች ያለችውን ሴት ስንመለከት ማን እንደሆነች ግልጽ ሆኖ ይታየናል። የእብድ ገጸ ባህሪን ለማሳየት ሙሉ ለሙሉ ለማለት ጥቂት በሚቀረው መልኩ አንድ ዓይነት ገጽታ፣ አንድ ዓይነት አነጋገርና አኳኋን እንመለከታለን። ሰካራምና ፈላስፋውንም ሆነ ምሁር ፕሮፌሰሩን ለመግለጽ በአንድ ዳይሬክተርና ሜካፕ አርቲስት የተዘጋጁ ያህል ተመሳስለው ይታያሉ። ሌላው ቀርቶ ገበሬውን ገጸ ባህሪ ለማሳየት ማንን እንደምንጠቀም ሳይጻፍ በአዕምሯችን ቀርጸን የያዝነው ሕግ ያለ ይመስላል።

ይህን መሰሉ የገጸ ባህሪያት አሳሳል መጥፎ ነው ባንለውም የሚያጎድለው ነገር ግን ብዙ ነው። የመጀመሪያው ነገር በድግግሞሽ የተሞላና ተመልካችን የሚያሰለች መሆኑ ነው። ሁለተኛው ስንክሳር ደግሞ አንድን ባህል ወይንም ማህበረሰብ የወከልንበት ጽንሰ ሃሳብ የተሳሳተና ያንን ማህበረሰብ ብቻ የማይወክል ሆኖ እናገኘዋለን። አንድ ጊዜ ልንጠቀመው እንችላለን ግን በሁሉም ቦታና ጊዜ እሱኑ ብቻ መደጋገም አስፈላጊ አይደለም። እነዚህ ምክንያቶች ደግሞ ሦስተኛውን እንድንል ያስገድዱናል፤ የደራሲውንም ሆነ የዳይሬክተሩን የፈጠራ ችሎታ ያወርደዋል። ከላይ ለአብነት ያሰፈርናቸው አሳሳሎች ቀላልና ማንኛውም ተመልካች ሊያውቃቸው የሚችሉ ናቸው። ደራሲው ሲጽፍ ሌላ ምንም ዓይነት የጥናትና ምርምር ምልከታ ሳያደርግ በቀላሉ ከምናቡ ላይ የሰፈረውን ያወርደዋል። ዳይሬክተሩም በተለምዶ የሚያውቀውን ምስል ቁጭ ያደርገዋል። በአዲስ እይታ፣ አዲስ ፈጠራ ውስጥ እንዳይዋኙ፤ ባሉበት ብቻ መንቦራጨቅ ይሆናል።

የገጸ ባህሪያትን አሳሳል ጠቅለል ስናደርገው በሁለት ዋና ክፍሎች ልንመድበው እንችላለን። የመጀመሪያው ውጫዊ (አፋዊ) አሳሳል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ውስጣዊ (አዕምሯዊ) የአሳሳል መንገድ ነው። በአንደኛው መንገድ ላይ የምንመለከተው ነገር ሁሉ ግልጽና ለሁሉም ተመልካች አንድ ዓይነት ምስልን የሚሰጥ ነው። ለምሳሌ አለባበስ፣ የሰውነት ገጽታ፣ መልክና ቁመት የመሳሰሉት የሚታዩበት ነው። በውስጣዊ ወይንም አዕምሯዊ የገጸ ባህሪያት ምስል ውስጥ ብዙ ጉዳዮች በቀጥታ በዓይን ብቻ ሊስተዋሉ የማይችሉ ናቸው። ከዓይን ይልቅ ለዓይነ ህሊና የቀረቡ ናቸው። በብዛት ከአንደኛው ገጸ ባህሪ በሌላኛው የሚገለጹ ናቸው። ክፋትና ደግነት፣ ኀዘንና ደስታ፣ ርህራሄና ጭካኔ ዓይነት ስሜቶች የሚዘዋወሩበት ነው። ባልናቸው ነገሮች ሁሉ ገጸ ባህሪያትን ተነፈስናቸው እንጂ ገና ምናቸውንም አልተመለከትነውም። ከምናብ ባህር የሚወጡ ብቻ ሳይሆኑ ራሳቸውም ሌላ ባህር ናቸውና ከግዙፍ መጽሐፍ ላይ ሁለት መስመር እንደማንበብ ይቆጠር።

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

ጎሜ

# የጥፋት ምሽግን ያፈረሰው የአንካራው ስምምነት

እስማኤል አረቦ

ኢትዮጵያ ከሶማሌ ላንድ ጋር ያደረገችውን የመግባቢያ ሰነድ ተከትሎ የኢትዮጵያን እድገት እና ለውጥ የማይፈልጉ ኃይላት ጉዳዩን ከልኩ በላይ ማጦዝ ጀመሩ። ኢትዮጵያን በጠብ አጫሪነት ፈረጁ። ለቀጣናውም ስጋት መፍትሄ ነን ብለው ተከሰቱ። በሰላም አስከባሪነት አንድም ቦታ ተሰማርተው የማያውቁ ሀገራት ሁሉ የሶማሊያን ሰላም የምናስከብረው እኛ ነን አሉ። አልፎ ተርፎም የሶስትዮሽ ትብብር ፈጠርን በሚል አስመራ ላይ መከሩ፤ዘከሩ።

እነዚህ ኃይላት ኢትዮጵያ የባህር በር ካገኘች ትበለጽጋለች፤ በአካባቢውም ላይ ተጽዕኖ ፈጣሪ ሆና ትዘልቃለች የሚል ስጋት አላቸው። ከዚም ባሻገር በህዳሴ ግድብ ያጡትን ተሰሚነት በዚህኛው የማስመለስ ህልምም ያላቸው ናቸው። እነዚህ ኃይላት ምቹ አጋጣሚ አገኘን በሚል ስሜት በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ የሶማሊያ ሉአላዊነት ተጣሰ በሚል በሰላም አስከባሪነት የምረጡኝ ቅስቀሳ አካሄዱ።

ይባስ ብሎም የኢትዮጵያን የሰላም አስከባሪነት ሚናም ማሳነስ ጀመሩ፤ ሽበርተኝነት የመከላከል ሚናዋንም አንኳሰሱ፤ ለ17 ዓመታት የሶማሊያን ደህንነት እና ጸጥታን ለማስከበር የከፈለችውን መስዋዕትነት ካዱ። ይባሱኑም ኢትዮጵያ ከሰላም ማስከበር ተልዕኮው መውጣት አለባት የሚል ዘመቻ አወጁ።

እነዚህ ኃይላት አዛኝ ቅቤ አንጓች ሆነው በሶማሊያ ስም የራሳቸውን ድብቅ ፍላጎት ለማሳካት የሚጥሩ ናቸው። ሁልግዜም ቢሆን እነዚህ ኃይላት ለኢትዮጵያ ድብቅ ምሽግ የሚቆፍሩ፣ እድገቷን የሚጸየፉ፣ሀገር ለማፍረስ ለሚነሳ ሁሉ መሳሪያ የሚያቀብሉ እና ከለላ መሆን የሚፈልጉ ናቸው።

ሆኖም እነዚህ ኃይላት ዘላለማቸውን ከኢትዮጵያ ጫንቃ ላይ ባይወርዱም አንድም ቀን እንኳን ሴራቸው ተሳክቶላቸው ያሰቡት ሆኖላቸው አያውቅም።ኢትዮጵያ ከሴራቸው አልፋ በምሥራቅ አፍሪካ ተሰሚነት ያላት ሀገር ሆናለች። በቀጣናው ግዙፍ ኢኮኖሚ ከመገንባቷም ባሻገር ታላቁን የህዳሴ ግድብ ገንብታ ወደ ማጠናቀቁ ደርሳለች።

በቀጣናው ግዙፍ ኢኮኖሚ እየገነባች የምትገኘው ይህችው ሀገር በቀላሉ ሲገፏት የምትገፋ አይደለችም። እንደድሮው በዲፕሎማሲ የምትበለጥ እና በድህነት የምትገለጽ ሀገር አይደለችም። ዛሬ የፈጠረችው ተሰሚነት ከሩቅ ሆና ብትጣራ ብዙዎች አቤት የሚሏት እና ለጥያቄዋም ምላሽ የሚሰጧት ሀገር ነው የሆነችው።

የባህር በር ጥያቄዋም በአፋጣኝ መልስ ያገኘውም ለዚህ ነው። ዛሬ የኢትዮጵያ የባህር በር ጥያቄ እንዴት ይስተናገድ እንጂ ፍትሐዊነቱን የሚጠራጠር ሀገር የለም። ለዚህም ነው የቱርኩ መሪ ረሲፕ ጣሂር ኤርዶጋን ኢትዮጵያን እና ሶማሊያን ለማደራደር ቆርጠው የተነሱት። በመጨረሻም በአንካራ በተደረገ ድርድር ኢትዮጵያ እና ሶማሊያ ከስምምነት ደረሱ። ይህ አጋጣሚ ለሀገራቱ ትልቅ ብስራት ሲሆን ለጥፋት ኃይሎች ግን ከባድ መርዶ ነበር። የሶስትሽ ኃይል አቋቁመን ኢትዮጵያን እናንበረክካለን ብለው የተነሱት ኃይላት ሴራቸው የመከነበት እና የገነቡትም የጥፋት ምሽግ የፈረሰበት ታሪካዊ ዕለት ነው።

የአንካራው ስምምነት አካባቢያዊ መረጋጋት የሚያመጣና ኢትዮጵያም በቀጣናው ላይ አለኝ የምትለውን የባለቤትነት ጥያቄ መልስ እንዲገኝ በር የሚከፍት ነው። ቀጣናዊ ሰላምን በማስፈን የአፍሪካ ቀንድ አካባቢ የተረጋጋ እንዲሆን በር ይከፍታል።

በእርግጥ ከሶማሌ ላንድ የተደረገው የመግባቢያ ሰነድ ለጊዜው ከሶማሌ ሪፐብሊክ ጋር ያለመግባባት ቢፈጠርም ሰሞኑን በተደረገው የአንካራ ውይይት መግባባት ላይ ተደርሷል። በቱርኩ መሪ አደራዳሪነት በአንካራ በተካሄደው ውይይት ኢትዮጵያ ጥቅሟን አስጠብቃ መጥታለች።በዋናነትም ሶስት ጉዳዮችን አሳክታለች።

የመጀመሪያው እና ዋነኛው የኢትዮጵያ የባሕር በር ጥያቄ ተገቢ እና ፍትሐዊ መሆኑን ታምኖበታል።

**የአንካራው ስምምነት ግጭቱን ለራሳቸው ተጠቃሚነት ለማዋል ያሰቡ ሀገራትን እና በቀጣናው የሚንቀሳቀሱ የሽብር ቡድኖችን ከዓላማቸው ያደናቀፈ ድንቅ ስምምነት ነው**

ኢትዮጵያ ከ120 ሚሊዮን በላይ ሕዝብ ይዛ እና እ.ኤ.አ በ2030 ወደ 150 ሚሊዮን ሕዝብ ባለቤት ሆና፤በምሥራቅ አፍሪካ ግዙፍ ኢኮኖሚ ግንባታ እና በሚቀጥሉት ዓመታት በዓለም ላይ ከፍተኛ እድገት ከሚያስመዘግቡት ሀገራት ተርታ ተሰልፋ በአንድ ወደብ ላይ ጥገኛ ሆና መቀጠል አትችልም። ከዚህም ባሻገር በጎረቤት ፈቃድ ላይ የተንጠለጠለ ወደብ ተከራይታ መቆየት ለህልውናዋም አሳሳቢ ነው።

ስለዚህም በግፍ ከባሕር በር ይዞታዋ የተነጠለችው ኢትዮጵያ ወደ ተፈጥሯዊ ማንነቷ መመለስ አለባት።

ይህም ጥያቄዋ ፍትሐዊ በመሆኑ ከግብጽ እና መሰሎቿ በስተቀር ሁሉም ተቀብሏታል። ግብጽና መሰሎቿ ግን ቀድሞውኑ የኢትዮጵያን ውሃ ሀብት በኢ ፍትሐዊ መንገድ ሲጠቀሙ የኖሩ በመሆኑ ከእነሱ ፍትሐዊነትን አንጠብቅም።

ስለዚህም እያደገ የሚሄደውን የሕዝብ ቁጥሯን ለመመገብ እና የኢኮኖሚ ጥያቄዋን ለመመለስ የአማራጭ ወደቦች ባለቤት መሆን አለባት። ይህንን እውን ለማድረግ ደግሞ ሰላማዊ አማራጮችን እየተጠቀመች ነው።

ሆኖም የኢትዮጵያ ጥያቄ መልስ እንዳያገኝ የሚመኙ እና በህዳሴው ግድብ የተሸነፉ ሀገራት ጉዳዩን የተለየ መልክ በመስጠት በሰላም አስከባሪ ስም ምሥራቅ አፍሪካ ድረስ በመምጣት ቀጣናውን የግጭት ማዕከል ለማድረግ እየጣሩ ነው።

እንደ ኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር 2003 ላይ ጅማሬው የተበሰረው የዓባይ ግድብ ከ15 ዓመታት በኋላ ወደ ፍጻሜው ተቃርቧል። ሆኖም ግድቡ የመሰረት ድንጋይ ከተጣለበት ጊዜ አንስቶ እስካሁኗ ሰዓት ድረስ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ኢትዮጵያ ግድቡን እንዳታጠናቅቅ በብዙ ተደክሟል።

በተለይም የኢትዮጵያ፣ ግብጽና ሱዳን የሶስትዮሽ ድርድር ሁሌም እንከን እንዲኖረው በግብጽ በኩል በብርቱ ሲሠራበት ሰንብቷል። ከመነሻው ጀምሮ ኢትዮጵያ በዓባይ ወንዝ ላይ ምንም አይነት የልማት ሃሳብ እንዳይኖራት ለዘመናት ስትባዝን የኖረች ግብጽ፣ የሕዳሴ ግድቡ የመሠረት ድንጋይ ሲቀመጥ በኢትዮጵያ ላይ የማስፈራሪያና የማስጠንቀቂያ ዶፍ ስታዘንብ መክረሟ የሚታወቅ ነው።

ከማስፈራራትና ከያዙኝ ልቀቁኝ በኋላ ዶሴዋን በመያዝ፤ ‘ሲሆን ሲሆን ግድቡ እንዳይገነባ በማድረገው ጥረት ከጎኔ ይቆማሉ፤ ካልሆነም ኢትዮጵያ ላይ ጫና ያሳድሩልኛል’ ወዳለቻቸው አካላትም፣ሀገራትም ዘንድ ተንከራትታለች። ይሁንና ኢትዮጵያ በግብጽ ግልምጫም ሆነ ዛቻ እንዲሁም በሌሎቹ ሀገራት ጫና ከአቋሟ ዝንፍ ሳትል ግንባታዋን ሌት ተቀን ስታስኬደው ከርማለች።

ነገር ግን በዚህ ሁሉ ውስጥ ያጋጠማት ፈተና በርከት ያለ ከመሆኑም በላይ በየምክንያቱ ብዙ ነገሮችን እንድታጣ ተደርጋለች። በአንድም ሆነ በሌላ ምክንያት ኢኮኖሚዋ እንዲዋዥቅ በብዙ ተጥሯል። ምክንያቱ ሌላ ይምሰል እንጂ በሀገር ቤትም ሆነ በውጭ ሀገር ባሉ ዜጎቿ ጫና ተፈጥሯል።

ግብጽ የሕዳሴ ግድቡን ወደ ጸጥታው ምክር ቤት በማመላለስ ኢትዮጵያ በብዙ ጫና ውስጥ እንድታልፍ ከማድረጓም በተጨማሪ ሐሰተኛ በሆነ መረጃዋ፤ አንዳንድ አቅላቸውን በሳቱ አካላት ግድቡ በቦንብ እንዲጋይ እስከማሰብ ተደርሷል። ስለ ዓባይ ግድብ ምንም የማያገባው የአረብ ሊግም በጉዳዩ ላይ ተደጋጋሚ መግለጫ እስከማውጣት ደርሷል።

ከዚህ በሻገርም በሀገር ውስጥ ጭምር ሰዎችን በገንዘብ በመግዛት ሁከትና ረብሻ እንዲስፋፉ እና ኢትዮጵያ እንድትፈራርስ በብዙ ተደክሟል። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ.ር) ሰሞኑን እንደተናገሩት፤ ከሞላ ጎደል 15ሺ የሚሆኑ በገንዘብ የተገዙ ሰዎች የህዳሴውን ግድብ ለማስተጓጎል በኢትዮጵያ ተሰማርተው ነበር። እነዚህ ሰዎች በየሚዲያው በመውጣት፣በየማህበራዊ ሚዲያውና በዩቱዩብ በመገኘት ያልተቋረጠ አሉባልታና ስም የማጥፋት ዘመቻ ሲያደርጉ ቆይተዋል፤ አሁንም በማድረግ ላይ ይገኛሉ።

በአጠቃላይ የዓባይ ግድብ ከዳር እንዳይደርስ የውጭና የውስጥ ኃይሎች ሲያደርሱት የነበረውን ተጽዕኖ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እንደሚከተለው ገልጸውት ነበር። «ሲሚንቶ ከማምረት አጓጉዞ እዚህ ቦታ እስካለው ሥራ 15 ሺህ የሚጠጋ የተለያየ ስም ያላቸው በመነሻነት የኛ የሆኑ፤ ግን የተገዙ ፣ የተሸጡ ሰዎች ይሄ ሥራ አሁን ያለበት ደረጃ እንዳይደርስ፣ እንዳይቋጭ ብዙ ጊዜ እና ገንዘብ እና ሕይወት አጥፍተዋል።

ሁልጊዜም ቢሆን የኢትዮጵያ ሕዝብ እና መንግሥት የሚያነሱት ጥያቄ ፍትሐዊ ነው። ስለዚህም ይህንን ፍትሐዊ በአግባቡ ከመመለስ ውጪ አማራጭ የለም። ኢትዮጵያውያን ያነሱት ትክክለኛ የመልማት እና የማደግ ጥያቄ በመሆኑ እነዚህን ጥያቄዎች በጭራሽ ማስቆም እንደማይቻል በአንካራው ድርድር በይፋ ታይቷል።

በአንካራው ድርድር ኢትዮጵያ ያሳካችው ሁለተኛው ጉዳይ ከሶማሌላንድ ጋር የተፈረመው የመግባቢያ ሰነድ የሚቀደድ አለመሆኑ ነው። ኢትዮጵያ ከሶማሌ ላንድ ጋር የፈረመችው የመግባቢያ ሰነድ ባለበት እንዲቀጥል ስምምነቱ አካቷል። ኢትዮጵያ እና ሶማሌ ላንድ ታኅሣሥ 23 ቀን 2016 ዓ.ም የመግባቢያ ሰንድ ተፈራርመዋል። ሰላማዊ አማራጭን ሲከተል ቆየው የኢትዮጵያ መንግሥት ሰሞኑን ከሶማሌ ላንድ ጋር የባሕር በር የሚገኝበትን መግባቢያ ሰነድ (Memorandum of understanding) ተፈራርሟል።

ይህ የመግባቢያ ሰነድ ሲተገበር አካባቢያዊ መረጋጋት የሚያመጣና ኢትዮጵያም በቀጣናው ላይ አለኝ የምትለውን የባለቤትነት ጥያቄ መልስ እንዲገኝ በር የሚከፍት ነው። ቀጣናዊ ሰላምን በማስፈን የአፍሪካ ቀንድ አካባቢ የተረጋጋ እንዲሆን በር ይከፍታል።

በአጠቃላይ ኢትዮጵያ እና ሶማሊያ ያደረጉት ስምምነት ከሁለቱ ሀገራት ባሻገር ለሌሎች የቀጣናው ሀገራት እና ለቀጣናው ሰላም ትልቅ እፎይታ ነው። በተለይም በድርቅ፣ በጦርነት ፣በሕገወጥ ስደት ፣ በሽብር የመሳሰሉት መለያው የሆነው የምሥራቅ አፍሪካ አካባቢ ተጨማሪ ጦርነት እና ግጭት የሚያስተናግድበት አቅም የለውም። ከዚህ እውነታ ባፈነገጠ መልኩ አካባቢውን ወደ ተጨማሪ ቀውስ ለመውሰድ የሚደረጉ ሙከራዎች ከቀጣናው አልፎ ዓለም አቀፍ ስጋትም የሚፈጥር ነው። ስለዚህም የአንካራው ስምምነት ግጭቱን ለራሳቸው ተጠቃሚነት ለማዋል ያሰቡ ሀገራትን እና በቀጣናው የሚንቀሳቀሱ የሽብር ቡድኖችን ከዓላማቸው ያደናቀፈ ድንቅ ስምምነት ነው።

በቀጣይም ስምምነቱ ውጤታማ እንዲሆን ያሉ ችግሮችን እየነቀሱ በመፍታት፣ ሀገራቱ መተማመን ላይ የተመሰረት ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት እንዲኖራቸው መሥራት ይገባል። የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት፣ በቀጣናው የሚንቀሳቀሱ የሽብር ቡድኖችን ጥቃት የመከላከል እና የቀጣናው መረጋጋት ላይ ትኩረት አድርጎ መሥራትም ያስፈልጋል።

ስምምነቱ ኢትዮጵያንም ሆነ ሶማሊያን በእጅጉ ያስደሰተ ነው። የሶማሊያ ፕሬዚዳንት ሀሰን ሼክ ሙሃመድ የአንካራው ስምምነት በተፈረመበት ወቅት፤ የምሥራቅ አፍሪካ ቀጣና ለችግር ተጋላጭ በመሆኑ በትብብር ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ወሳኝ መሆኑን ገልጸዋል። አያይዘውም የኢትዮጵያ ወታደሮች ለሶማሊያ ሰላም የከፈሉት መስዋእትነት አይዘነጋም በማለት፤ በቀጣይም ሶማሊያ የኢትዮጵያ ጥሩ ወዳጅ ሆና ትቀጥላለች ማለታቸው ይታወሳል።

በአሁኑ ወቅት 120 ሚሊዮን ሕዝብ በ2050 አካባቢ ደግሞ በእጥፍ የሚያድግ ሕዝብ ተይዞ "ስለቀይ ባሕር እና ስለ ወደብ አታንሳ፤ ዝም ብለህ ተቀመጥ" የሚለው አፋኝ አመለካከትም እየተሰበረ ይገኛል። በምትኩም የኢትዮጵያ ጥያቄ ተቀባይነት እያገኘ እና በሰጥቶ መቀበል መርህ እየተመራ ዛሬ ላይ ደርሷል።

ሶማሊያ በሺዎች ኪሎ ሜትር የሚቆጠር የባሕር በር አላት። ግን ይህ ሁሉ ኪሎ ሜትር ለሶማሊያ ወደብ ሆኖ ሊያገለግል የሚችል አይደለም። ስለዚህም ሶማሊያ ከኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ተጠቃሚ ለመሆን ከፈለገች ወደብ ከኢትዮጵያ ጋር ማልማት ትችላለች። ወይንም ደግሞ ለም መሬት ወስዳ በምትኩ ወደብ ልታቀርብልን ትችላለች። ብቻ አማራጩ ብዙ ነው።

ዘይላ ሶማሊያ እንደሀገር ከመፈጠሯ በፊት ኢትዮጵያ የምትጠቀምበት የባሕር በር ነው። ከዛግዌ መንግሥት ጀምሮ ኢትዮጵያ በወደቡ ስትጠቀም ኖራለች። ለኢትዮጵያ ቅርበት አለው። ከሞቃዲሾ በርካታ ኪሎ ሜትሮችን የሚርቅ ስለሆነ ሶማሊያ ልትጠቀምበት አትችልም። ስለዚህም መነጋገር ከተቻለ በቅርብ ርቀት ላይ የሚገኘውን የዘይላን ወደብ ኢትዮጵያ ብትጠቀምበትና ሶማሊያም በምትኩ ጥቅም ብታገኝ ሁለቱም ሀገራት አሸናፊ መሆን ይችላሉ። የአንካራውም ስምምነት የሚያረጋግጠውም ይህንኑ ነው።

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ነፃ ሃሳብ



ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።


በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com


# አመድ አፋሽ እያደረገ ያለው ሕገ ወጥ ደላላና ኬላ

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ካሳሁን ጎፌ (ዶ/ር) በሰሞኑ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ማብራሪያቸው፤ የግብይት ሥርዓቱን በማበለሻሸት ትልቅ ድርሻ የያዘውን የደላሎች ጣልቃ ገብነት ለመቀነስ እየተደረገ ያለው ጥረት ገልጸዋል። የደላሎች እጅ ረዥም በመሆኑ በዚህ ጉዳይ ላይ የተሠራውና እየተሠራ ያለው ሥራ መልካም ቢሆንም አሁንም ገበያው ከሕገወጥ ደላሎች እጅ አልወጣም። አሁንም የደላሎች ጡንቻ ፈርጥሞ የሚታይበት አካባቢ ስላለ በዚህ ረገድ ተጀመሩ የተባሉ የሕግ ማስከበርና ዕርምጃዎች በያዝ ለቀቅ ሳይሆን ባልተቋረጠ መንገድ ከተሄደበት ለውጥ ሊመጣ ይችላል ብለዋል።

በገበያ ውስጥ የምርት እጥረት እንዲፈጠርና የዋጋ ንረትን የሚያባብሱ ናቸው ብለን ከምንጠቅሳቸው ውስጥ ምርት በመሸሸግና ጊዜ ጠብቆ ያልተገባ ትርፍ ለማግኘት የሚደረግ ጥረት አንዱ ነው። የኮንትሮባንድ ንግድ፣ የደላሎች ጣልቃ ገብነትና የመሳሰሉ ሁኔታዎች ለገበያ ያለመረጋጋት ምክንያት ስለመሆናቸው በተደጋጋሚ የሚጠቀስ ነው። የብር የመግዛት አቅም መዳከምና ሌሎች ለዋጋ ንረት ምክንያት ናቸው የሚባሉ ሰው ሠራሽ ውንብድናዎችም ችግሩን በማባባስ የየራሳቸው አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ይለናል የአማርኛው ሪፖርተር ጋዜጣ።

እስካሁን ከምንሰማቸው ሕገወጥ ተግባራትና የተለመዱ ተግዳሮቶች ባሻገር ሕገወጥ የተባሉ ኬላዎች እየተፈጸሙ ነው የተባለው ችግር ደግሞ በግብይት ሥርዓቱ ውስጥ አዲስ ተግዳሮት ሆኖ መጥቷል። ሰሞኑን የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተገኝው ስለመሥሪያ ቤታቸው የሥራ አፈጻጸም ገላጸ ካደረጉት የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትሩ ስለሕገወጥ ኬላዎች የተናገሩትና ችግሩንም ለማስቆም የተቸገሩ መሆኑን የገለጹበት መንገድ የሁኔታውን አሳሳቢነት አመላክቷል።

ሕገወጥ በተባሉ ኬላዎች ዙሪያ የሰጡትን ማብራሪያ ቃል በቃል እንዲህ የሚል ነበር። ‹‹አሁንም የቀረጥና የኬላ ችግር አንገብጋቢ መሆኑን ይህ ምክር ቤት እንዲገነዘብ እንፈልጋለን። እስከ ትናንትናው ድረስ በኢትዮጵያ ኬላ ይነሳ ተብሎ በመንግሥት ደረጃ ቢወሰንም የተለያዩ ሰበባሰበቦች እየተፈለጉ 283 ሕገወጥ ኬላዎች በመላ አገሪቱ ተንሰራፍተው ይገኛሉ። እነዚህ ኬላዎች በሙሉ የምርት ነፃ ዝውውርን የሚገድቡ የሎጀስቲክስ ቅልጠፋውን የሚገድቡ በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ጫና ያላቸው መሆኑን ፓርላማውም አውቆ በራሱ ትግል ማድረግ አለበት ብዬ አስባለሁ። በእኛ በኩል ለሚመለከታቸው አካላት አሳውቀናል። ዕርምጃ ይወሰዳል ብለን እናስባለን።

ኬላ ተነስቷል ይባላል ግን በዚህ በኩል ደግሞ ቺንጋ ይወጠራል። በእኛ በኩል ያደረግነው ጥናት ድሬዳዋን ጨምሮ በሁሉም ክልሎች 283 [ኬላ] ውጠራ ያለበት ሁኔታ ነው ያለው። ይኼ ሲነሳ ነው እንግዲህ የዋጋ ንረት የሸቀጦች ዋጋ ሊቀንስ የሚችለው እንጂ በየጣቢያው ዋጋ የሚጨምሩ ኑሮ የሚያባብሱ ጉዳዮች እየተቀመጡ ሊሆን አይችልም። በእኛ በኩል የተቻለንን እያደረግንና ጥናቱን ከጉምሩክ ኮሚሽን ጋር በጋራ ሆነን ነው ያጠናነው። ይህ ጥናት ቦታ አለው። መረጃ አለው። የሚታወቅ ጉዳይ ነው፤›› በማለት ይህንን ከአቅም በላይ የሆነባቸውን ችግር ለመቅረፍ ፓርላማውም እንዲተባበር የጠየቁበት ነበር።

የኢትዮጵያ ፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት በአንድ ወቅት ይፋ ባደረገው ጥናት ምርት ሸማቹ ጋ የሚደርሰው እስከ 60 በመቶ ዋጋ ተጨምሮበት ይላል። ሸማቹ ላይ ያልተገባ የዋጋ ጭማሪ እያስከተሉ ካሉ የግብይት ችግሮች አንዱ በመላ ሀገሪቱ የተወጠሩና የተዘረጉ ሕገ ወጥ የገመድ ኬላዎች ናቸው። የዚህ ዋጋ ጭማሪ ሌላው ምክንያት ምንም እሴት የማይጨምረው ደላላ ነው። አምራቹ ባመረተው ምርት ተጠቃሚ ካለመሆኑ ባሻገርም ሸማቹ ላልተገባ የዋጋ ጭማሪ ይዳረጋል።

በአገራችን የኑሮ ውድነትና የዋጋ ግሽበት ተጀምለው የአብዛኛውን ኢትዮጵያዊ የዕለት ተዕለት ኑሮ ፈተና እያደረጉት ነው።ዳሩ ግን ከአምራቹና ከሸማቹ ቁጥር የማይተናነሰው ደላላ ገበያውን አንቆ አላላውስ ከማለት አልፎ በመዳፉ ስር ማድረጉ በእንቅርት ላይ ቆረቆር ሆኗል።መንግስት የኑሮ ውድነቱን ለማርገብ የሚያደርገው ጥረት በሕገ ወጥ ደላላ የተነሳ አመድ አፋሽ እያደረገው ነው። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርም ሆነ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ሕገ ወጥ ደላላን ከግብይት ሰንሰለቱ ለማስወጣት ያግዛል ያሉትን መመሪያ ቢያዘጋጁም ወደ ሥራ ስላልገባ ችግሩ ተባብሶ ቀጥሏል። በነጻ ገበያ ስም ገበያው ስድ መለቀቁና የትርፍ ሕዳግ አለመወሰኑ ሌላው ችግር ነው።

የአገራችን ኢኮኖሚ በአዳም ስሚዝ የኢኮኖሚክስ ሀ ሁ በፍላጎትና አቅርቦት ሳይሆን በደላላ የሚዘወር ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። ገበያው ካለበት መዋቅራዊ ችግር ባልተናነሰም በገበያው የሕግ የበላይነትን የማረጋገጥ ክፍተት መኖሩ ችግሩን አወሳስቦታል። በዓለማችን ባልተለመደና ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ በአገራችን የተሰገሰገው ደላላ በገበያውና በኢኮኖሚው ላይ አዛዥና ናዛዥ ሆኗል። ደላላው በመንግሥት ውስጥ ያለ ሌላ የገበያ መንግሥት ሆኗል። ምንም አይነት ጊዜያዊና ዘላቂ መፍትሔ ቢቀመጥ ደላላውን ከኢኮኖሚ መዋቅር ማስወጣትና በሕግና በሥርዓት እንዲመራ ካልተደረገ ከዚህ የዋጋ ግሽበትና የኑሮ ውድነት አዙሪትና ቀለበት ሰብሮ መውጣት አይቻልም።

በእያንዳንዳችን ሕይወት አዛዥ ናዛዥ የሆነው "ድለላ!?" የቃሉ ትርጉም ምን ማለት ይሆን!? ምንም እንኳ በሥነ ልሳን አስተምህሮ በስያሜውና በተሰያሚው መካከል የባህሪ ግንኙነት እንደሌለ ቢበየንም፤ የቃሉ ግብርና ምግባር ስለተማታብን፣ ስለተጣረሰብን ትርጉሙን እንመልከት። የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል በ1993 ዓ.ም ያዘጋጀው የአማርኛ መዝገበ ቃላት፤ "ደላላ"ን፡- 'ገንዘብ እየተከፈለው ተፈላላጊዎችን (ሻጭና ገዥን፣ አከራይና ተከራይን፣...) አገናኝ፣ አስማማ፤' በማለት ይተረጉመዋል።

በመደለል ሥራ ላይ የተሰማራ ሰው፤ አታላይ፣ በውሸት አግባብቶ ለማሳመን የሚሞክር፤ "ድላል"ን ደግሞ ለደላላ የሚከፈል ገንዘብ በማለት ይተረጉማል። የደስታ ተክለወልድ ዘሀገረ ወግዳ በ1970 ዓ.ም የአማርኛ መዝገበ ቃላት ደግሞ፤ ደለለ፡- አሞኘ፣ አታለለ፣ ሸነገለ፣ የማያደርገውን አደርጋለሁ አለ፤ ደላላ፡- አመልካች፣ ጠቋሚ፤ ድላል፡- ለጠቋሚ፣ ላስማሚ የሚሰጥ ገንዘብ ሲል ይተረጉመዋል። ይሄኛው ትርጉም ከቀደመው ይልቅ የአገራችንን ደላላ ቁልጭ አርጎ ይገልፀዋል።

የእንግሊዝኛውን ትርጉም 'broker' ስረወ ቃል ስንመለከት "brocour" ከሚለው የፈረንሳይኛ ቃል የመጣ ሲሆን፤ ከ14ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የቋንቋው አካል መሆኑን ሜሪያም ዌቢስተር የእንግሊዘኛ መዝገበ ቃላት ያወሳና ትርጉሙም፡-{bro·ker: a person who helps other people to reach agreements, to make deals, or to buy and sell property (such as stocks or houses)} ነው ይለናል። የአማርኛውም ሆነ የእንግሊዘኛው መሰረታዊ ትርጉም ተቀራራቢ ቢሆንም፤ "ድለላ" ሲነሳ አብሮ ማታለል፣ መሸንገል፣ ማሞኘት፣ በውሸት አግባብቶ ማሳመን፤ የሚሉ አሉታዊ አንድምታዎች ግዘፍ ከመንሳት አልፈው "ድለላ" በተነሳ ቁጥር ቀድመው ወደ አዕምሯችን የሚመጡት እነዚህ አሉታዊ ብያኔዎች ናቸው። በአገራችን ያለውን አብዛኛውን ደላላም ይገልፁታል ተብሎ ይታመናል። ሆኖም እጅግ ያነሱና በጣት የሚቆጠሩ ቢሆኑም ታማኝ፣ ሀቀኛና መልካም ሥነ ምግባር ያላቸው ደላሎች መኖራቸው ግን ሊዘነጋ አይገባም።ድለላ ማኀበራዊና ኢኮኖሚያዊ መስተጋብሮችን ሳይቀር እንዴት እያወከ እንደሆነ ላነሳሳ፤

1.**ኢኮኖሚያዊ**፡-ኢኮኖሚያችን ከሌሎች አገራት ለየት ያደርገዋል ብዬ ከማምንባቸው ግርምቶች ቀዳሚው፤ በአዳም ስሚዝ የኢኮኖሚክስ ሀ ሁ ዝቅተኛ መስፈርት በሆኑት ፍላጎት/ demand እና አቅርቦት/supply አለመዘወሩ ነው። ከጉልት እስከ ጅምላ ንግድ፣ ከጎጥ እስከ ፌዴራል፣ ከሸንኩርት ማሳ እስከ አትክልት ተራ፣ ከሚዛን ተራ እስከ እህል በረንዳ፣ ከአንድ ክፍል ጭቃ ቤት እስከ ተንጣለለ ቪላና ፎቅ፣ ከአንድ ጥማድ መሬት እስከ ጋሻ መሬት፣ ከአራጣ ብድር እስከ ባንክ ብድር፣... ከታች እስከ ላይ በተሰገሰጉ ህልቁ መሳፍርት ደላሎች ሳምባ የሚተነፍስ ኢኮኖሚ መሆኑ ነው።

አንድ ወዳጄ በዚያ ሰሞን እንዳጫወተኝ ከሆነ ከለውጡ በፊት የደላላ እጅ ሀይ ባይ በማጣቱ እረዝሞ እረዝሞ አገራችን በምትፈርማቸው ብድርና እርዳታ ሳይቀር ፈርቅ እስከመያዝ ደርሶ ነበር። እግራችን እስኪቀጥን ብንዞር የደላላ እጅ ያልገባበት የኢኮኖሚ ዘርፍ የለም። ከላይ ከትርጉሙ እንደተመለከትነው የድለላ ሥራ ሻጭና ገዥን ማገናኘት ለዚህም ድላል (የአገልግሎት ክፍያ) መቀበል ቢሆንም፤ የአገራችን ደላላ ግን በዓለም ታይቶም ተሰምቶም በማያውቅ ሁኔታ ዋጋ ቆራጭ፣ ተማኝ፤ ገበያ መሪ እስከመሆን ደርሷል።

አሁን ያለው የእህል፣ የአትክልት፣ የሸቀጣ ሸቀጦች ዋጋ፤ የመኪና የንግድም ሆነ የኪራይ ቤት ክፍያ፣ የመሬት ዋጋ፣... የተቆረጠው፣ የተተመነው በገበያ ሳይሆን በደላላ ነው። በዚህም ገበያ አመጣሽ ሳይሆን፤ ደላላ ዘራሽ የኑሮ ውድነትና የዋጋ ግሽበት አስከትሏል። በዚህ የተነሳ ዜጋው በኑሮ ውድነት ፍዳውን እያየ ነው። የሸቀጡ፣ የምርቱ፣ የአገልግሎቱ አምራች፣ አቅራቢም የሚገባውን ጥቅም እያገኘ አይደለም።

ከሸማቹም፣ ከሻጩም በሁለት ቢላዋ እየበላ ያለው ሕገ ወጥ ደላላው ነው። ዛሬ በመላው አገራችን ያሉ አርሶ አደሮችም ሆኑ አርብቶ አደሮች በተደጋጋሚ የሚያነሱት ጥያቄ የገበያ ትስስር እንዲፈጠርላቸው የሚወተውቱ ናቸው። ለገበያ ከሚቀርቡ እንስሳትም ሆነ ተዋጽኦ ተገቢውን የድካማቸውን ዋጋ እንዲያገኙ ሲወተውቱ፣ ሲማፀኑ በየሚዲያው ብንሰማም፣ ብንመለከትም መፍትሔ ባለማግኘታቸው ዋጋ የሚቆርጥላቸው ደላላው ነው። በምርቱ ተጠቃሚዎች እነሱ ሳይሆን ደላላው ነው። አርባ ምንጭ ገበሬው ኪሎ ሙዝ 20 ብር ባልሞላ ዋጋ እንዲሸጥ፤ አዲስ አበባ ላይ ደግሞ 60 ብር እንዲሸጥ የወሰነው ገበሬው ሳይሆን ደላላ ነው። አርሶ አደሩም ሆነ አርብቶ አደሩ የድካሙ፣ የላቡ ተጠቃሚ ካለመሆኑ ባሻገር፤ ደላላ አመጣሽ የሆነው የዋጋ ግሽበትና የኑሮ ውድነት የኢኮኖሚውን ወደለየለት ቀውስ እያንደረደረው ነው።

ሕገ ወጥ ደላላው ያለ አዛዥ ናዛዥ ገበያውን በብቸኝነት መቆጣጠሩ፤ መንግሥት በነፃ ኢኮኖሚ ስም መነሻ ዋጋ ወይም ጣራ ተመን እና የትርፍ ሕዳግን /profit margin/ አለመወሰኑ፤ ከሕገ ወጥ ደላላው ጋር እሳትና ጭድ ሆኑ የኑሮ ወድነቱን እያቀጣጠለ፤ በዜጋው ላይ ብሶትን፣ ምሬትን ተስፋ መቁረጥን እየከዘነ ይገኛል። በዓለማችን የነፃ ገበያ አባት የምንላቸው ምዕራባውያን ሳይቀሩ የትርፍ ሕዳግንም ሆነ የመነሻ ዋጋ ደረጃን እየወሰኑ፤ ገበያውን እየተቆጣጠሩ ባለበት፤ እኛ ለዛውም ያልሰለጠነውን ኢኮኖሚ ስድ መልቀቃችን ዛሬ ለምንገኝበት የኑሮ ውድነት ዳርጎናል።

2.**ማሕበራዊ**፡-ባለፉት ዓመታት ምሳሌ፣ አርዓያ የሚሆን ቤተሰብ፣ ተቋም፣ መሪ በየደረጃው አለመፈጠሩ፤ የግብረ ገብ ትምህርት አለመሰጠቱ፤ ፈሪአ እግዚአብሔር (ፈጣሪ) ያለው ትውልድ አለመታነፁ ዛሬ ለምንገኝበት የማሕበራዊ ቀውስ አፋፍ አድርሶናል። ውሸት፣ ሌብነት፣ ዘረፋ፣ ማጭበርበር፣ መካድ፣ ጥሎ ማለፍ፣... ነውር መሆናቸው ቀርቶ የሚያሸልሙበት ጊዜ ላይ ደርሰናል። የዚህ ትውልድ፣ ማሕበራዊ ቀውስ ውጤት የሆነው አብዛኛው ደላላም መዋሸትን፣ ማታለልን፣ በአቋራጭ መክበርን ሙያ እስከማድረግ ተግቷል። ገንዘብ እስካገኘ ድረስ ለዜጋው ለወገኑ ደንታ ቢስ ሆነ። እህት ወንድሞቹን በማይጨበጥ ተስፋ እየደለለ ለስደት፣ ለመከራ ዳርጎ በበርሀ፣ በባህር አለቁ። በአረመኔዎች እጅ ወድቀው የአካላቸውን ክፍል አጡ። ሕገ ወጥ ድለላው በዚህ የሚያበቃ አይደለም።

በአገራችን እየተስፋፋ በመጣው የወሲብ ንግድም ግንባር ቀደም ተዋናይ ነው። ለአቅመ ሔዋን ያልደረሱ ልጃገረድ ሕፃናትን ሳይቀር ለሕገ ወጥ የወሲብ ንግድ እስከማቅረብ፣ የዩኒቨርሲቲ ሴት ተማሪዎችን ለዚህ ሕገ ወጥ ተግባር እየመለመለ የፎቶ አልበም አዘጋጅቶ የሚያቀርብ አረመኔ ደላላ በየዩኒቨርሲቲዎቻችን በሮች ማግኘት እየተለመደ መምጣቱ የአደባባይ ሚስጥር ነው። ዛሬ ዛሬ ደግሞ አዲስ የድለላ ዘርፍ ማለትም ስለ የማህፀን ኪራይ /surrogacy/ ደላሎች መስማት ከጀመርን ውለን አደርን፤ ልጅህን ለልጄ ማለት እየቀረ ተጋቢዎች ራሳቸው ወስነው ትዳር መመስረት እየተለመደ ቢመጣም፤ አሁን ሶስት ጉልቻ በደላላም ተጀምሯል። ምን አለፋችሁ ድለላ ያልገባበት የሕይወታችን ቅንጣት የለም።

በእንቅርት ላይ እንዲሉ በተለያዩ ገፊ ምክንያቶች እየተሸረሸረ በመጣው ማሕበራዊ ተራክቦ ላይ ሥነ ምግባር የሌለው ሕገ ወጥ ደላላ በአናቱ ተጨምሮበት ቀውሱን እያባባሰው ነው።

ራሳቸውን ሕጋዊ ብለው የሚጠሩትም ሆነ ሕገ ወጥ ደላላዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ በዜጋው፣ በአገሪቱ ላይ እያሳደሩት ያለውን አሉታዊ ዘርፈ ብዙ ተፅዕኖ ለማስወገድ መንግሥት የዘነጋውን፣ ችላ ያለውን ኃላፊነቱን ዛሬ ነገ ሳይል መወጣት ሊጀምር ይገባል። በድለላ የሚዘወረው ኢኮኖሚ ግንባር ቀደም ገፈት ቀማሽ የሆነው ሸማች፣ ሕዝብም ኢኮኖሚውን ከድለላ ምርኮ ነፃ ለማውጣት የድርሻውን ማበርከት ይጠበቅበታል። የኢፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የችግሩን አሳሳቢነት በመገንዘብ የሚመለከታቸው የመንግሥት መስሪያ ቤቶችን መጠየቅና ከጥልቅ እንቅልፋቸው መቀስቀስ ይጠበቅበታል። የዘርፉ ልሒቃንም የአደጋውን ስፋት በጥናት ተንትነው ሊያስረዱ ይገባል።

ከዚህ ጎን ለጎን መንግሥት በየደረጃው ከጎጥ እስከ ፌዴራል፣ ከሸንኩርት፣ ከቲማቲም እስከ ጅምላ ንግድ ገበያውን፣ የንግድ ሥርዓቱን በኔት ወርክ ተደራጅቶ እያተራመሰ ያለውን ሕገ ወጥ የድለላ ኃይል ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በቃህ!!! ሊለው ይገባል። መንግሥት በአጭር ጊዜ መሰረታዊ ሸቀጦችን አገልግሎቶችን ሙሉ በሙሉ ከደላላ ነፃ በማድረግ፤ ሸማቹና ሻጩ ያለደላላ በገበያ ሥርዓት በቀጥታ እንዲገበያዩ መደላደሉን ሊፈጥር ይገባል። ከዚህ በመቀጠል የገበያ ሰንሰለቱን ከሕገ ወጥ ደላላ መዳፍ ፈልቅቆ ነፃ አውጥቶ ሕግን ማስከበር ይጠበቅበታል። በመቀጠል ሕጋዊ ደላላው የሚገዛበት ሕገ ደንብ እና እንደአስፈላጊነቱ የሥነ ምግባር መመሪያ ሊዘጋጅ ይገባል። የደላላ ክፍያና ድለላ የሚፈቀድባቸውና የሚከለከልባቸው ምርቶችና አገልግሎቶች በሕግ በማያሻማ ሁኔታ መለየት አለባቸው።

ሻሎም ! አሜን።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## የፋይናንስ ዘርፉን ለውጭ ኢንቨስትመንት ክፍት ያደረገው አዋጅ

በኃይሉ አበራ

የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከትናንት በስቲያ በአካሄደው 11ኛ መደበኛ ስብሰባው የፋይናንስ ስርዓቱን ለማሳለጥ የሚያግዝ የብሄራዊ ባንክ ረቂቅ አዋጅን እንዲሁም የውጭ ባንኮች በሀገር ውስጥ ገብተው እንዲሰሩ የሚፈቅደውን የባንክ ሥራ ረቂቅ አዋጅን መርምሮ አጽድቋል፡፡ የብሄራዊ ባንክ አዋጁ በሙሉ ድምጽ፣ የባንክ ሥራ አዋጁ በሶስት ታቃውሞ በአብላጫ ድምጽ ጸድቀዋል፡፡

ረቂቅ አዋጆቹ ከመጽደቃቸው በፊት ማብራሪያ የተሰጠባቸው ሲሆን፣ ከምክር ቤቱ አባላትም ጥያቄዎች ቀርበው በሚመለከታቸው አካላት ምላሽ ተሰጥቶባቸዋል፡፡ በወቅቱም ምክር ቤቱ መርምሮ ያጸደቀውን የብሄራዊ ባንክ ረቂቅ አዋጅን በተመለከተ የምክር ቤቱ የፕላን፤ በጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ዶክተር ደሳለኝ ወዳጄ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ረቂቅ አዋጅን ሪፖርት እና የውሳኔ ሃሳብ ለምክር ቤቱ ባቀረቡበት ወቅት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ረቂቅ አዋጅ ባንኩ ዋጋን ለማረጋጋት፤ ጤናማ የፋይናንስ ስርዓት ለማስፈንና ለኢኮኖሚው ዕድገት መፋጠን እና ተልዕኮውን በአግባቡ ለመወጣት እንደሚረዳው አስረድተዋል፡፡

የሀገርን ኢኮኖሚ ለማሻሻል ምርታማነትን ለማሳደግ፣ ቁጠባና ኢንቨስትመንትን ለማጠናከርና ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርሞችን ለመተግበር እንደሚያግዝ አስገንዝበዋል፡፡

የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ እንዳብራሩት፤ የሀገሪቱ የባንክ ዘርፍ ለውጭ ባለሀብቶች ዝግ ሆኖ ቆይቷል። የውጭ ባንኮች በመስኩ እንዲሰማሩ ባለመፈቀዱ በሀገር ውስጥ ባንኮች መካከል ፈጠራ የታከለበት እና በአዳዲስ አገልግሎቶች የታገዘ ውድድር አነስተኛ ሆኗል፤ ከውጭ ገበያውና ኢኮኖሚው ጋር ያለው ትስስር ዝቅተኛ በመሆኑ ባንኮች ብድርና የውጭ ምንዛሪ በሚፈለገው መጠን ማቅረብ አልቻሉም።

የባንክ ዘርፉ ዘመናዊ የሆነ የአሠራር ሥርዓትን ያልተከተለ፣ ወቅቱን ያልዋጀ፣ ብቃትን፣ ጥራትንና ውጤታማነትን ያላማከለ የተደራሽነት ውስንነት፣ የግለሰቦችንና የተቋማትን ፍላጎት መሠረት ያደረጉ አገልግሎቶች እጥረት፣ የፋይናንስ ገበያ መሠረተ ልማት ውስንነት ያለበት፤ ከባንክ ሥራ ዕውቀት፣ ክህሎት፣ ልምድና ከቴክኖሎጂ አጠቃቀም አኳያ ብዙ የሚቀረው መሆኑን አመልክተዋል።

አዋጁን አስመልክቶ ከምክር ቤቱ አባላት ለቀረቡት ጥያቄዎችና አስተያየቶች ምላሽና ማብራሪያ የሰጡት የኢትጵያ ብሄራዊ ባንክ ገዥ አቶ ማሞ ምህረቱ፤ አዋጁ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የተረጋጋ ሆኖ እንዲቀጥል ያስችላል ብለዋል፡፡

የብሔራዊ ባንክ አደረጃጀትና ዓላማ ግልጽ እንዲሆን ከሌሎች የአቻ ማዕከላዊ ባንኮች ልምድ በመውሰድ በዓለም አቀፍ ደረጃ ያሉ መመሪያዎችን መሰረተ በማድረግ የተዘጋጀ መሆኑን ጠቅሰው፣ በማርቀቁ ሂደትም የእንግሊዝ የስዊዲን፣ የኬንያ የሩዋንዳና ሌሎች አገራት ባለሙያዎች መሳተፋቸውንና ከየሀገሮቹም ሰፊ ልምድ መወሰዱንም አስታውቀዋል፡፡

የባንኩ ገዥ እንዳብራሩት፤ አሁን የወጣው የባንኩ ዋና ቁልፍ ሥራ ምን እንደሆነ በግልፅ ያመላከተ ነው። የዋጋ መረጋጋት እንዲኖር ማስቻል፣ የፋይናንስ ስርዓቱን ጤናማ እንዲሁም ቀጣይነት ላለው እድገት አስተዋፅኦ ማድረግ የባንኩ ሶስት ዋና ዋና ቁልፍ ዓላማዎች ናቸው።

አዋጁ የኢትዮጵያን የቆየ ማዕከላዊ ባንክ አሰራር ከሌሎች ማዕከላዊ ባንኮች አሰራር ጋር እኩል እንዲጓዝ እንዲሁም የማዕከላዊ ባንኩን አሰራር ዘመናዊ የሚያደርግ እና በሕግ፣ በአዋጅ እና በሕገመንግስት ለሕዝቡ የተሰጡትን ኃላፊነቶች በብቃት መወጣት የሚያስችል አውድ ይፈጥራል።

የክሪፕቶ አሴትን በተመለከተ ከምክር ቤት አባላት ለተነሱ ጥያቄዎች በሰጡት ምላሽ የክሪፕቶ አሴትና ቢተኮይንን በሁለት መልኩ ማየት የተሻለ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ይህን አስመልክተው ሲያብራሩ እንዳሉትም፤ በመጀመሪያ የክሪፕቶ ማይኒንግ አለ። ይህ አሁን በኢትዮጵያ ውስጥ በተለይ ከኃይል አቅርቦት መስፋፋት ጋር በተገናኘ /ከታዳሽ ኃይል ጋር ተገናኝቶ/ በስፋት ኢንቨስትመንት እየተደረገበት ይገኛል። ይህም ለኢትዮጵያ የውጭ ምንዛሪ የሚያስገኝ እና ኢትዮጵያ የክሪፕቶ ማይኒንግ መዳረሻ መሆኗ ምንም ችግር የሌለበት ነው። የዳታ ማዕከል ኢንቨስትመንት ተደርጎ የሚታይና አሁን ሥራ ላይ የሚገኝ ነው ብለዋል።

ከዚያ በዘለለ ግን የክሪፕቶ አሴትን እንደመገበያያ መጠቀምን በተመለከተ በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ የተፈቀደ አለመሆኑን አስታውቀዋል። በአጠቃላይ የዓለም የገንዘብ ፖሊሲ አካሄድ አሁን ሰው ጥሬ ገንዘብ /ካሽ/ መጠቀሙ እየቀረ ወደዲጂታል ከረንሲ እንዲዞር እየተደረገ መሆኑን ጠቁመዋል። የክሪፕቶ ከረንሲን በተመለከተ የዓለም የገንዘብ ፖሊሲ በሂደት እየተቀየረ ስለሚሄድ ለውጦችንና ልማቶችን እያየ ብሔራዊ ባንክ እንደሌሎች ማዕከላዊ ባነኮች እንደአስፈላጊነቱ መመሪያ ሊያወጣ እንደሚችል አመላከተዋል።

ምክር ቤቱ በእለቱ መርምሮ ያጸደቀው ሌላው አዋጅ የባንክ ሥራ ረቂቅ አዋጅ ነው፡፡ ረቂቅ አዋጁን አስመልክቶም የምክር ቤቱ የፕላን፤ በጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ዶክተር ደሳለኝ ወዳጄ ሪፖርት እና የውሳኔ ሃሳብ ለምክር ቤቱ አቅርበዋል፡፡

ሰብሳቢው የባንክ ሥራ ረቂቅ አዋጅ የውጭ ባንኮችን በሀገር ውስጥ በማሳተፍ ዘርፉን ለውጭ ኢንቨስትመንት ክፍት በማድረግ የባንኮችን ተወዳዳሪነት እና ውጤታማነት በማሻሻል ለኢኮኖሚው ዕድገት ፋይዳው የጎላ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

የምክር ቤቱ አባላትም በውሳኔ ሀሳቡ ላይ ባቀረቡት ጥያቄና አስተያየት በቂ ቅድመ ዝግጅት ሳይደረግ የውጭ ባንኮች ወደ ሀገር ውስጥ ገብተው እንዲሰሩ ፈቃድ መስጠቱ የሀገር ውስጥ ባንኮች ላይ ተጽእኖ ሊኖረው እንደሚችል መረዳት ይገባል ሲሉ አስገንዝበዋል፡፡

የዓለም አቀፍ ተቋማት ወደ ሀገር ውስጥ መግባታቸው ጠቀሜታው እንዳለ ሆኖ በተለይ የግል ባንኮች ላይ ያለውን ተወዳዳሪነት እና አቅምን ያማከለ ረቂቅ አዋጅ መሆን እንዳለበት ጠቁመዋል፡፡

ብሔራዊ ባንክ የውጭ ባንኮችን ለመቆጣጠር እና ለማስተዳደር የሚያስችል ዘመኑን የዋጀ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት እንደሚጠበቅበትም አሳስበዋል፡፡ የውጭ ባንኮች ከዲጅታል አሰራር ጋር በተያያዘ የሀገርን ሉአላዊነትና ደህንነት በጠበቀ መልኩ የፋይናንስ ስርዓቱ እንዲመራ ብሔራዊ ባንክ በትኩረት መስራት እንዳለበት አስገንዝበዋል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገዢ ዶክተር ማሞ ምህረቱ ለጥያቄዎቹ በሰጡት ምላሽና ማብራሪያ እንዳስታወቁት፤ ረቂቅ አዋጁ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የተረጋጋ ኢንዲሆን ከፍተኛ ድርሻ አለው። ከ17 ዓመታት በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ የባንክ ዘርፉን በተመለከተ ሰፋ ያለ መሰረታዊ ማሻሻያ የተደረገበት አዋጅ ነው። ባንኮች በኢኮኖሚው ውስጥ ቁልፍ ሚና አላቸው። የባንኮችን ጤናማነት ማረጋገጥ፣ የባንክ ሥራ የተሳለጠ መሆን ቀጥታ ከኢኮኖሚ ማረጋጋት ጋር ግንኙነት አለው።

የባንኮች ዋና ሚና ቁጠባ በማሰባሰብ፣ ወደ ተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች በማሰራጨት ለኢንቨስትመንት ቀጣይነት ላለው ልማት ቁልፍ ሚና መጫወት መሆኑን የባንኩ ገዥ ጠቁመው፣ በባንኮች እና በተቆጣጣሪው መስሪያቤቶች ያለው ግንኙነት ከሌሎች ቢዝነሶች የተለየ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል ብለዋል።

እሳቸው እንዳብራሩት፤ ብሔራዊ ባንክ በፋይናንስ ዘርፉ ያለው ተቆጣጣሪ መስሪያቤት በመሆኑ በባንኮች እና በተቆጣጣሪ መስሪያቤት መካከል ያለው ግንኙነት ከሌሎች ተቆጣጣሪ መስሪያቤቶች ካለው ግንኙነት ይለያል። ምክንያቱም ባንኮች ሲመሰረቱ፣ እንቅስቃሴ ሲያደርጉ እንዲሁም ችግር ተከስቶ ባንኮች የሚፈርሱ ከሆነም ከምስረታቸው አንስቶ እስኪፈርሱ ድረስ ቁጥጥር የሚያደርግባቸው መስሪያቤት ብሔራዊ ባንክ ነው።

በመሆኑም ዘርፉን በአግባቡ መምራት ስርዓት ባለው መልኩ ፍቃድ መስጠት፣ የሚኖራቸውን ባለሙያዎች



ብቁነትት ማረጋገጥ እና እነሱ ላይ ማረጋገጫ መስጠት፣ የሚሰሩበትን ሕግና የቁጥጥር ስርዓት ማስቀመጥ፣ መምራት፣ መቆጣጠር እና መከታተል የብሔራዊ ባንክ ቁልፍ ኃላፊነት ነው ሲሉም አብራርተዋል። አዋጁ በዋነኝነት በባንክ ዘርፍ የውጭ እና የሀገር ውስጥ የባንክ ዘርፍ የፍቃድ አሰጣጥ ላይ የቁጥጥር ማዕቀፍ የተሟላ ማድረግ፤ ከሁሉም በላይ ደግሞ ከዓለም አቀፍ አሰራር እና ደረጃዎች እንዲሁም ከወቅቱ ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል ብለዋል።

እንደ ባንኩ ገዥ ማብራሪያ፤ ይህ ጥረት የተደረገበት ዋና ምክንያት በአጠቃላይ የባንክ ዘርፉን ደህንነት፣ ጤናማነት እና መረጋጋት ለማረጋገጥ ነው። በሁለተኛ ደረጃ አዋጁ የሚያደርገው ነገር የባንክ ዘርፉ ለውጭ ኢንቨስትመንት ክፍት እንዲደረግ ፣ ከዚህ በፊት በመንግስት የተላለፈውን የፖሊሲ ውሳኔ ወደ ተግባር ለማሸጋገር እና የውጭ ባንኮች እና ኢንቨስተሮች በዘርፉ ተሰማርተው ለኢኮኖሚው ዕድገት ቀጣይነት ያለው አስተዋፅኦ ማድረግ እንዲችሉ ለማድረግ ነው አዋጁ የወጣው።

ረቂቅ አዋጁ ብዙ የተመከረበት፣ የባለሙያዎች ኮሚቴ ከማቋቋም አንስቶ፣ የሌሎች አገራትን ልምድ በመውሰድ፣ በባንክ ዘርፉ ካሉ ባለሙያዎች ጋር ከመወያየት ጀምሮ ባለፉት ሶስት ዓመታት ሰፊ ዝግጅት ሲደረግበት የቆየ ነው።

አዋጁ አንድ ባንክ የፋይናንስ ቀውስ ሲያጋጥመው ለተከሰተው ቀውስ በብሔራዊ ባንክ እልባት ሰጪነት ሚና ስልጣንና ኃላፊነት በግልፅ ያስቀመጠ የመፍትሔ ሀሳቦችንና አማራጮችን በግልፅ ደንግጓል። ብሔራዊ ባንክ እንደተቆጣጣሪ መስሪያቤት ኃላፊነቱን እንዲወጣ የሚያስችሉትን የሕግ ድንጋጌዎችን አካቷል።

አዋጁን በጥንቃቄ ለተመለከተው ከ50 በመቶ በላይ የሚዘረዝረው የብሔራዊ ባንክ የእልባት ሰጪነት ስልጣን ነው ያሉት አቶ ማሞ፣ አንድ የፋይናንስ ተቋም ችግር ቢያጋጥመው፣ ቀውስ ቢያጋጥመው ምን መደረግ አለበት? በሚል የመጀመሪያ፣ የሁለተኛ፣ የሶስተኛ ደረጃ እርምጃ ምን እንደሆነ እና በአጠቃላይ የአስቀማጮች ሀብት፣ የፋይናንስ ዘርፉ ጤናማነት እና ደህንነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል መሰረታዊ የሕግ ድንጋጌዎችን ያስቀመጠ በአይነቱ የተለየ አዋጅ መሆኑን አብራርተዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ይህም የብሔራዊ ባንክ ከተሰጡት ቁልፍ ኃላፊነቶች መካከል አንደኛውና ዓይነተኛው የፋይናንስ ዘርፉን ጤናማነት መጠበቅ ነው። ይህን ማድረግ ከተቻለ ብቻ የማክሮ ኢኮኖሚው የተረጋጋ ይሆናል፤ የኢኮኖሚ እድገት ቀጣይነት የሚኖረው ይህንን ዓላማ ማሳካት የሚያስችል የሕግ ድጋፍ ሲኖር ነው። ይህንንም ዓላማ ለማሳካት የሚያስችል የሕግ ድጋፍ፣ የአሰራር ማዕቀፍ ያስቀመጠ አዋጅ ነው ሲሉም አስገንዝበዋል።

ከሶስት ዓመት በፊት የባንክ ዘርፉ ለውጭ ኢንቨስትተሮች ክፍት መደረግ እንዳለበት የፀደቀ መሆኑን አስታውሰው፣ አዋጁ በዋናነት የወጣው ይሄንን ውሳኔ ወደ ሕግ ለመቀየር ነው ብለዋል። የፋይናንስ ዘርፉ ለውጭ ኢንቨስትመንት ክፍት በመደረጉ ብሔራዊ ባንክ የመቆጣጠር አቅሙን እንደማያጣ አስታውቀው፣ ዘርፉን በመክፈት የቁጥጥር አቅሙን እንደሚያጠናክር ገልጸዋል፡፡

እንደ ባንኩ ገዥ ገለጻ፤ የፋይናንስ ዘርፉ ክፍት ተደረገ ሲባል የውጭ ባንኮች እዚህ መጥተው እንደፈለጉ ይሰራሉ ማለትም አይደለም። መክፈቱ አለ፤ አከፋፈቱ ደግሞ የራሱ መንገድ አለው። በመጀመሪያ የውጭ ባንኮች መጥተው እዚህ ተቀጥላ ኩባንያ ሊያቋቁሙ ይችላሉ። ሁለተኛ የውጭ ባንኮች መጥተው ከሀገር ውስጥ ባንኮች ጋር በሽርክና ሊሰሩ ይችላሉ። ሶስተኛ የውጭ ባንኮች መጥተው ቅርንጫፍ እዚህ ሊመሰርቱ ወይም የእንደራሴ ቢሮ የሚከፍቱበት ሁኔታም ይኖራል። ይህ ግን የውጭ ባንኮች መጥተው የኢትዮጵያን ባንክ ሊያጥለቀልቁ የሚችሉበት ሁኔታ እንደማይኖር ተናግረዋል። በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የሚፈልገውን የብድር እና የውጭ ምንዛሪ ግኝት በማስፋት እና አምራች የሚባሉት የልማት ዘርፎች በቂ ብድር አግኝተው የኢኮኖሚ ዕድገት እንዲቀጥል የሚያደርግ ነው ሲሉም ገልጸዋል።

እሳቸው እንዳብራሩት፤ የኢትዮጵያ ፋይናንስ ዘርፍ ተጨማሪ ዘመናዊ አዳዲስ አሰራሮች እንዲኖረው የሚያስችል አውድ ለመፍጠር የወጣ አዋጅ ነው። በእንዲህ ዓይነቱ የፖሊሲ ውሳኔ መሰረተ የኢትዮጵያ ባንኮች የበለጠ ይጠናከራሉ፤ የበለጠ ይጎለብታሉ፣ የበለጠ ለአምራች ዘርፉ ፋይናንስ ያቀርባሉ፣ የበለጠ ሀብታቸው ይጨምራል ሲሉም አስታውቀዋል፡፡

የውጭ ባንኮች ገቡም አልገቡም የኢትዮጵያ ባንኮች ቀጣይነት ባለው መንገድ አቅማቸውን እያሳደጉ፣ ካፒታላቸውም እየጨመረ መሄድ ይኖርበታል። አስፈላጊ ከሆነም ከሌሎች ባንኮች ጋር እየተቀናጁ አሴታቸውን ትርፋቸውን፣ ካፒታላቸውን የሚሰበስቡበትን ሀብት መጨመር መቻል አለባቸው። የውጭ ባንኮች ስለሚገቡ ብቻ ሳይሆን ኢኮኖሚው እያደገ ስለሚሄድ ተለዋዋጭ ከሆነው ዘመን ጋር መሄድ ይጠበቅባቸዋል ብለዋል።

የባንክ ሥራ አዋጁ ከ17 ዓመታት በኋላ ታሪካዊ የተባለውን የባንኮች አሰራር አዋጅ ቁጥር 1360/2017 በሶስት ተቃውሞ እና በአብላጫ ድምፅ አፅድቋል። የብሄራዊ ባንክ አዋጁ ደግሞ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ አዋጅ 1359/2017 በሚል በሙሉ ድምፅ ፀድቋል።

# ስፖርት



## የአትሌቲክሱን ችግር አውቆ ለመፍትሔ የሚሠራ አመራር ሊመጣ ይገባል

**-የኢትዮጵያ አትሌቶች ማኅበር**

**ብርሃን ፈይሳ**

ኢትዮጵያ ከታላቁ አትሌት ሻምበል አበበ ቢቂላ አንስቶ በስመጥር አትሌቶቿ ብቃት በስፖርቱ ዓለም ለዘመናት ስትከበር የኖረች ሃገር ናት። ለዚህ ደግሞ ጀግኖች አትሌቶች ሊመሰገኑ ይገባል። የሚሊዮኖችን አደራ ተሸክመው በዓለም አቀፍ መድረኮች የሚሮጡ ብርቅዬ አትሌቶች ከሌሉ ስፖርቱ የለም። ስለዚህ ለእነሱ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠርና በየትኛውም ሁኔታ ቅድሚያ መስጠት ስፖርቱን የሚመራው ፌዴሬሽን ኃላፊነት ነው።

ይሁን እንጂ እንደየጊዜው ዘመናዊና ምቹ ሁኔታን ለአትሌቶች ከመፍጠር ይልቅ ዕንቁ አትሌቶችን የሚያስከፋና ሀገርም ውጤት እንድታጣ የሚያደርጉ አስተዳደራዊ ችግሮች በየዘመኑ ፌዴሬሽን ውስጥ ጠፍቶ አያውቅም። እንዲህ አይነት አስተዳደራዊ ችግሮችን ለመቅረፍ ከዚህ ቀደም አትሌቲክሱንና አትሌቶችን መረዳት አልቻሉም በሚል ወቀሳ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በስፖርቱ ባለፉ ባለሙያዎች እንዲመራ መደረጉ ይታወቃል። ይሁን እንጂ በአትሌትነት ዘመናቸው የተሳካላቸው አትሌቶችም ከችግር የፀዳ የፌዴሬሽን አመራር ለመሆን ሲቸገሩ በግልጽ ይታያል።

አትሌቶች ዛሬም ድረስ ትክክለኛውን የፌዴሬሽን አመራር እንዳላገኙ ቅሬታ ያቀርባሉ። ከቀናት በኋላ በሚካሄደው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን 28ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ ግን ሁነኛውን የስፖርት መሪ ለማግኘት ተስፋ አድርገዋል።

ጠቅላላ ጉባኤውን ተከትሎ በሚደረገው የፌዴሬሽኑ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትና የፕሬዚዳንት ምርጫ፤ የስፖርቱን ቁልፍ ችግር አንጥሮ በማውጣት ለመፍትሔ የሚሠራ ሰው ወደ አመራርነት ሊመጣ እንደሚገባም የኢትዮጵያ አትሌቶች ማኅበር ፅኑ አቋም አለው። የማኅበሩ ፕሬዚዳንት አትሌት የማነ ፀጋዬ፣ አዲስ የሚሰየመው ሥራ አስፈጻሚ ትኩረት ሊያደርግ ከሚገባቸው ጉዳዮች መካከል አንገብጋቢውና በቅርቡ በተደረገው የፓሪስ ኦሊምፒክ ላይ የታየው የብሔራዊ ቡድን አትሌቶችና አሠልጣኞች የመምረጫ መስፈርት መሆኑን ይናገራል።

አትሌቶችን ለሥነልቦና ጫና እየዳረጋቸው የሚገኘውና ውድድሩ እስከሚካሄድበት ሰዓት ድረስ ማን ሊመረጥ ይችላል የሚለውን አለማወቅ ከባድ ችግር ሲፈጥር ታይቷል። አትሌቶች በዚህና በሌሎች ምክንያቶች ለውድድር ከሄዱበት አዝነው መመለሳቸውም ይታወሳል። ስለዚህ ይህ ችግር ሊፈታ የሚገባው ቁልፍ ጉዳይ መሆኑ ነው አትሌት የማነ የሚናገረው።

ሌላኛው በየጊዜው እየተባባሰ ያለና መፍትሔም ያላገኘው የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራ ጉዳይ ሲሆን፤ የነበሩትም ከአገልግሎት ውጪ በመሆናቸው አትሌቶች ልምምድ ለመሥራት በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ለማለፍ እየተገደዱ ነው። ለወራት በእድሳት ምክንያት የተዘጋው የአዲስ አበባ ስታዲየም ለዓመታት ወደ ሥራ ባለመመለሱ አትሌቲክሱን እየፈተነው ይገኛል። በሜዳው ምክንያት መሙ አገልግሎት እንዳይሰጥ መደረጉ ለእግር ኳስ ሲባል አትሌቲክሱን ያሳጣል የሚል ስጋት ያሳደረበት የማነ ‹‹እንደ ጀግናው አትሌት ቀነኒሳ በቀለ እና የአትሌቲክስ ክለቡ መብራት ኃይል ያሉት መም በመገንባት አስተዋፅዖ ለማድረግ እየሞከሩ ቢሆንም መንግሥትስ ምን አደረገ?›› ሲልም ይጠይቃል።

እንደ የማነ ገለፃ፣ የፌዴሬሽን አመራሮች ከመንግሥት ጋር በመሆን ስፖንሰር አፈላልገው ብዙ መሥራት የሚችሉ ቢሆንም አንድም መፍትሔ ሳይዘይዱ የሥራ ዘመናቸውን ማጠናቀቃቸው የእነሱ እንጂ የሌላ አካል ድክመት አይደለም። ይህ ችግር በሀገር ውጤት ላይ የራሱ ተፅዕኖ እያሳረፈ በመሆኑ በስፖርቱ ትልቅ ስም ያላት ኢትዮጵያ ክብሯ ከእጇ እንዳይወጣም ስጋት አለው።

‹‹የእነ አበበ ቢቂላ፣ ምሩፅ ይፍጠር፣ ማሞ ወልዴ ሃገር ልምምድ መሥሪያ የላትም መባሉ አሳፋሪ ነው። በኢትዮጵያ የሚሠሩ በርካታ ማናጀሮች እንደመኖራቸው ካምፕ እንዲሁም የማዘውተሪያ ስፍራ እንዲገነቡ ማድረግ ሲገባ እነሱን የሚያሳድድ ሕግ እያወጡ ስፖርቱ ተጠቃሚ እንዳይሆን ተደርጓል›› የሚለው አትሌት የማነ፣ በመሆኑም መጪው ሥራ አስፈጻሚ ስፖርቱ ላይ የሚሠሩ አካላትን የሚያርቅ አካሄድ ሳይሆን የሚነሱ ቅሬታዎችን በመፍታትና የተቀላጠፈ አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ አትሌቲክሱን እንዲጠቅሙ መሥራት እንዳለባቸው ተናግራል።

ከምርጫ መስፈርትና ከማዘውተሪያ ስፍራዎች አለመኖር ጋር በተያያዘ አትሌቶች ላይ እየደረሰ ካለው ጫና ባለፈ የብሔራዊ ቡድን መፍረስም ሌላኛው የአትሌቲክሱ ራስ ምታት ነው። በተለይም በሜዳ ተግባራት ችግሩ ጎልቶ የሚታይ በመሆኑ አዲሱ ሥራ አስፈጻሚ ሊሠራበት የሚገባ ጉዳይ ነው መሆኑንም ያብራራል። አመራሩ የኢትዮጵያን አትሌቲክስ ከማስተዳደር ባለፈ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተፅዕኖ የማሳደር አቅምም መፍጠር አለበት ሲልም አሳስቧል። ይኸውም ኢትዮጵያን ጨምሮ የምሥራቅ አፍሪካ ሃገራት ውጤታማ የሆኑበትና አሁን ላይ በመጥፋት ላይ የሚገኙትን የመም ረጅም ርቀት ሩጫዎች ጨምሮ አሉታዊ ሚና የሚጫወቱ ዓለም አቀፍ ውሳኔዎችን የማስቀልበስ ችሎታን ያዳበሩና በተቋሙ እስከማገልገልም ሊደርስ የሚችል ነው።

የመጪዎቹ አራት ዓመታት የኢትዮጵያ አትሌቲክስን ዕጣ ፋንታ የሚወስነው ቁልፍ በመራጮች እጅ ላይ ነው። ስለዚህም ድምፅ ያላቸው የጠቅላላ ጉባኤ አባላት ድምፃቸውን ስፖርቱን ለመለወጥ ቃል ለገቡት ብቻም ሳይሆን ቃላቸውን በተግባር መለወጥ ለሚችሉ አካላት ሊሰጡ እንደሚገባ ፕሬዚዳንቱ በአደራ ጭምር መልዕክቱን አስተላልፏል።